

# ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. የተደረገውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ የተመለከተ ሪፖርት

ቀን፡- ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም.

Election Mission
IRI
NDI
Ethiopia 2021

ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. የተደረገውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ የተመለከተ ሪፖርት

የቅጂ መብቱ የተጠበቀ ነው © 2013 ዓ.ም. ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት (IRI) እና ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት (NDI)

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

የዚህ ሥራ ክፍሎች ከንግድ ውጭ ለሆኑ ዓላማዎች ሊባዙ እና/ወይም ሊተረጎሙ ይችላሉ፤ ሆኖም ግን ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት እና ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት የሥራው ምንጮች መሆናቸው ሊገለጽ እና የትርጉሙ ቅጂ ሊላክላቸው ይገባል። ቅጂዎቹን በሚከተለው አድራሻ ይላኩ፡-

በተለይ ለውጭ ጉዳይ መምሪያ
ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት
1225 Eye Street NW, Suite 800
Washington, DC 20005
info@iri.org

በተለይ ለግንኙነት መምሪያ
ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት
455 Massachusetts Ave NW, 8th Floor
Washington, DC 20001
http://www.ndi.org/contact

# ማውጫ


የተልዕኮው አጭር ቅኝት . . . 1

በአጭሩ የቀረቡ ግኝቶች እና ወዲያውኑ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገቡ ምክረ-ሀሳቦች . . . 2

የፖለቲካው ምህዳር . . . 4

ትንተና . . . 6

- የሕግ ማዕቀፍ . . . 6
- የምርጫ ሥርዓት . . . 7
- የምርጫ አስተዳደር . . . 7
- የምርጫው መተላለፍ . . . 8
- ኮቪድ-19 እና የምርጫው ሂደት . . . 9
- የምርጫ ክልሎች አከላለል . . . 9
- የመራጮች ምዝገባ . . . 10
- የመራጮች ስልጠና . . . 11
- የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ . . . 11
- የዕጩዎች ምዝገባ . . . 11
- የምርጫ ቅስቀሳው ምህዳር . . . 12
- ለምርጫ ቅስቀሳ የሚውል ገንዘብ . . . 13
- ከምርጫው ጋር በተያያዘ ያለው የጸጥታ ሁኔታ እና ግጭቶች . . . 14
- የመገናኛ ብዙሀን ምህዳር . . . 15
- ማህበራዊ ሚዲያ . . . 16
- የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማካተት . . . 17
- የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች እና የዜጎች ተሳትፎ . . . 20
- በዜጎች የሚደረግ ምርጫ መታዘብ . . . 21
- የምርጫው ቀን . . . 22
- የድምጽ ቆጠራ እና ውጤት ማሳወቅ . . . 22
- በምርጫ ሂደት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች . . . 23

ምክረ-ሀሳቦች . . . 24

- የሕግ ማዕቀፍ . . . 24
- የምርጫ አስተዳደር . . . 24
- ጸጥታ እና በምርጫ ሂደት የሚፈጠሩ ግጭቶች . . . 25
- የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የምርጫው ምህዳር . . . 25
- ማካተት . . . 26
- የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች፣ የዜጋ ምርጫ ታዛቢዎች እና የመራጮች ምዝገባ . . . 27

የመረጃው ምህዳር . . . 27

# የተልዕኮው አጭር ቅኝት

ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት (NDI) እና ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት (IRI) ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ግብዣ የቀረበላቸው ሲሆን ተቋማቱ በጋራ የሚያከናውኑት የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮ (Limited Election Observation Mission for Ethiopia) ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይፋዊ ዕውቅና ተሰጥቶታል። ተልዕኮው የተከናወነው በኢትዮጵያ ሕግ እና ተአማኒነት ያለው ዓለም አቀፍ ምርጫን የመታዘብ ሂደትን ለማከናወን እንደ መሠረት በሚያገለግለው እና በ56 የበይነ መንግስታት እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በተፈረመው ዓለም አቀፍ ምርጫ የመታዘብ መርሆዎች ዲክላሬሽን (Declaration of Principles for International Election Observation) መሠረት ነው።[1] ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት እና ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ከመራጮች፣ ከምርጫ ኃላፊዎች፣ ከዕጩዎች፣ ከፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች እና አባላት፣ ከመንግስት ባለስልጣናት እና ከመገናኛ ብዙሀን እንዲሁም ከሲቪል ማህበራት ተወካዮች ለተደረገላቸው መልካም አቀባበል እና ትብብር ምስጋና ይሰማቸዋል። በተጨማሪም ተልዕኮው ሌሎች ዓለም አቀፍ የታዛቢዎች ልዑካን ቡድኖችን እና የኢትዮጵያ ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ የሆኑ የዜጋ ታዛቢዎች ቡድኖችን አነጋግሯል። ተልዕኮው የተጀመረው እ.ኤ.አ. ማርች 2021 ሲሆን ለጳጉሜ 1 ቀን የተቆረጠላቸውን እና ይከናወናሉ ተብለው የሚጠበቁትን የተላለፉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤት ምርጫዎች ተከትሎ እስከ እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 2021 ይቀጥላል። ይህ ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት/ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት በገለልተኝነት የሚያከናውኑት የጋራ ሥራ የሚያከናወነው ከዩናይትድ ስቴትስ የዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የጤና ቀውስ በፈጠራቸው ውስንነቶች የተነሳ ተልዕኮው የተከናወነው ገለልተኛ እና ከወገንተኝነት ነጻ የሆኑ ግምገማዎች በሚከናወኑባቸው መርሆዎች ዲክላሬሽን (Declaration of Principles for independent, impartial assessments) ውስጥ በተቀመጡት መርሆዎች እና በአፍሪካ ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች የሚመሩባቸውን መርሆዎች በተመለከተ የአፍሪካ ህብረት ያወጣውን ዲክላሬሽን (African Union (AU) Declaration on the Principles Governing Democratic Elections in Africa) ጨምሮ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አህጉራዊ ሰነዶች መሰረት የርቀት ክንውን ዘዴን በመጠቀም ነው። በተጨማሪም የኢትዮጵያዊያንን እንዲሁም የተልዕኮውን አባላት ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል በአጠቃላይ ተልዕኮው ወቅት ሁሉም አባላት ዓለም አቀፍ እና የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና እርምጃዎችን ተከትለዋል።

የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ዋና ቡድን የተልኮው ዳይሬክተር በሆኑት ስቴፋኒ ሞንዶን፤ የተልዕኮው ምክትል ዳይሬክተር በሆኑት ስቴፋን ዝዌድ፤ እና የረጅም ጊዜ ትንተና ባለሞያዎች አስተባባሪ በሆኑት ናታሻ ሮዝቻይልድ የተመራ ነበር። የተልዕኮው ዳይሬክተር መቀመጫቸው አዲስ አበባ የነበረ ሲሆን የኮቪድ-19 ፕሮቶኮሎች በፈቀዱባቸው ጊዜያት የተልዕኮው ምክትል ዳይሬክተርም አብረዋቸው ነበሩ። በተጨማሪም ዋና ቡድኑ ከርቀት ሆነው በተለዩ ዘርፎች[2] ላይ የሚሰሩ ስምንት ዓለም አቀፍ የረጅም ጊዜ ትንተና ባለሞያዎችን (Long-Term Analysts) ያካተተ እና መቀመጫቸውን አዲስ አበባ ባደረጉ ስምንት ብሔራዊ ረዳት ተመራማሪዎች እንዲሁም ከዘጠኝ ክልሎች እና "በቻርተር የምትተዳደር ከተማ" ከሆነችው ድሬደዋ በሚሠሩ አሥር የክልል ተጠሪዎች[3] የተደገፈ ነበር። የተሻሻለው ምርጫ የመታዘቢያ ዘዴ የረጅም ጊዜ ትንተና ባለሞያዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን እና ቁልፍ ተዋንያንን ጨምሮ ከኢትዮጵያ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅድመ-ምርጫ ኩነቶች እና ክስተቶች ዙሪያ መደበኛ በሆነ መልኩ በቀጥታ ግንኙነት እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ነበር። ባለድርሻ አካላትን በቀጥታ በማነጋገር የረጅም ጊዜ ትንተና ባለሞያዎች የሰበሰቧቸው የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች መቀመጫቸውን አዲስ አበባ ባደረጉ የረጅም ጊዜ ትንተና ባለሞያዎች ቡድን እና በክልል ተጠሪዎች ይበልጥ ተጠናክሮ የኢትዮጵያን ምርጫ ለመታዘብ ውስን ተልዕኮው ትንተና እንደ ግብዓት ጥቅም ላይ ውሏል። በተልዕኮው የቆይታ ጊዜ ውስጥ ተልዕኮው በመቶዎች ከሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ባለድርሻ አካላት ጋር የበይነ መረብ ውይይት እና በአካል የሚደረጉ ስብሰባዎችን አድርጓል።

ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት/ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ቦርድ አባል እና የቀድሞ የዩናይትድ እስቴትስ የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት ጸሀፊ በሆኑት በአምባሳደር ጆኒ ካርሰን፤ የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት የቦርድ አባል እና የቀድሞ የዩናይትድ እስቴትስ የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት ጸሀፊ በሆኑት በተከበሩ ኮንስታንስ ቤሪ ኒውማን፤ እና የቀድሞ የኬኒያ ገልተኛ የምርጫ ቦርድ እና የድንበር ኮሚሽን ሊቀመንበር በሆኑት በተከበሩ አህመድ ኢሳክ ሀሰን የተመራ የበይነ መረብ የቅድመ-ምርጫ ግምገማ ተልዕኮ (Virtual Pre-Election Assessment Delegation ) ከሚያዝያ 1 እስከ 18 ያዘጋጀ ሲሆን ይህም የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ወሳኝ አካል ነው።[4] የበይነ መረብ የቅድመ-ምርጫ ግምገማ ተልዕኮው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሊቀ መንበር የሆኑትን የተከበሩ ብርቱካን ሚደቅሳን ጨምሮ ከበርካታ የተለያየዩ ቁልፍ የምርጫ እና የፖለቲካ ባለድርሻ አካላት ጋር ከፍተኛ የበይነ መረብ ምክክሮችን አድርጓል። ሪፖርቱ[5] ግንቦት 5 ቀን የወጣ ሲሆን የቅድመ-ምርጫ ምህዳሩን እና ለምርጫው የሚደረጉ ዝግጅቶችን የተመለከተ ትንተና የቀረበበት እንዲሁም የምርጫውን አሳታፊነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ለማሻሻል ከሰኔው ምርጫ አስቀድሞ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ 12 ተጨባጭ ምክረ-ሀሳቦች የቀረቡበት ነበር።

የበይነ መረብ የቅድመ-ምርጫ ግምገማ ተልዕኮውን ሪፖርት ተከትሎም የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ሰኔ 2 ቀን የምርጫ ክትትል መግለጫ[6] አውጥቷል። የምርጫ ክትትሉ ከበርካታ የተለያዩ የምርጫ እና የፖለቲካ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ከሚያዝያ 18 እስከ ግንቦት 23 ድረስ በረጅም ጊዜ የትንተና ባለሞያዎች (LTAs) ከርቀት የተከናወኑ ጥልቅ ቃለ መጠይቆችን እና አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ግምገማን መሠረት ያደረገ ነበር። ተልዕኮው ጳጉሜ 1 እንዲከናወኑ ቀን ተቆርጦላቸው የተላለፉት ምርጫዎች መከናወናቸውን ተከትሎ ሁለተኛ የምርጫ ክትትል መግለጫውን የማውጣት ዕቅድ አለው።

---

1 በተጨማሪም ተልዕኮው በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ በሚፈጸሙ ጥቃቶች ላይ ማተኮርን ጨምሮ ከዓለም አቀፍ ምርጫን የመታዘብ ሂደት ጋር የተያያዙ የሥርዓተ-ጾታ እሳቤዎች መመሪያ መርሆዎች ዲክላሬሽን (Declaration of Principles (DoP) Guidelines on Gender Considerations in International Election Observation) መሠረት የተከናወነ ነው።

2 የፖለቲካ እና የምርጫ ምህዳር፣ የሕግ ማዕቀፍ፣ የምርጫ አስተዳደር፣ የመረጃ ምህዳር፣ የምርጫ ጸጥታ፣ የሴቶች ተሳትፎ፣ የአካል ጉዳተኞች እና ወጣቶች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና በቁጥር አናሳ የሆኑ በሔረሰቦች ተሳትፎ እና የዜጎች ተሳትፎ።

3 የክልል ተጠሪዎች ተመድበውባቸው የነበሩት ዘጠኝ ክልሎች የሚከተሉት ናቸው፡- አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሱማሌ፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ፣ ሲዳማ፣ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች (ደ/ብ/ብ/ሕ) ክልል፣ ጋምቤላ እና ሀረር።

4 በተጨማሪም ተልዕኮው የሚከተሉትን የምርጫ እና አህጉራዊ ባለሞያዎች ያካተተ ነበር፡- የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ምክትል ፕሬዝዳንት የሆኑትን ሼሪ ብራያንን፤ የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት አፍሪካ ዲቪዥን ዳይሬክተር የሆኑትን ግሬጎሪ ከርንስን፤ የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት የደቡባዊ እና ምስራቅ አፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር የሆኑትን ጀሚማ ባርሎውን፤ እና የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት ከፍተኛ የአፍሪካ ጉዳይ አማካሪ የሆኑትን ምቬምባ ዲዞሌሌን።

5 የበይነ መረብ የቅድመ-ምርጫ ግምገማ ተልዕኮውን ሪፖርት የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት እንዲሁም የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ድረገጾች ላይ ማግኘት ይቻላል።

6 የምርጫ ክትትል መግለጫውን የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት እንዲሁም የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት ድረገጾች ላይ ማግኘት ይቻላል።

በተጨማሪም የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ከሰኔ 9 እስከ 17 አዲስ አበባ ውስጥ በነበረ የምርጫ ዕለት የቴክኒክ ቡድን የተደገፈ ነበር።[7] ቡድኑ ከሰኔ 14ቱ ምርጫ አስቀድሞ በኢትዮጵያ ጉብኝት ያደረገ ሲሆን ዓላማውም ስለ ቅድመ-ምርጫ ጊዜው እንዲሁም በምርጫው ዕለት እና ያንን ተከትሎ የድምጽ አሰጣጥ፣ የቆጠራ እና ውጤት የማስላት ሂደቶች ስለሚከናወኑበት መንገድ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ስላሏቸው አመለካከቶች የላቀ ግንዛቤ ማግኘት ነበር። የቴክኒክ ቡድኑ ዕውቅና ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም ከኮቪድ-19 እና ከጸጥታ ጋር በተያያዙ ውስንነቶች የተነሳ አባላቱ በምርጫው ዕለት የነበሩ ሂደቶችን ስልታዊ በሆነ መልኩ ያልታዘቡ ሲሆን ባለድርሻ አካላትን እንዲሁም በተለይም ደግሞ የዜጋ ታዛቢዎችን እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ታዛቢዎችን ስለ ምርጫው ባላቸው አመለካከት ዙሪያ በማነጋገር ላይ አተኩረዋል። ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት/ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት ጳጉሜ 1 የሚደረገውን ምርጫ የሚመለከተውን ሁለተኛውን የምርጫ ክትትል መግለጫ እስከሚያወጡ ድረስ ከምርጫ ጋር በተያያዘ የሚኖሩ ክስተቶችን መከታተላቸውን ይቀጥላሉ።

# በአጭሩ የቀረቡ ግኝቶች እና ወዲያውኑ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገቡ ምክረ-ሀሳቦች

የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው የምርጫው ሂደት ያልተጠናቀቀ መሆኑን የሚገነዘብ በመሆኑ ስለ አጠቃላይ የምርጫ ሂደቱ መደምደሚያዎችን እያቀረበ እንዳልሆነ ሊያስምርበት ይወዳል እንዲሁም ምርጫው ያለውን ትርጉም እና ባህሪ ከማንም በላይ የሚወስነው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚሆን በተጨማሪ የሚያስምርበት ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ሂደቱን መከታተሉን እና ኢትዮጵያ ውስጥ ግልጽ እና ሰላማዊ ምርጫ ዕውን እንዲሆን በመሥራት ላይ ካሉ አካላት ጎን መቆሙን የሚቀጥል ይሆናል።

ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. የተደረገው የኢትዮጵያ ምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሲቪል ማህበራት የምርጫ ተዋንያን ሆነው ብቅ እንዲሉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አቅሙን እና ተአማኒነቱን ለመገንባት አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን እንዲወስድ የሚያስችሉ ወሳኝ ማሻሻያዎችን ተከትሎ የተደረገ ነው። ምንም እንኳን የተወሰዱ አዎንታዊ እርምጃዎች ቢኖሩም ሀገሪቱ በወረሰችው አምባገነን አገዛዝ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ የቆዩ የብሔር እና የቋንቋ እንዲሁም የፖለቲካ ኃይል ክፍፍሎችን መሰረት ባደረጉ ስሩፋት የሚስተዋሉ የጸጥታ ችግሮች እና ግልጽ ግጭቶች፣ የምርጫ የመጫወቻ ሜዳው ላይ ባለው የሚዛን መዛባት፣ የፖለቲካ ሀሳብን ከመግለጽ አንጻር ወደኋላ ሸርተት የማለት ሁኔታዎች በመከሰታቸው፣ ከሎጂስቲክስ ጋር በተያያዙ ተግዳሮቶች እና የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ባስከተላቸው ውጤቶች የተነሳ የፖለቲካ ምህዳሩ፣ ተሳትፎው እና ፉክክሩ አሁንም በከፍተኛ ሁኔታ ውስን ነበር።

ምንም እንኳን ሰኔ 14 ከተደረገው ምርጫ አስቀድሞ የነበረው አጠቃላይ የምርጫ ሂደት በምርጫ ምህዳሩ ውስጥ ባሉ ከፍተኛ እና የተለያዩ ተግዳሮቶች የተሞላ ቢሆንም ከዚህ ቀደም ከነበሩት ምርጫዎች ጋር ሲነጻጸር በተለይም ደግሞ ብሔራዊ የምርጫ አካሉ ከመቋቋሙ እና ተወዳዳሪዎቹ እና የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ብሔራዊ ምርጫውን የሚታዘቡበት ሁኔታ ከመመቻቸቱ ጋር በተያያዘ ወሳኝ መሻሻሎች የታዩበት ነበር። ሆኖም ግን የምርጫ ምህዳሩ ሰብአዊ እና ሲቪል ነጻነቶችን፣ የምርጫ ቅስቀሳን፣ ለሁሉም አካላት በበቂ ሁኔታ ጸጥታ ማስጠበቅን እና አጠቃላይ ሰላም እና ጸጥታን የሚመለከቱ ቁልፍ የደረጃ መስፈርቶችን ያሟላ አልነበረም።[8] አዎንታዊ ሁኔታዎቹ ኢትዮጵያውያን ትክክለኛ እና ጥልቅ ውይይት ለማድረግ አስፈላጊው ፈቃደኝነት ካላቸው ለወደፊቱ ይበልጥ ተአማኒነት ያላቸው ምርጫዎችን ለማድረግ እንደ መሠረት ሊያገለግሉ እና ብሔራዊ እርቅ እንዲመጣ እና ተጨማሪ ዴሞክራሲያዊ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ።

ከብዙ ማስተላለፍ በኋላ ኢትዮጵያ ሰኔ 14 ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 547 የምርጫ ክልሎች ውስጥ በ425 የምርጫ ክልሎች ምርጫ አድርጋለች።[9] የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በፈጠራቸው ውስንነቶች የተነሳ ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት እና ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን የጋራ ተልዕኮአቸውን በዋነኝነት የርቀት ክንውን ዘዴን በመጠቀም ማከናወን ኖሮባቸዋል። የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ለኢትዮጵያ ዜጎች እና ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የምርጫ ምህዳሩን በተመለከተ ገለልተኛ፣ ከወገንተኝነት ነጻ የሆነ እና ትክክለኛ ግምገማ ለመስጠት እና ዴሞክራሲያዊ ምርጫን በተመለከተ የተቀመጡ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ደረጃዎችን መሠረት ያደረጉ እና ከሀገሪቱ ሕግ እና ከዓለም አቀፍ ምርጫ የመታዘብ መርሆዎች ዲክላሬሽን (Declaration of Principles for International Election Observation) ጋር የሚጣጣሙ ገንቢ ምክረ-ሀሳቦችን ለማቅረብ ያስቻለ ነው።

ኢትዮጵያ የምታከናውነውን ምርጫ መጀመሪያ ላይ በርካታ ባለድርሻ አካላት ያዩት በሀገሪቱ የአምባገነንነት ታሪክ የሚቋጭበት እና ይበልጥ አሳታፊ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት አስተዳደር የሚገነባበት መልካም ዕድል አድርገው ነበር። አብይ አህመድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ከመሾማቸው ጋር ተያይዞ ከ2010 ዓ.ም. ጀምሮ በሀገሪቱ ተግባራዊ የተደረጉ ማሻሻያዎች ዜጎች፣ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና መገናኛ ብዙሀን የላቁ ነጻነቶችን ማግኘታቸውን ጨምሮ መጠነ ሰፊ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ለውጦችን አስከትለዋል። ከምርጫ፣ ከሲቪል ማህበራት ድርጅቶች እና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በተያያዙ ሕጎች ላይ የተደረጉ ለውጦች በሕግ ማዕቀፉ ውስጥ የነበሩ በርካታ ገዳቢ ይዘቶችን ፈትተዋል። በጣም የተከበሩ የቀድሞ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር እና ዳኛ የነበሩት ብርቱካን ሚደቅሳ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሊቀ መንበር ተደርገው መሾማቸው ተአማኒነት ያለው ምርጫ በማድረግ ረገድ ትልቅ ቦታ የተሰጠው እና በአጠቃላይ የፖለቲካው ማህበረሰብ ዘንድ ተቋሙ ያለውን ክብር ያሻሻለ ሲሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሚተዳደርበት ሕግ ላይ የተደረጉት ለውጦች ደግሞ የተቋሙን ነጻነት አጠናክረውታል።

በአንድ ወቅት ታግደው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕጋዊ ሆነዋል እንዲሁም በምርጫው ለመወዳደር መደራጀት ጀምረዋል። ፍርድ ቤቶች የዜጎችን እና የፓርቲዎችን በምርጫው የመወዳደር መብት የሚደግፉ ወሳኝ ውሳኔዎችን ሰጥተዋል። ለረጅም ጊዜ ተጨቁነው የቆዩት ሲቪል ማህበራት መልሰው ብቅ ማለት እና በመራጮች ስልጠና እና በዜግነት ትምህርት እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሁም የምርጫ ሂደቱን ገለልተኛ እና ከወገንተኝነት ነጻ በሆነ መልኩ በመታዘብ መሳተፍ ጀምረዋል። በአንጻሩ ይበልጥ ሰፋ ባለ መልኩ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን (ኢሰመኮ) የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና የላቀ የመገናኛ ብዙሀን ነጻነት (በተለይም ደግሞ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን እና በይነ መረብ) ላይ መሥራት ጀምሯል፤ መረጃን የማጋራት እና ከአዳዲስ ሀሳቦች ጋር የመታዋወቅ ሁኔታን አጠናክሯል። በተጨማሪም ሴቶች ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ መሾማቸው እና ተመርጠው መቀመጣቸው የምርጫ ሂደቱን ይበልጥ አሳታፊ ማድረግ እና የፖለቲካ ህይወትን ማስፋት ዋጋ እንዳለው ያመላከተ ወሳኝ እርምጃ ነው።

7 የቴክኒክ ቡድኑ የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት የደቡባዊ እና ምስራቅ አፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር በሆኑት በጀሚማ ባርሎው የተመራ እና የሚከተሉትን ያካተተ ነበር፦ የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት አፍሪካ ዲቪዥን ዳይሬክተር የሆኑትን ግሬጎሪ ከርንስን፣ የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት ከፍተኛ የአፍሪካ ጉዳይ አማካሪ የሆኑትን ምሼምባ ዲዞሌሌን፤ እና የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት የምርጫ ከፍተኛ አማካሪ የሆኑትን ሪቻርድ ኤል. ክሊይንን።

8 ለምሳሌ "የዴሞክራሲያዊ ምርጫ መርሆዎችን በጥብቅ ተግባራዊ ማድረግ"ን የሚመለከተውን በአፍሪካ ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች የሚመሩባቸውን መርሆዎች በተመለከተ የአፍሪካ ህብረት ያወጣውን ዲክላሬሽን ክፍል 3 ይመልከቱ፡፡

9 በተጨማሪም አብዛኛዎቹ የክልል እና የከተማ ምክር ቤት ምርጫዎች የተከናወኑ ቢሆንም በሀገሪቱ ደቡብ-ምዕራብ ክፍል ክልል መሆንን በተመለከተ ህዝበ ውሳኔ አልተከናወነም።

ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት በምርጫው ምህዳር ውስጥ የነበሩ ዋና ዋና ችግሮች ሰኔ 14 የተደረገው ምርጫ እስከሚደርስ በነበረው ረጅም ጊዜ ውስጥ ተባብሰው ነበር። ሀገሪቱ ለረጅም ጊዜ ከቆዩ የብሔር ውጥረቶች እና ከስልጣን ክፍፍል ጋር የተያያዙ በርካታ የጸጥታ ችግሮች አጋጥመዋት የነበሩ እና አሁንም የቀጠሉ ሲሆን ይህም በርካታ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ያለመረጋጋትን እና ግልጽ ግጭትን አስከትሏል። ግልጽ ግጭት በመኖሩ የተነሳ 38 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልሎች ባሏት በትግራይ ክልል ምርጫ እንዲደረግ ያልታቀደ ሲሆን የጸጥታ እና የሎጂስቲክስ ችግሮች በመኖራቸው የተነሳ በሌሎች 82 የህዝብ ተዋካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልሎች ምርጫው ወደ ሌላ ጊዜ ተላልፏል። በርካታ አንጋፋ የኦሮሞ የፖለቲካ አመራሮች መታሰራቸው እና ሌሎች ችግሮች የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው ላይ ባለመሳተፍ አድማቸውን እንዲገልጹ እና በኢትዮጵያ በህዝብ ብዛት ትልቁ በሆነው በዚህ ክልል በርካታ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫዎች ላይ አንድ ዕጩ ብቻ እንዲወዳዳር ምክንያት ሆነዋል። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለምርጫ ቅስቀሳ የሚውል ገንዘብን የሚመለከቱ አዲዳስ እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደረገ ቢሆንም የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ከመቻል ጋር በተያያዘ ልዩነቶች መኖራቸው አሁንም ችግር እየፈጠረ ይገኛል እንዲሁም ስልጣን ላይ መሆን የሚያስገኛቸው ጥቅሞች እና የመንግስት ሀብትን መጠቀም ለመሪው ፓርቲ ከመጠን በላይ ጠቅሞታል። በመሆኑም የምርጫ ቅስቀሳው በአንጻሩ መሪው ፓርቲ ጫና ያሳደረበት እና የገነነበት ነበር።

የጸጥታ ችግር መኖሩ ሴቶች እና ሌሎች በተለምዶ የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በምርጫው ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ባላቸው ዕድል ላይ ከመጠን በላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረ ሲሆን ወረርሽኙ ይበልጥ ጫና ያሳደረው በእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ መሆኑ በምርጫው ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ያላቸውን ዕድል የባሰ አጥብቦታል። በመሆኑም ምንም እንኳን ከአንዳንድ ነገሮች አንጻር መሻሻሎች ያሉ ቢሆንም ሴቶች፣ በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሔረሰቦች እንዲሁም የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በአብዛኛው በምርጫው ሂደት ውስጥ ያላቸው አቅም አሁንም እንደተዳከመ ነው። በአንጻሩ የላቀ የመገናኛ ብዙሀን ነጻነት የነበረ ቢሆንም አንዳንድ ከፍተኛ ችግሮች እንደቀጠሉ ነው። በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን ላይ የመንግስት ደጋፊ የሆኑ ድምጾች እንደገነኑ ቀጥለዋል እንዲሁም በፖለቲካው ውስጥ ከሁሉም ወገን ግለሰቦች የሚያሰራጯቸው የሀሰት መረጃዎች መራጮች ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ያላቸውን አቅም አዳክሞታል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሰኔ 14 ምርጫን ከማዘጋጀት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ተግዳሮቶች አጋጥመውታል። በስፋት በተተቹት የ1997፣ 2002 እና 2007 ምርጫዎች ዙሪያ የነበረው የፖለቲካ ጭቆና እና አምባገነን አስተዳደር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን (እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን) አቅም በከፍተኛ ሁኔታ ያዳከመው ሲሆን ይህም ወደ አሁኑ ምርጫ በሚገባበት ወቅት ሊስተካከሉ የሚገቡ ድክመቶችን ፈጥሯል። የችግሮቹ ትልቀት እና ስፋት፣ የቦርዱ አባላት አዲስ መሆን እና በምርጫ ዙሪያ አነስተኛ ልምድ ያላቸው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች ተቋሙን መቀላቀላቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለማድረግ ለሞከራቸው ከፍተኛ ማሻሻያዎች እንቅፋት ሆነዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ንዑስ-ብሔራዊ መዋቅሮች ያላቸው አቅም ተመጣጣኝ አይደለም እንዲሁም ስለ ገለልተኝነታቸው የተነሱ ስጋቶችም ነበሩ። በዚህ አውድ ውስጥ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ግልጽነቱን እና ምላሽ ሰጪነቱን ጨምሮ ያደረጋቸው ማሻሻያዎች ቢኖሩም አንዳንድ ወሳኝ ወቅቶች ላይ ያሳየው ግልጽነት በቂ አልነበረም እንዲሁም በመራጮች ምዝገባ ወቅት፣ በዕጩዎች ምዝገባ ወቅት እና በምርጫው ዕለት ለሚኖረው ድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ በሚዘጋጅበት ወቅት ከፍተኛ የአሠራር ተግዳሮቶች አጋጥመውት ነበር፤ ይህም ምርጫው እንደገና ወደ ሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ ምክንያት ሆኗል።

ዜጎች እና ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች እንደገለጹት ከሆነ ሰኔ 14 የነበረው የድምጽ አሰጣጥ እና የቆጠራ ሂደት በአብዛኛው ሰላማዊ ነበር እንዲሁም የምርጫ ኃላፊዎች በአጠቃላይ ሥነ-ሥርዓቱን ተከትለዋል። በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች አካባቢ ግጭቶች እንደነበሩ እና የንዳንድ የምርጫ ማቴሪያሎች እጥረት እንደነበረ የሚገልጹ አልፎ አልፎ የወጡ ይፋዊ ዘገባዎች የነበሩ ሲሆን ይህም በንዳንድ አጋጣሚዎች የምርጫ ጣቢያዎች እንዳይከፈቱ ምክንያት ሆኗል። ረጅም ሰልፎች የነበሩ በመሆኑ የተነሳ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ድምጽ የመስጠት ሂደቱን ለተጨማሪ ሦስት ሠዓታት አራዝሟል፤ ይህም ባለድርሻ አካላት በስፋት የደገፉት እርምጃ ነበር። ሐምሌ 3 ቀን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የ425 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልሎችን ውጤት ይፋ ያደረገ ሲሆን በዚህም ስልጣን ላይ ያለው ብልጽግና ፓርቲ 410 ወንበሮችን ማሸነፉ እና በአብዛኛዎቹ ክልሎች ከተመዘገበው ውስጥ ከ90 በመቶ በላይ መራጭ ድምጽ መስጠቱ ተገልጿል። ከ201 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልሎች ጋር በተያያዘ ቅሬታዎች የቀረቡ ሲሆን የዘጠኝ ምርጫ ክልሎች ውጤት ተሰርዟል።

ሰኔ 23 ለአውሎ ሚዲያ ማዕከል እና የዩቲዩብ ብሮድካስተር ለሆነው ለኢትዮ ፎረም የሚሰሩ ጋዜጠኞች በቁጥጥር ሥር ውለዋል።[10] በተጨማሪም በኢንተርኔት የሚሰራጭ ጋዜጣ የሆነው አዲስ ስታንዳርድ ከሐምሌ 8 እስከ 14 ድረስ ለጊዜው ህትመት እንዲያቆም በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሀን ባለስልጣን ተገዷል።[11] ምንም እንኳን ከምርጫው ጋር የተያያዘ ባይሆንም ከሰኔ 14 አንስቶ ጳጉሜ 1 ድምጽ እስከሚሰጥ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከመገናኛ ብዙሀን ነጻነት ጋር በተያያዘ ስጋቶች እንዳሉባቸው አስተያየት ሰጪዎች ገልጸዋል። ሰኔ 14 የተደረገውን ድምጽ የመስጠት ሂደት ተከትሎ በትግራይ የነበረው ግጭት ከቀጠለ በኋላ የተኩስ አቁም ተደርጓል፤ ይህም በዚሁ ከቀጠለ እና ቀውሱን የመፍታቱን ጉዳይ ወደፊት ማራመድ ከተቻለ ጳጉሜ 1 ከሚደረገው ምርጫ በፊት ለሚኖረው ምህዳር የሚጠቅም ውጤት ሊኖረው ይችላል።

ኢትዮጵያ ምርጫው በተላለፈባቸው 82 የምርጫ ክልሎች ምርጫ የምታደርግበት ጳጉሜ 1 ቀን እየደረሰ ነው።[12] ጳጉሜ 1 የሚደረገውን ምርጫ የተሻለ ለማድረግ ባለችው ውስን ጊዜ ውስጥ መወሰድ የሚችሉ ወሳኝ እርምጃዎች አሉ። በመሆኑም ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት ኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው የዚህ ሪፖርት መጨረሻ ላይ ከቀረቡት 39 ምክረ-ሀሳቦች በተጨማሪ የሚከተሉትን 13 ምክረ-ሀሳቦች ያቀርባል፦

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የዕጩዎች ዝርዝሮችን፣ የመራጮች ምዝገባ መረጃን፣ የድምጽ መስጫ ስፍራዎችን እና ሌሎች አግባብ የሆኑ መረጃዎችን ጨምሮ ጊዜው የተላለፈውን ምርጫ በተመለከተ ለፖለቲካ ፓርቲዎች እና ለሲቪል ማህበረሰብ ደርጅቶች ዝርዝር መረጃዎችን ጊዜውን ጠብቆ በመስጠት ግልጽነቱን ይበልጥ ማጠናከር አለበት፤
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከተመዘገቡ መራጮች ብዛት ጋር በተያያዘ ምዝገባው ከመጠን በላይ እና ከመጠን በታች ነው ለሚሉ ስጋቶች በገለልተኛ ባለሞያ እንደሚደረግ ግምገማ ባሉ መንገዶች በይፋ መፍትሄ መስጠት እና የመራጮች ምዝገባ ሂደቱን ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ከዚህ ቀደም ለመመዝገብ ዕድሉን ላላገኙ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ክፍት በማድረግ ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጋር በተያያዘ የሚሠሩ ሥራዎችን ይበልጥ ማጠናከር አለበት፤
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ ጣቢያዎች እና የምርጫ ቆጠራ በሚከናወንባቸው ስፍራዎች የሚገኙ የፓርቲ ወኪሎች (እንዲሁም ቢቻል ታዛቢዎች) የሕጋዊ ውጤት ማሳወቂያ ቅጹ የተረጋገጠ ቅጂ እንዲሰጣቸው ለማድረግ የሚሠሩ ሥራዎችን ሊያጠናክር ይገባል፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ ጣቢያ የተከፋፈሉ ውጤቶችን በጊዜው ማቅረብ አለበት፤

10 የጋዜጠኞች መብት ጥበቃ ኮሚቴ (Committee to Protect Journalists) ያወጣውን ጥቆማ ይመልከቱ።

11 የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለስልጣንን እገዳ በተመለከተ አዲስ ስታንዳርድ ያወጣውን መግለጫ ይመልከቱ።

12 ትግራይ ላይ በኋላ ላይ ምርጫ የሚደረግበት ቀን አልተወሰነም።

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች፣ አጣሪ ኮሚቴዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ መድረኮች እና ፍርድ ቤቶች በምርጫ ሂደት በሚነሱ የተለያዩ የቅሬታ ዓይነቶች ላይ የየራሳቸውን የስልጣን ወሰን እና ቅሬታ የሚሰሙበትን ሥነ-ሥርዓት ግልጽ ከማድረግ እና ለህዝብ ይፋ ከማድረግ ጎን ለጎን እንዲህ ያሉትን ቅሬታዎች ውጤታማ በሆነ መልኩ በጊዜው ለመፍታት ያላቸውን አቅም መገንባት አለባቸው፤
- የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የመንግስት ባለስልጣናት እና ሌሎች የምርጫ ተዋንያን በሙሉ ጠብ አጫሪ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ከማድረግ ወይም በግጭት፣ በማስፈራራት እና በጥላቻ ንግግር ውስጥ ከመሳተፍ መቆጠብ አለባቸው፤ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የመንግስት ባለስልጣናት እንዲህ ያሉትን እርምጃዎች ላለመውሰድ ቃል መግባት እና ሰላማዊ የምርጫ ውድድር እንዲኖር ጥሪ ማስተላለፍ አለባቸው፤
- የፖለቲካ ፓርቲዎች ይበልጥ ሀሳብን መሰረት ያደረጉ የምርጫ ቅስቀሳዎችን ማዘጋጀት እና መራጮችን ቅድሚያ በሚሰጧቸው ፍላጎቶቻቸው ዙሪያ ማነጋገር አለባቸው፤
- የፌዴራል እና የክልል የጸጥታ ኃይሎች በዕጩነት፣ በመራጭነት፣ በምርጫ ኃላፊነት እና በታዛቢነት የሚሳተፉ ሴቶችን ጨምሮ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት አስተማማኝ የሆነ አካባቢን ለመፍጠር የሚሰሩትን ሥራ አጠናክረው መቀጠል አለባቸው፤
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሴቶችን፣ የወጣቶችን፣ በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሔረሰቦችን፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችን እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ተሳትፎ ለማጎልበት ዝርዝር እርምጃዎችን ለይተው ማስቀመጥ እና መውሰድ አለባቸው፤
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ በቅርቡ የተቋቋመው የኢትዮጲያ መገናኛ ብዙሀን ባለስልጣን፣ የጋዜጠኞች እና የመገናኛ ብዙሀን ማህበራት እና የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የመገናኛ ብዙሀን እና የማህበራዊ ሚዲያ ክትትሎችን በማድረግ፣ ለሀሰተኛ መረጃዎች መፍትሔ በመስጠት እና ሚዛናዊ የመገናኛ ብዙሀን ሽፋን መኖሩን፣ የጋዜጠኞች ደህንነት መጠበቁን እና መረጃ ተደራሽ መሆኑን በማረጋገጥ በምርጫ አውድ ውስጥ የመረጃ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ይበልጥ ጥረት ማድረግ አለባቸው፤
- የፌዴራል እና የክልል መንግስታት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር ያላቸውን ቅንጅታዊ አሠራር ማጠናከር እና አስፈላጊውን ድጋፍ እና ሀብት ማቅረብ አለባቸው፤
- ከመራጮች ስልጠና እና መራጮችን ከማነሳሳት ጋር በተያያዘ የሚሰሩ ሥራዎች መቀጠል እና በተለይም ደግሞ በምርጫው ውስጥ በስፋት መሳተፋቸውን ለማረጋገጥ ከትላልቅ ከተሞች ውጭ ያሉ አካባቢዎችን ጨምሮ የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ዒላማ ማድረግ አለባቸው፤
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና የፌዴራል እና የክልል መንግስታት በምርጫው አውድ ውስጥ የህብረተሰቡን ጤና ለማስፋት እና የኮቪድ-19 ወረርሽኝ የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ለመቀነስ የሚሰሯቸውን ሥራዎች ማጠናከር አለባቸው፤ እና
- የዜጋ ምርጫ ታዛቢዎች ሁሉንም የምርጫ ሂደቱን ገጽታዎች ያለገደብ እንዲታዘቡ እና ግኝቶቻቸውን እንዲያጋሩ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ያለ ቢሆንም ይህ መብት በተግባር ጥበቃ የሚደረግለት መሆኑን ለማረጋገጥ ይበልጥ ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል።

ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ያለው የጸጥታ ከባቢ ሁኔታ በፍተኛ ሁኔታ አሳሳቢ እና ከዴሞክራሲ አንጻር ያለው አካሄድ አጠራጣሪ ቢሆንም ዜጎች ከዴሞክራሲ ጋር በተያያዘ የመጡት ለውጦች ስር እንዲሰዱ ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ ነው። በአፍሪካ የዴሞክራሲ፣ የምርጫ እና የአስተዳደር ቻርተር (African Charter on Democracy, Elections and Governance) ውስጥ እንደተገለጸው ሁሉም ተዋንያን "የፖለቲካ እና ማህበራዊ ውይይትን እንዲሁም በፖለቲካ አመራሮች እና በህዝቡ መካከል ያለውን መተማመን እና ግልጽነት በማረጋገጥ እና ጠብቆ በማቆየት ዴሞክራሲን እና ሰላምን ለማጠናከር" እርምጃዎችን እንዲወስዱ ያስፈልጋል።[13] አካታች የሆነ ባህልን ለመገንባት፣ ትርጉም ያላቸው ምርጫዎችን ለወደፊቱ ለማድረግ እና ከጳጉሜ 1 በኋላ ወደፊት ለመራመድ የሚያስችል መሰረት ለመጣል የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች፣ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ሲቪል ማህበራት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሰላማዊ፣ የበለጸገች እና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት የሚለውን የጋራ ራዕይ ለማሳካት ተግተው መሥራት ይኖርባቸዋል።

# የፖለቲካው ምህዳር

ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. የተደረገው ምርጫ ኢትዮጵያ ወደ ሲቪል አመራር ከተመለሰች ወዲህ ያደረገችው ስድስተኛው ምርጫ ነበር። ሆኖም ግን ከዚህ ቀደም የነበሩት የምርጫ ሂደቶች በስፋት የታዩት መሰረታዊ ግድፈት የነበረባቸው ተደርገው በመሆኑ ሀገሪቱ ተአማኒነት ካለው ምርጫ ጋር በተያያ ያላት ተሞክሮ በአንጻሩ ውስን ነው። ዶ/ር አብይ አህመድ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆኑ በኋላ ከ2010 ዓ.ም. ጀምሮ የተደረጉት ከፍተኛ ማሻሻያዎች መጀመሪያ ላይ የፖለቲካ ምህዳሩን በማስፋት የላቁ ነጻነቶችን የሰጡ እና ተአማኒነት ያለው ምርጫ ይደረጋል የሚል አዲስ ተስፋን የፈጠሩ ነበሩ። ከፍተኛ አክብሮት የሚሰጣቸው ግለሰቦች በርካታ ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ መሾማቸው እና ተመርጠው መቀመጣቸው እና ከእነሱ ውስጥም አብዛኞቻቸው ሴቶች መሆናቸው በህዝቡ ዘንድ የመተማመን ስሜት ይበልጥ እንዲጨምር ያደረገ ነበር። ነገር ግን በቀደመው ጊዜ በሀገሪቱ የብሔር ፌዴራሊዝም ሥርዓት ይተዳደሩ የነበሩ ስር የሰደዱ እና ለረጅም ጊዜ ታፍነው የቆዩ የብሔር ውጥረቶች እንዲሁም ሚዛናዊ ያልሆኑ የኃይል ክፍፍሎች እና አጠቃቀሞችም እንዲሁ ብቅ ብለዋል። በመሆኑም ምርጫው የተከናወነው መጠነ ሰፊ የጸጥታ ችግር፣ የፖለቲካ ጭቆና እና ግልጽ ግጭት የተስተዋሉባቸው አጋጣሚዎች እንዲሁም በክልሎች ከፍተኛ ውጥረቶች በነበሩበት አውድ ውስጥ ነበር። እነዚህ ችግሮች ተአማኒነት ያለው ምርጫ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ ተግዳሮቶችን ፈጥረዋል እንዲሁም ከመራጮች ተሳትፎ እና በተለይም ደግሞ ከሴቶች፣ ከወጣቶች፣ ከአካል ጉዳተኞች፣ ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ከሌሎች የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ጋር በተያያዘ የነበሩትን እንቅፋቶች ይበልጥ አብሰዋቸዋል።

ብሔርን መሠረት ባደረገው የፌዴራል ሥርዓት ውስጥ በብሔር እና በክልል የተዋቀሩ ፓርቲዎችን በስሩ ያቀፈ አንድ ጥምረት ለሦስት አሥርት አመታት ገኖ መቆየቱን ተከትሎ በስልጣን ላይ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ)በ2011 ዓ.ም. ከፈረሰ ወዲህ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ስታካሂድ ይህ የመጀመሪያዋ ነው። ኢህአዴግ የትግራይ ህዝብ ነጻነት ግንባርን (ትህነግ)፣ የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄን (ብአዴን፣ በኋላ ላይ የአማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የሆነውን)፣ የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅትን (ኦህዴድ) እና የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄን ጨምሮ ከአራት ፓርቲዎች የተዋቀረ ጥምረት ነበር። ኢትዮጵያ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር እያለች ሙስና እና የመሰረታዊ ነጻነቶች ያለመከበር የፖለቲካ መልክአ ምድሯ መገለጫ ነበሩ። ስልጣን ላይ የነበረው አምባገነን ፓርቲ

13 የአፍሪካ የዴሞክራሲ፣ የምርጫ እና የአስተዳደር ቻርተር አንቀጽ 13

እና በብሔር የተከለሉ ክልሎችን መሠረት በማድረግ በክልል ደረጃ የፖለቲካ ስልጣንን ለማከፋፈል ጥቅም ላይ የዋለው የብሔር ፌዴራሊዝም ሥርዓት ለረጅም ጊዜ የቆዩ የብሔር እና የፖለቲካ ውጥረቶች እንዲያመረቅዙ ምክንያት ሆነዋል። እነዚህ ሁኔታዎች የፖለቲካ ተሳትፎን እና ውድድርን እንዲሁም መገናኛ ብዙሀን እና ሲቪል ማህበራት የሚጫወቱትን ሚና አሽመድምደዋል።

በመጋቢት ወር 2010 ዓ.ም. ወደ ስልጣን ከመጡ ጀምሮ በአብይ አህመድ የተመራው መንግስት ዜጎች ሀሳብን የመግለጽ፣ የመደራጀት እና የመሰብሰብ መሰረታዊ ነጻነቶቻቸውን እንዲጠቀሙ የፖለቲካ እና የሲቪል ምህዳሩን የማስፋት አላማ ያላቸው በርካታ አዎንታዊ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ከማድረግ ጎን ለጎን በፌዴራል መንግስት እና በክልሎች መካከል ያለውን ግንኙነት አዲስ ቅርጽ ለማስያዝ ጥረቶችን አድርጓል። ማህበራዊ አገልግሎቶችን ብቻ እንዲሰጡ ተደርገው የነበሩ በርካታ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ዕድገት ውስጥ መብት ያላቸው ባለድርሻ አካላት ሆነው በምርጫዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ተፈቅዶላቸዋል። ይህንኑ ለማሳካት ሲባልም ጠቅላይ ፍርድ ቤትን፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንን (ኢሰመኮ) እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ጨምሮ በህዝብ ተቋማት ውስጥ ቁልፍ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ በርካታ የሰብአዊ መብት አክቲቪስቶች ተሹመዋል።

ማሻሻያዎችን ከማድረግ አጀንዳው ትግበራ ጎን ለጎን አንዳንድ የፖለቲካ እስረኞች የተፈቱ ሲሆን ይህም በስደት ላይ የነበሩ አክቲቪስቶች እና ተቃዋሚዎች ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ ለብሔራዊ ምርጫው ራሳቸውን እንዲያደራጁ መድረኩን ፈጥሯል። አንዳንድ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ወደ ሀገራቸው መመለሳቸው እና ከእስር መፈታታቸው በብሔራዊ እና በክልል ደረጃዎች አዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቅ እንዲሉ ያስቻለ እንዲሁም ሰፋ ባለ መልኩ ስንመለከተው ውድድር ያለበት ምርጫ እንደሚኖር እና ኢትዮጵያ ለወደፊቱ ስለሚኖረው ዴሞክራሲ ተስፋን የሰጠ ነበር።

ሆኖም ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያስጀመሯቸው የፖለቲካ ማሻሻያዎች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አልተደረጉም እንዲሁም ከፌዴራል አንስቶ እስከ ክልል እና አካባቢ ደረጃዎች ድረስ አልተዳረሱም የሚሉ ስጋቶች እንደቀጠሉ ነው። ተቃዋሚ ፓርቲዎች አሁንም ደካማ ናቸው እንዲሁም ራሳቸውን ከማቋቋም ጋር በተያያዘ ተግደሮቶች አሉባቸው፤ በተጨማሪም ያላቸው የገንዘብ እና የሰው ሀብት ውስን ነው። በስልጣን ላይ ጠንካራ ፓርቲ መኖሩ እና እንደ አዲስ የተቋቋሙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መኖራቸው የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳው ሚዛኑ እንደተዛባ እንዲጥል የሚያደርግ ነው።

በስልጣን ላይ የነበረውን ጥምረት መልሶ ለማወቀር የተደረጉ ጥረቶች በተለይም ደግሞ ከትግራይ እና ከዚህ ቀደም ኢህአዴግን ተቆጣጥሮ ከነበረው እና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ገኖ ከቆየው ከትህነግ ከፍተኛ ተቃውሞን አስነስተው ነበር። ለውጦቹ የኢዮጵያን ብሔራዊ አንድነት ራዕይን በሚያቀነቅኑ የለውጡ ደጋፊዎች እና የኢትዮጵያን የብሄር ፌዴራሊዝም ሥርዓት በሚደግፉ ወገኖች መካከል ግጭቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆነዋል። ኢህአዴግን መልሶ የማዋቀሩ ስራ በሂደት ብልጽግና ፓርቲ የተሰኘ አዲስ ፓርቲን ወደመፍጠር ያመራ ቢሆንም ትህነግ ለመቀላቀል ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል።

ምንም እንኳን መጀመሪያ ላይ ብሔራዊ ምርጫው ይደረጋል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው ለመጨረሻ ጊዜ ግንቦት 16 ቀን 2007 ዓ.ም. ከተደረገው ምርጫ በኋላ አምስት ዓመት ቆይቶ ግንቦት ወር 2012 ዓ.ም. ላይ የነበረ ቢሆንም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫው በነሀሴ ወር እንደሚደረግ በይፋ አስታውቆ ነበር። ከዚያም በሚቀጥለው ወር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ የተነሳ ምርጫው እንደተራዘመ ገልጿል። በኋላ ላይ ምርጫው ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም. እንዲደረግ ቀን ተቆርጦለት የነበረ ቢሆንም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከሎጂስቲክስ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችን በመጥቀስ ወደ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. ተላልፏል።

የትህነግ አመራር የምርጫ የጊዜ ሰሌዳው መራዘሙን እና የ2012 ብሔራዊ ምርጫ ላልተወሰነ ጊዜ መተላለፉን ተቃውሟል።[14] ትግራይ በጳጉሜ ወር 2012 ዓ.ም. በተናጠል የክልሉን ምርጫ ያደረገች እና ይህም የነበሩትን የፖለቲካ ያለመስማማቶች ያባባሰ ሲሆን በመጨረሻም በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሊታወጅ ችሏል። ጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም. ፌዴራል መንግስት ሰራዊቱን ወደ ትግራይ በማሰማራት "ሕግ እና ሥርዓትን የማስከበር ወታደራዊ ተልእኮ" መጀመሩን ገልጿል። ምንም እንኳን መንግስት ወታደራዊ ምላሹ ተጀምሮ ብዙም ሳይቆይ መጠናቀቁን ያወጀ ቢሆንም ያንን ተከትሎ የተፈጠረው ግጭት ያልቀቋረጠ እና አሁንም የቀጠለ ሲሆን በግምት ከአንድ ሚሊዮን በላይ የትግራይ ተወላጆች በሀገር ውስጥ እንዲፈናቀሉ እና በአካባቢው ያለመረጋጋት ስጋት እንዲኖር ምክንያት ሆኗል። የኤርትራ ሰራዊት የፌዴራሉን መንግስት በመደገፍ መሳተፉ እና ለረጅም ጊዜ ከቆየ የድንበር ያለመግባባት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ እና በሱዳን ሰራዊት መካከል ግጭቶች መከሰታቸው ሁኔታውን ይበልጥ አባብሶታል። ኢሰመኮ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በሲቪሊያኖች ላይ የተፈጸሙ ግድያዎችን፣ የወሲብ ጥቃቶችን እና ምግብን እንደ መሳሪያ መጠቀምን ጨምሮ በግጭቱ ውስጥ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች መፈጸማቸውን የሚዘረዝሩ ሪፖርቶችን አውጥተዋል፤ እንዲሁም የአፍሪካ የሰብአዊ እና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን (African Commission on Human and Peoples' Rights) ትግራይን የሚመለከት አጣሪ ኮሚሽን አቋቁሟል።[15] እነዚህ ክስተቶች በአጠቃላይ የምርጫው ምህዳር ውስጥ የሚስተጋቡት ውጥረቶች እንዲጨምሩ አድርገዋል።

በቀድሞ አጠራሩ ኢህአዴግ ተብሎ ይጠራ በነበረው ግንባር ውስጥ በተፈጠሩ የኃይል ሽኩቻዎች የተነሳ ሰፋ ባለ መልኩ ስንመለከተው በኢትዮጵያ የብሔር ፌዴራሊዝም ሥርዓት ውስጥ ያሉ ግንኙነቶች ሻክረዋል። ሽኩቻዎቹ በተለያዩ የኦሮሞ ቡድኖች መካከል እንዲሁም በብሔሮች እና በተለይም ደግሞ በአማራ እና በትግራይ ክልል አመራሮች መካከል ውጥረት እንዲጨምር ምክንያት ሆነዋል። የመሬት ይገባኛል የትጥቅ ግጭትን፣ ህዝባዊ ተቃውሞዎችን እንዲሁም በርካታ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው ላይ አድማ ማድረጋቸውን እና ከምርጫው ራሳቸውን ማግለላቸውን ጨምሮ ውጥረቶች በመላው ኢትዮጵያ በተለያዩ መንገዶች ተስተውለዋል። የተቃዋሚ አመራሮች እና ደጋፊዎቻቸው ከምርጫው አስቀድሞ በቁጥጥር ስር መዋላቸው እና መታሰራቸው የጸጥታ ችግሩን አባብሶታል እንዲሁም የፖለቲካ ምህዳሩን አጥብቦታል።[16]

በመጨረሻም እስከ ጳጉሜ 1 ከሚዘገዩት በርካታ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫዎች እና ቀን ካልተቆረጠለት የትግራይ ምርጫ በስተቀር ምርጫው ሰኔ 14 ቀን ሊደረግ ችሏል።

---

14 ምርጫው የተራዘመበትን እና የተላለፈበትን ምክንያቶች እና ቅደም ተከተሎች እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች በተመለከተ በዚህ ሪፖርት የኋለኛው ክፍል ውስጥ ተሸፍኗል፡፡

15 የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የማህበራዊ ሚዲያ ገጽ ላይ የተለጠፉትን ሪፖርቶች ይመልከቱ፤ በተጨማሪም አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ የካቲት 19 ቀን 2013 ዓ.ም.፤ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ የካቲት 26 ቀን 2013 ዓ.ም.፤ በኢትዮጵያ የትግራይ ጦርነት፡- ህይወቶችን እየቀጠፈ ያለው አደገኛ ፍጥጫ የተሰኘው የኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ አጭር መግለጫ 171፤ መጋቢት 24 ቀን 2013 ዓ.ም.።

16 በእስር ላይ ከነበሩ ወይም ከሆኑ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራሮች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡- እስክንድር ነጋ፣ ስንታየሁ ቸኮል እና አስቴር ስዩም ከባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ፤ በቀለ ገርባ፣ ጃዋር መሀመድ፣ ደጀኔ ታፋ እና ቆርሳ ደቻሳ ከኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ (ኦፌኮ)፤ እና በለጠ ኦርጌሳ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)። በአዲስ መልኩ ምዝገባው የተሰረዘው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲው (ኢዴፓ) ልደቱ ያሌው ከእስር ተፈትተው ከምርጫው አስቀድመው ለህክምና ከሀገር ወጥተዋል። የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ እና ዴሞክራሲ ፓርቲን (ኢዜማ)፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባርን (ኦብነግ) እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ንቅናቄን (ኢብን) ጨምሮ የሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት ምርጫው በመቃረብ ላይ እያለ ታስረው የነበረ ቢሆንም በዋስ ተለቀዋል።

# ትንተና

## የሕግ ማዕቀፍ

በኢትዮጵያ ምርጫ የሚተዳደርባቸው ዋነኞቹ የሕግ ሰነዶች የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት (1987)፣ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ (የምርጫ አዋጅ) እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ (ሁለቱም በ2011 የወጡ) ናቸው። እ.ኤ.አ. በ2018 ዓ.ም. በሕግ እና ፍትህ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ የተጀመረውን የሕግ ማዕቀፉን በከፍተኛ ሁኔታ የማሻሻል ስራ ተከትሎ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዲስ የምርጫ፣ የሲቪል ማህበራት እና የመገናኛ ብዙሀን ሕጎችን አጽድቋል። እነዚህ አዳዲስ ሕጎች ከምርጫ ጋር በተያያዘ ያለውን የሕግ ማዕቀፍ አዎንታዊ በሆነ መልኩ የቀየሩት ሲሆን የሀገር ውስጥ ምርጫዎችን በተመለከተ የተቀመጡ ቁልፍ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ደረጃዎችን ለማሟላት ይበልጥ የተጠጋ እንዲሆን አድርገውታል። ሆኖም ግን የምርጫ ሕጉ አተገባበር ወጥነት ያለው አልነበረም እንዲሁም በተጻፈው እና በተግባር በሚደረገው መካከል በርካታ ክፍተቶች ተስተውለዋል።

ዕጩ ከመሆን ጋር በተያያዘ የተቀመጡ ገደቦች፤ ማለትም የቋንቋ መስፈርቶች እና በአንድ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልል አሥራ ሁለት ዕጩዎች የሚለው ምክንያታዊ ያልሆነ ገደብ መነሳታቸው የፖለቲካ መብቶች ጥበቃን አጠናክሯል። ፓርቲዎች ሴቶችን እና የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችን ዕጩ እንዲያደርጉ እንዲሁም የአስተዳደር መዋቅራቸው ውስጥ ሴቶችን እንዲያካትቱ የሚያበረታቱ አዲስ የገንዘብ ማትጊያዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና የህግ ታራሚዎች ድምጽ የመስጠት መብት እንዲሁም የህግ ታራሚዎች በምርጫ የመወዳደር መብት በሕጉ ውስጥ በግልጽ ዕውቅና ተሰጥቶታል። በተጨማሪም የመንግስት አስተዳደርን ለፓርቲ ወገንተኛ ከሆነ ፖለቲካ ለማራቅ ሲባል የመንግስት ተቋማት ውስጥ በመማር ማስተማር ላይ የተሰማሩ ባለሞያዎችን ጨምሮ የመንግስት ሠራተኞች በምርጫው ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃድ እንዲወስዱ የሚጠይቅ ደንብ ተቀምጧል። የምርጫ ክልሎች በትልቀት ተመጣጣኝ እንዲሆኑ እና ከ15 በመቶ የበለጠ ልዩነት በመካከላቸው እንዳይኖር የሚጠይቅ አዲስ መስፈርትም እንዲሁ ተቀምጧል።

ሆኖም ግን የህግ ታራሚዎች እና ዳያስፖራዎች ድምጽ መስጠታቸውን ጨምሮ አብዛኛዎቹ ድንጋጌዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በርካታ የተለያዩ ማሻሻያዎችን በማስተናገድ ላይ የነበረ በመሆኑ ተግባራዊ አልተደረጉም። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በማረሚያ ቤቶች ዕጩዎችን አልመዘገበም እንዲሁም ሁላቸውም የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ ዕጩዎች የሆኑ አራት ዕጩዎች በዕጩነት እንዲመዘገቡ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ መጀመሪያ ላይ ፈቃደኛ አልነበረም። የምርጫ ክልል ድንበሮች ድምጾች እኩል ክብደት ሊኖራቸው ይገባል የሚለውን መርህ ያላሟሉ ቢሆንም ሊከለሱ ያልቻሉ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከናወነ የህዝብ ቆጠራ ያለመኖሩ ነው። በሕገ መንግቱ ውስጥ በቁጥር አናሳ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የተቀመጡ ልዩ የምርጫ ክልሎች እንደ መደበኛ ወረዳዎች መተዳደራቸው ቀጥሏል እንዲሁም በቁጥር አናሳ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን አቅም ትርጉም ባለው መልኩ ለማጎልበት የተወሰዱ እርምጃዎች የሉም። ሴቶችን እና የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችን እጩ ለሚያደርጉ ፓርቲዎች የተዘጋጁ የገንዘብ ማትጊያዎች ከእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረቡ ዕጩዎች ቁጥር ጉልህ በሆነ መልኩ እንዲጨምር አላደረጉም።

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ ሕግ ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ቦርዱን ይበልጥ ነጻ አድርጎታል እንዲሁም ሹመትን እና ሥነ-ምግባርን የሚመለከቱ አዲስ ድንጋጌዎችን አካቷል፤ በተጨማሪም የአስተዳደር ጉዳዮች በፍርድ ቤት የሚከለሱበት ስርዓት ያለው መሆኑ ቦርዱን ይበልጥ ተጠያቂነት ያለው አድርጎታል። ሆኖም ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መጨረሻ ላይ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን የተቀበለ ቢሆንም በፍርድ ቤት የተወሰኑበትን ውሳኔዎች ሁል ጊዜም ጊዜውን በጠበቀ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ አክብሯል ለማለት አይቻልም።

የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ምርጫን ከማድረግ ጋር በተያያዘ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፍተኛ ስልጣን ይሰጣል እንዲሁም የጊዜ ማዕቀፎች የሉትም ወይም ደግሞ መለወጥ የሚችሉ ናቸው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ 27 መመሪያዎችን አውጥቷል። እነዚህ መመሪያዎች ዘግይተው ሲጸድቁ በተደጋጋሚ ታይቷል እንዲሁም ሦስት መመሪያዎች ከነጭራሹ አልጸደቁም። ወደ ሌሎች ቋንቋዎች ካለመተርጎማቸውም በላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ድረገጽ ላይ የሚገኙት ሰባት መመሪያዎች ብቻ (በአማርኛ ቋንቋ ብቻ) ነው። የምርጫ አዋጁ ወደ ሌሎቹ አራት የኢትዮጵያ የሥራ ቋንቋዎች የተተረጎመ ቢሆንም የተሰራጨው በኤሌክትሮኒክ መንገድ ብቻ ነው። ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ህዝብ ውስጥ በተወሰነ ደረጃ አማርኛ መናገር የሚችለው 60 በመቶው ብቻ እንደሆነ እ.ኤ.አ. በ2007 ለመጨረሻ ጊዜ የተደረገው ብሔራዊ የህዝብ ቆጠራ ይጠቁማል። ሕጉ ውስን በሆነ መልኩ በሌሎች ቋንቋዎች መታተሙ እና መሰራጨቱ የሕጉ ተደራሽነት በተለይም ደግሞ በቁጥር አናሳ ለሆኑ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች በቂ ያለመሆኑን የሚያሳይ ነው።[17]

---

17 ወርልድ ፖፑሌሽን ሪቪው ባወጣው መረጃ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ 88 ቋንቋዎች ያሉ ሲሆን ከእነሱም ውስጥ 34 በመቶው ህዝብ የሚናገረው ኦሮምኛ፣ 6.25 በመቶው የሚናገረው ሱማሊኛ፣ 6 በመቶው የሚናገረው ትግሪኛ፣ 5 በመቶው የሚናገረው ሲዳምኛ፣ 2.2 በመቶው የሚናገረው ወላይትኛ፣ 2 በመቶው የሚናገረው ጉራጊኛ እና 1.75 በመቶው የሚናገረው አፋርኛ ነው።

# የምርጫ ሥርዓት

ኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት፣ አሥር ክልሎች እና ሁለት “በቻርተር የሚተዳደሩ” ከተሞች[18] ሥልጣን የሚጋሩበት ፌዴራል ሥርዓት ያላት ሀገር ነች። ፌዴራል ፓርላማው ሁለት ምክር ቤቶች ያሉት ሲሆን እነሱም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ናቸው። የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንድ ተወካይ ካላቸው የምርጫ ክልሎች በአብላጫ ድምጽ በቀጥታ በህዝብ የሚመረጡ ተወካዮች ብቻ የሚቀመጡባቸው 547 ወንበሮች አሉት። የፌዴሬሽን ምክር ቤት 153 አባላት ደግሞ የሚመረጡት በአሥሩ የክልል ምክር ቤቶች ነው።[19] የሁለቱም ምክር ቤቶች አባላት የሚያገለግሉት ለአምስት ዓመታት ነው። የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ አብዛኛዎቹን ወንበሮች የሚያሸንፈው የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥምረት መንግስት ይመሰርታል። በርዕሰ መንግስትነት የሚያገለግሉት የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሁም በአብዛኛው በደንቡ መሰረት በርዕሰ ብሔርነት የሚያገለግሉት የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት የሚመረጡት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው።

ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወንበሮች ውስጥ ቢያንስ 20 ወንበሮች (ከ1987 ጀምሮ 22 ወንበሮች) በቁጥር አናሳ ለሆኑ ብሔረሰቦች የተያዙ ናቸው። ከእነሱም ውስጥ 13 የምርጫ ክልሎች ሰኔ 14 ምርጫ አድርገዋል። ነገር ግን ማዕቀፉ የሚመረጡት ተወካዮች የግድ በቁጥር አናሳ የሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች አባላት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ አይደለም። የክልል ምክር ቤቶች እና የከተማ አስተዳደሮች ምርጫ ከአንድ በላይ ተወካይ ባላቸው የምርጫ ክልሎች ህዝቡ በቀጥታ በሚሰጠው ድምጽ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ ጎን ለጎን ይደረጋል። ሁለት ምክር ቤት ካላቸው ከሀረሪ እና ከደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች (ደ/ብ/ብ/ሕ) ክልል በስተቀር ሁሉም የክልል ምክር ቤቶች ያላቸው አንድ ምክር ቤት ነው። ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ የሀረሪ ብሔራዊ ጉባዔ አባላት በመላው ሀገሪቱ በሚኖሩ የሀረሪ ተወላጆች ሲመረጡ ቆይተዋል። የሀረሪ ክልል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከዚህ አሠራር ውጭ ያስተላለፈውን ውሳኔ በመቃወም ተከራክሮ አሸንፏል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሀረሪ ክልል ምክር ቤት አባላት የሚመረጡት በመላው ሀገሪቱ በሚኖሩ የሀረሪ ተወላጆች ነው በማለት ወስኗል።[20] ፍርድ ቤቱ ስልጣን እንደሌለው በመወሰን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሕገ መንግስቱን መሠረት በማድረግ ባቀረባቸው ተቃውሞዎች ላይ ውሳኔ አልሰጠም። ለአንድ በቁጥር አናሳ የሆነ ማህበረሰብ ብቻ በመላው ሀገሪቱ የሚኖሩ አባላቱ እንዲመርጡ መፍቀድ ዕኩል ድምጽ የመስጠት መብትን በተመለከተ ጥያቄዎችን ያስነሳል።

# የምርጫ አስተዳደር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማንኛውንም ምርጫ እና ህዝበ ውሳኔ በሕገ መንግስቱ እና በምርጫ ሕጉ መሠረት ከወገንተኝነት ነጻ በሆነ መልኩ ማስፈጸምን፣ የመራጮች ስልጠና ለሚሰጡ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ዕውቅና መስጠትን እና መቆጣጠርን እና የፖለቲካ ፓርቲዎችን መመዝገብን ጨምሮ የተለያዩ ሥልጣናት እና ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል። በህዳር ወር 2011 ዓ.ም. የቀድሞ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር እና ዳኛ የነበሩት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሊቀ መንበር ተደርገው ተሹመዋል። በፖለቲካው ውስጥ በሁሉም ወገን ያሉ የፓርቲ አመራሮች፣ ሲቪክ አክቲቪስቶች፣ በመማር ማስተማር ላይ ያሉ ምሁራን እና የመገናኛ ብዙሀን ባለሞያዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአዲሷ ሊቀ መንበር ሥር ነጻ እንደሚሆን በአጽንኦት የገለጹ ከመሆኑም በላይ የእሳቸውን ብቻ ሳይሆን የሌሎቹንም ኮሚሽነሮች ጭምር ታማኝነት አድንቀዋል፤ ይህም ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የታየው በምክክር የሚያምን እና ከምርጫ ባለድርሻ አካላት ጋር የመስራት ፍላጎት ያለው ተደርጎ ነበር። ይህም ከዚህ ቀደም የነበረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለፓርቲ ወገንተኛ ተደርጎ ይታይ የነበረ በመሆኑ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

ሆኖም ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስላለው የቴክኒክ አቅም የጊዜ ሰሌዳዎችን ማክበር እና በሕግ የተሰጡትን ኃላፊነቶች መወጣት ስለመቻሉ በቅድመ-ምርጫ ወቅት የተነሱ ስጋቶች ነበሩ። በአዲስ መልኩ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫን የማስተዳደር ልምድ በከፍተኛ ሁኔታ ያንሰው ነበር እንዲሁም አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አአካላት ስለ ግልጽነቱ እና የምርጫ መረጃዎችን በጊዜው መስጠት ስለመቻሉ ጥያቄዎችን አንስተው ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከዚህ ቀደም ምርጫን የማስተዳደር ልምድ የሌላቸው እና በዚህም የተነሳ ብዙ ስልጠና የሚያስፈልጋቸው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አዲስ ሠራተኞችን መመልመል ያስፈልገው ነበር፤ ከዚህ ጎን ለጎንም ብሔራዊ ምርጫ ለማከናወን እና ከፍተኛ የምርጫ ማሻሻያዎችን የማድረግ ኃላፊነቶችን ተቀብሏል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በፌዴራል ደረጃ ከፍተኛ የህዝብ አመኔታ አለው። ቦርዱ የንዑስ-ብሔራዊ መዋቅሮቹን ምን ያህል ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ይችላል የሚለውን ጨምሮ በክልል እና በአካባቢ ደረጃ ያሉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ኃላፊዎች ያላቸው የተባባሪነት መጠን የተለያየ ከመሆኑ እንዲሁም ከአድሎ ነጻ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ ስጋቶች እንዳሏቸው ፓርቲዎች ገልጸዋል።

በ2010 ዓ.ም. ተግባራዊ መደረግ የጀመሩት አዳዲስ ማሻሻያዎች አንደኛው አካል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አባላት በሚሾሙበት ሥነ-ሥርዓት ላይ የተደረገው ለውጥ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የሚሾሙት ለህዝብ የሚተላለፍ ዕጩዎችን የማቀረብ ጥሪን፣ በአስመራጭ ኮሚቴ የሚደረግ የማጣራት ሂደትን እና በፓርላማ ማስጸደቅን ጨምሮ ግልጽ በሆነ ሂደት ማካኝነት ነው። ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቦርድ ሹመቶች የሚደረጉት ከሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር ምክክር ሳይደረግባቸው ነበር። አሁን ያለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አባላት ግን ከቦርዱ ሊቀ መንበር ከብርቱካን ውጭ የተሾሙት በአዲሱ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ከመሆኑም በላይ ሹመቶቹ ሲቪል ማህበራትን፣ የትምህርት እና የሕግ ዘርፎችን ጨምሮ በርካታ የተለያዩ ዘርፎችን የሚያንጸባርቁ ናቸው። የቦርዱ ሊቀ መንበር ብርቱካን የተሾሙት ሕጉ ከመሻሻሉ በፊት ሲሆን ለኃላፊነት ቦታው ከመመረጣቸው በፊት ሰፊ ምክክር ተደርጎ ነበር። በውጤቱም ሁለት ሴቶችን እና ሦስት ወንዶችን ጨምሮ አምስት አባላት ያሉት ቦርድ የተቋቋመ ሲሆን አባላቱ የተሾሙት ለአምስት ዓመታት እንዲያገለግሉ ነው።

ምርጫው የሚተዳደረው ሦስት ደረጃዎች ባሉት መዋቅር ሲሆን ይህም የክልል ጽ/ቤቶች፣ ከ670 በላይ የምርጫ ክልል ጽ/ቤቶች፣ ከ100 በላይ የዞን ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች እና ወደ 50,000 የሚጠጉ የምርጫ ጣቢያዎች ያሉትን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ያካተተ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መጀመሪያ ላይ ባቀደው የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ  የምርጫ ክልል ጽ/ቤቶችን በመላው ሀገሪቱ ወጥ በሆነ መልኩ ለማቋቋም ሳይችል ቀርቷል። ይህም የምርጫ የጊዜ ሰሌዳውን ከማክበር አንጻር መዘግየቶችን አስከትሏል። ቦርዱ በዋና ሥራ አስፈጻሚዋ እና በምክትላቸው በሚመራ እና አዲስ አበባ በሚገኘው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና መሥሪያ ቤት 229 ሠራተኞች እና በአሥራ አንዱ የክልል ጽ/ቤቶች 127 ሠራተኞች ባሉት ጽ/ቤት የተደገፈ ነው። ነገር ግን ቦርዱ በአጠቃላይ እንዲሁም በተለይ የቦርዱ ሊቀ

18 በቻርተር የሚተዳደሩ ከተሞች በሕገ መንግስት ጥበቃ የሚደረግላቸው ሲሆን በዚህም ከክልሎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሥልጣን አላቸው።

19 “በቻርተር የሚተዳደሩ ከተሞች” በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ውክልና የላቸውም።

20 የሰበር ፋይል ቁ. 207036፣ ግንቦት 19 ቀን 2013 ዓ.ም.። ሕገ መንግስቱን ለመተርጎም ሥልጣን ያለው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሀረሪ ያለው አሠራር ሕገ መንግስታዊ እንደሆነ እና እንዳልሆነ ለመከራከር ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማመልከት ነበረበት።

መንበር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሥራ ሂደት ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና ይጫወታሉ። በህዳር እና በታህሳስ 2013 ቦርዱ የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ እና ስልጠና አከናውኗል። ከምልመላ መስፈርቶቹ ውስጥ የትምህርት ደረጃ፣ ልምድ እና ከወገንተኝነት ነጻ መሆን ተጠቃሽ ናቸው። እንደተገለጸው ከሆነ አብዛኛዎቹ ወጣቶች መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ቢሆኑም አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ግንኙነት ነበራቸው። ቦርዱ የጾታ ተዋጽኦው በተመጣጠነ መልኩ የምርጫ አስፈጻሚዎቹን ለመመልመል ጥረት አድርጓል እንዲሁም ሴቶች ይበልጥ እንዲሳተፉ በሚያስችል መልኩ በመስፈርቶቹ ላይ ማስተካከያዎችን አድርጓል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቦርድ እንደገለጸው ከሆነ የምልመላ ሂደቱ ከታቀደው በላይ ጊዜ ወስዷል፣ ይህም በስልጠና የጊዜ ሰሌዳው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል።

በአጠቃላይ የቅድመ-ምርጫ ዝግጅቱ ወቅት ቦርዱ ከሥራ ሂደት ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶች ያጋጠሙት ሲሆን ይህም እንደ የምርጫ ክልል ጽ/ቤቶችን ማቋቋም፣ የዕጩዎች ምዝገባ፣ የመራጮች ምዝገባ፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ እና ስልጠና እና የምርጫ ካርድ ማሳተም ያሉ የተለያዩ የምርጫ እንቅስቃሴዎች ላይ ተከታታይ መዘግየቶችን አስከትሏል። በታህሳስ ወር 2013 ዓ.ም. ቦርዱ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳውን ያወጣ እና በማህበራዊ ሚዲያ እና በፖለቲካ ፓርቲ ስብሰባዎች ላይ ያስታወቀ ቢሆንም የጊዜ ሰሌዳውን ሙሉ በሙሉ ሊያከብረው አልቻለም እንዲሁም የጊዜ ሰሌዳዎች ሳይጠበቁ በቀሩባቸው ወይም ምርጫው በተላለፈባቸው ጊዜያት በወቅቱ የተሻሻሉትን የጊዜ ሰሌዳዎች በይፋዊ እና ሰፊ ተከታይ ባሉላቸው መንገዶች አማካኝነት ለባለድርሻ አካላት አላጋራም።

## የምርጫው መተላለፍ

ምርጫው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ድምጹን እንዲሰጥ ዕድል የሰጠ አልነበረም እንዲሁም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሚደረገው ምርጫ ውስጥ ወደ አንድ አምስተኛ የሚጠጋው ሰኔ 14 ቀን አልተከናወነም። በትግራይ የተፈጠረው ግጭት፣ የጸጥታ ችግሮች፣ በመራጮች ምዝገባ ወቅት የተፈጠሩ ችግሮች፣ ሕግ ነክ ተግዳሮቶች እና ከሎጂስቲክስ ጋር የተያያዙ ችግሮች ሁሉም ለምርጫው መተላለፍ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ምንም እንኳን መጀመሪያ ላይ ምርጫው በግንቦት ወር 2012 ዓ.ም. ይደረጋል ተብሎ ይጠበቅ የነበረ ቢሆንም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በየካቲት ወር 2012 ዓ.ም. ይፋ ባደረገው የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ምርጫው በነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም. እንደሚከናወን አስታውቋል። ከዚያም በመጋቢት ወር 2012 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኮቪድ-19 የተነሳ የምርጫው የጊዜ ሰሌዳ ላልተወሰነ ጊዜ መራዘሙን እና ነሀሴ 23 ቀን ሊደረግ ታስቦ የነበረው ምርጫ መተላለፉን አስታውቋል። በግንቦት እና በሰኔ ወር 2012 ዓ.ም. ሁለቱ የፓርላማ ምክር ቤቶች ይህን ጥያቄ አጽድቀውታል እንዲሁም ስልጣናቸው በመስከረም ወር ያበቃ የነበረውን የክልል መንግስታት ስልጣን አራዝመዋል። በታህሳስ ወር 2013 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫው ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም. እንደሚደረግ በማስታወቅ አዲስ አበባ እና በድሬ ዳዋ የከተማ ምክር ቤት ምርጫዎች ሰኔ 5 ቀን እንዲደረጉ ቀን ቆርጧል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የትግራይ ክልል በተናጠል ላዘጋጀው የጳጉሜ 2012 ምርጫ ዕውቅና አልሰጠውም እንዲሁም በኋላ ላይ በክልሉ ባለው ግጭት የተነሳ በዚያ ምርጫ ማድረግ እንደማይችል ወስኗል። በመሆኑም በትግራይ በሚገኙት 38 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልሎች እና 152 የክልል ምክር ቤት መቀመጫዎች ምርጫ አይደረግም።

ግንቦት 7 ቀን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከሎጂስቲክስ ጋር በተያያዙ ችግሮች የተነሳ ምርጫው እንደገና እንደሚራዘም ገልጾ ሰኔ 14 ቀን እንዲደረግ ቀን ቆርጧል።[21] በተጨማሪም የሀረሪ እና የሱማሌ ክልሎች ምርጫ እንዲሁም በሌሎች ክልሎች ይደረጉ የነበሩ በርካታ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤት ምርጫዎች የደቡብ-ምዕራብ ኢትዮጵያን ክልል መሆን የሚመለከተውን ህዝበ ውሳኔ ጨምሮ በተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከሚደረገው ምርጫ ጋር ሳይሆን ጳጉሜ 1 እንደሚደረጉ (እና የትግራይ ክልል ምርጫ አሁንም ላልተወሰነ ጊዜ እንደሚተላለፍ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ገልጿል። የሀረሪ ክልል ምርጫ የተላለፈው የክልሉ ምክር ቤት ምርጫ ከሚከናወንበት መንገድ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባቀረበው ይግባኝ የተነሳ ሲሆን የሱማሌ ክልል ምርጫ ደግሞ የዘገየው ከመራጮች ምዝገባ ጋር በተያያዙ ችግሮች የተነሳ ነው። ክልል መሆንን የሚመለከተው ህዝበ ውሳኔ የተላለፈው አንዳንድ ችግር የደረሰባቸው ማህበረሰቦች በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና በክልል ምክር ቤት ምርጫዎች ድምጽ ባለመስጠታቸው ነው። በመረሻም ከ547 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወንበሮች ውስጥ የ436 ወንበሮች[22] እንዲሁም ከ2,504 የክልል እና የከተማ ምክር ቤት ወንበሮች ውስጥ የ1,990 ወንበሮች ምርጫ ሰኔ 14 ቀን ተከናውኗል።

የምርጫው ቀን ላይ ተጨማሪ መዘግየቶች እና ከሎጂስቲክስ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶች ነበሩ። ለምሳሌ በሲዳማ እና በጋምቤላ ክልሎች ውስጥ በሚገኙ በርካታ የምርጫ ጣቢያዎች ምርጫው የተከናወነው ሰኔ 15 ቀን ነበር እንዲሁም በነጌሌ የምርጫ ክልል አንዳንድ ክፍሎች መራጮች ሐምሌ 1 ቀን ተመልሰው በመሄድ ድምጻቸውን ሰጥተዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫውን ውጤት ይፋ ባደረገበት ወቅት በአዲሱ የግጭት አፈታት ሂደት መሠረት የቀረቡ ቅሬታዎችን ተከትሎ ዘጠኝ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫዎች እንደገና እንደሚከናወኑ ገልጿል።[23] በድምሩ በ82 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልሎች ምርጫው ጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም. እንዲደረግ ቀን ተቆርጧል።

21 በተጨማሪም "በቻርተር የሚተዳደሩት" የአዲስ አበባ እና ድሬ ዳዋ ከተሞች የከተማ ምክር ቤቶች ምርጫ በፊት ታቅዶ እንደነበረው ከአንድ ሳምንት በኋላ ሳይሆን በተመሳሳይ ጊዜ ሰኔ 14 የሚከናወኑ መሆኑን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አስታውቋል።

22 ምርጫው ወደ ጳጉሜ 1 ከተላለፈባቸው 37 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልሎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡- አፋር (2 - በምርጫ ካርድ ህትመት የተነሳ)፣ አማራ (6 - በጸጥታ ችግሮች የተነሳ፣ 3 - የተመዘገበ መራጭ ባለመኖሩ፣ 1 - የምርጫ ካርዶች እንደገና በመታተማቸው፣ እና 3 - የምርጫ አስተዳደር ችግሮች)፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ (2 - በጸጥታ ችግሮች የተነነሳ፣ 2 - የተመዘገበ መራጭ ባለመኖሩ፣ እና 2 - የምርጫ አስተዳደር ችግሮች)፣ ሀረሪ (1 - በፍርድ ቤት ክርክር የተነሳ፣ እና 1 - በመራጮች ምዝገባ ምርመራ የተነሳ)፣ ኦሮሚያ (7 - የተመዘገበ መራጭ ባለመኖሩ፣ 1 - የምርጫ አስተዳደር ችግሮች)፣ ሱማሌ (23 - ከመራጮች ምዝገባ ጋር የተያያዙ ግድፈቶች)፣ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል (2 - በፍርድ ቤት ክርክሮች የተነሳ፣ 8 - የምርጫ ካርዶች እንደገና በመታተማቸው፣ 1 - የተመዘገበ መራጭ ባለመኖሩ፣ 1 - የመራጮች ምዝገባ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባለመፈቀዱ፣ እና 5 - በጸጥታ ችግሮች የተነሳ)።

23 በድጋሚ ከሚደረጉት አሥር የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫዎች ውስጥ አንዱ በአፋር፣ አምስቱ በአማራ ክልል፣ አንዱ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እና ሦስቱ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የሚደረጉ ናቸው።

# ኮቪድ-19 እና የምርጫው ሂደት

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከጊዜ፣ በሂደቱ ወቅት ከሚኖረው የህዝብ ደህንነት እና ከባለድርሻ አካላት ሚና አንጻር በኢትዮጵያ ምርጫ ለይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። መራጮች፣ ዕጩዎች እና ደጋፊዎቻቸው፣ የምርጫ ኃላፊዎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ አክቲቪስቶች እና ታዛቢዎች በምርጫው ሂደት ውስጥ ደህንነታቸው ተጠብቆ መሳተፍ የሚችሉበትን ምህዳር መፍጠር ወሳኝ የሆነ ጉዳይ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ወረርሽኙን ለመዋጋት እና የህዝቡን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚደረጉ ጥረቶችን ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ አስፈላጊ ከሆኑ መሰረታዊ ነጻነቶች ጋር አመጣጥኖ ማስኬድ እና በየአካባቢው ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚወሰዱ እርምጃዎች ለማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ዕጩ ያልተገባ ጥቅም እንደማያስገኙ ለማረጋገጥ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው።

ይፋዊ ግምቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ እስከ ሰኔ 14ቱ ምርጫ ድረስ በኢትዮጵያ ከ275,000 በላይ ሰዎች በኮቪድ መያዛቸው እና ወደ 4,000 የሚጠጉ ሰዎች በበሽታው የተነሳ ህይወታቸው ማለፉ ሪፖርት ተደርጎ ነበር።[24] በኮቪድ-19 የተያዙ ሰዎች ቁጥር የመጋቢት ወር መጨረሻ ላይ ከፍተኛው ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረ እና በቀን ከ2,000 በላይ ሰዎች እንደ አዲስ በበሽታው በመያዝ ላይ የነበሩ ሲሆን ሰኔ 14 ላይ ይህ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል። በተመሳሳይ መልኩ ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር የሚያዝያ ወር አጋማሽ ላይ ከፍተኛው ደረጃ ላይ ደርሶ በቀን 35 ሰዎች የሚሞቱበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን በኋላ ላይ በሚታይ መልኩ በጣም ቀንሷል። በምርጫው ዕለት በበሽታው የተያዙ አዲስ ሰዎች ቁጥር በቀን ከ100 በታች የወረደ ሲሆን የሞቱ ሰዎች ቁጥር ደግሞ ከ10 በታች ወርዷል። ነገር ግን በሀገሪቱ ውስጥ ትክክለኛ የጤና መረጃዎችን ከማግኘት ጋር ተያይዞ ባሉ ተግዳሮቶች የተነሳ የኮቪድ-19 መረጃዎች በበሽታው የተያዙ እንዲሁም የሞቱ ሰዎችን ቁጥር አሳንሰው ሊያቀርቡ እንደሚችሉ በስፋት ይታመናል። ምንም እንኳን ኢትዮጵያ እስከ እ.ኤ.አ. 2021 መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ 110 ሚሊዮን ከሆነው የሀገሪቱ አጠቃላይ ህዝብ ውስጥ 20 በመቶውን አስከትባለሁ ብላ ተስፋ የምታደርግ ቢሆንም እስከ ሰኔ አጋማሽ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ክትባት ያገኙት 2.2 ሚሊዮን ሰዎች ብቻ እንደሆኑ ሪፖርቶች ይጠቁማሉ። የኢትዮጵያ መንግስት እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል እና የመራጮችን፣ የምርጫ ኃላፊዎችን፣ የዕጩዎችን እና የደጋፊዎቻቸውን እንዲሁም የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች ደህንነት ለመጠበቅ ፕሮቶኮሎችን ዘርግተዋል። ከእነዚህም ውስጥ ማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ፣ ማስክ ማድረግ እና የእጅ ሳኒታይዘር/ሳሙና መጠቀም ተጠቃሽ ናቸው፤ ሆኖም ግን እርምጃዎቹ ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ አልተደረጉም።

ኮቪድ-19 በምርጫው ዕለት በሚከናወነው ሂደት እና የምርጫ ኃላፊዎች እና መራጮች በሂደቱ ውስጥ ደህንነታቸው ተጠብቆ ለመሳተፍ በመቻላቸው ላይ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከወገንተኝነት ነጻ የሆኑ ሲቪክ ቡድኖች ምርጫውን ለመታዘብ በሚኖራቸው አቅም ላይም ጭምር ተጽዕኖ ያሳድራል። በተጨማሪም በወረርሽኙ ወቅት ወደ ኢትዮጲያ መጓዝ አዳጋች መሆኑ (እንዲሁም የጸጥታው ሁኔታ) ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ያሉባቸውን እንቅፋቶች የሚያባብስ እና ምርጫውን ከመጠበቅ እና የምርጫውን ሂደት በተመለከተ ገለልተኛ እና ከወገንተኝነት ነጻ የሆነ መረጃ ከመስጠት አንጻር የዜጋ ታዛቢዎች ቀድሞውንም የሚጫወቱትን ወሳኝ ሚና ከፍ የሚያደርግ ነው።

# የምርጫ ክልሎች አከላለል

በሕገ መንግስቱ መሠረት የምርጫ ክልሎች ድንበር የህዝብ ቆጠራ ውጤትን እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሚያቀርበውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይወሰናል። በተጨማሪም የድምጽ እኩልነት በሕገ መንግስቱ ውስጥ ጥበቃ የሚደረግለት ሲሆን በምርጫ ክልሎች መካከል ያለው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ልዩነት ከ15 በመቶ መብለጥ የለበትም የሚል ገደብ በሕግ ድንጋጌዎች ውስጥ ተቀምጧል።[25]

ምንም እንኳን እ.ኤ.አ. በ2007 የተደረገው የህዝብ ቆጠራ ውጤቶች ያሉ ቢሆንም እና በቂ ውክልና የለም በሚል በአንዳንድ ባለድርሻ አካላት የሚቀርበው ቅሬታ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 547 የምርጫ ክልሎች ለአሥሩ ክልሎች እና ለሁለቱ በቻርተር የሚተዳደሩ ክልሎች የተከፋፈሉበት መንገድ አዲስ በተቋቋመው የሲዳማ ክልል ካልሆነ በስተቀር ከ1987 ወዲህ ተከልሶ አያውቅም። እ.ኤ.አ. በ2017 እንዲደረግ ታቅዶ የነበረው የህዝብ ቆጠራ የተላለፈ በመሆኑ ነባሩ የወንበር ክፍፍል በዚህኛው ምርጫም ቀጥሏል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በምርጫ ክልሎች መካከል ያለውን የድምጽ ብዛት ሊቀይሩ የሚችሉ ከፍተኛ የስነ-ህዝብ ለውጦች ተከስተዋል ተብሎ ይታሰባል። ሞቻ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ በተለይም የብሔረሰቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ጠብቆ ከማቆየት አንጻር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ክልል ድንበሮችን ላለመከለስ ያስተላለፈውን ውሳኔ በመቃወም የተከራከረ ቢሆንም ወረዳዎችን መልሶ ከማካለል በፊት ብሔራዊ የሕዝብ ቆጠራ መደረግ አለበት በማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያቀረበውን ክርክር በማጽናት ፍርድ ቤቱ በፓርቲው ላይ ወስኖበታል።

የመራጮች ምዝገባ ቁጥሮች በክልሎች መካከል የድምጽ እኩልነት ያመኖሩን ያሳዩ ነበሩ። ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል 41,041 በምርጫ ክልል በአማካይ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር በማስመዝገብ ዝቅተኛውን ቦታ የያዘ ሲሆን የአፋር ክልል ደግሞ 164,234 በምርጫ ክልል በአማካይ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር በማስመዝገብ ከፍተኛውን ቦታ ይዟል። ይህም ወደ 400 በመቶ የሚጠጋ ልዩነት በመሆኑ በድምጽ ዕኩልነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው። በአጠቃላይ ያሉት የምዝገባ አሀዞች ከተመዘገቡት መራጮች አንጻር አፋር፣ ጋምቤላ፣ ኦሮሚያ፣ ሱማሌ እና ሲዳማ ክልሎች በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ያላቸው ውክልና ከሚገባው በታች መሆኑን እና አማራ፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እና ደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ደግሞ ያላቸው ውክልና ከሚገባው በላይ መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው።

24 የሮይተርስን [የኮሮና ቫይረስ ክትትል] ይመልከቱ።

25 የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 38(1)(ሐ)፤ አዋጅ ቁ. 1162/2011፣ አንቀጽ 13(1)(ለ)።

# የመራጮች ምዝገባ

ኢትዮጵያ ለእያንዳንዱ ምርጫ አዲስ የመራጮች መዝገብ የምትጠቀም በመሆኑ ለመምረጥ ብቁ የሆኑ መራጮች በሙሉ ድምጻቸውን መስጠት እንዲችሉ ከምርጫው አስቀድመው መመዝገብ ነበረባቸው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንዲሁም በኋላ ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖች በምዝገባ ሂደቶች ዙሪያ የመራጮች ስልጠና ረጃዎችን በመላ ሀገሪቱ አሰራጭተዋል። ለመመዝገብ ግለሰቦች በቀበሌያቸው ወዳለ የምርጫ ጣቢያ መሄድ እና የቀበሌ መታወቂያቸውን ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ከዚያም ለመምረጥ ብቁ የሆኑ ግለሰቦች ዝርዝር መረጃቸው የምርጫ ጣቢያው የመራጮች መዝገብ ላይ በእጅ ተመዝግቦ የምርጫ ካርድ ይሰጣቸዋል። ምንም እንኳን የመረጡ ሰዎች ጣት ላይ የማይለቅ ቀለም የተደረገ ቢሆንም በእጅ የሚጻፍ የመራጮች መዝገብ ጥቅም ላይ መዋሉ አንድ ሰው ከአንድ ጊዜ በላይ ሊመዘገብ የሚችልበትን ዕድል ከፍ አድርጎታል።

ሲጀመር የመራጮች ምዝገባ ጊዜ ከየካቲት 22 እስከ መጋቢት 21 እንዲሆን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም መጀመሪያ ላይ ከመጋቢት 16 እስከ ሚያዝያ 15 ድረስ ወዳለው ጊዜ ተሸጋግሮ ነበር። የመራጮች ምዝገባ ሲጀመር የተለያዩ ቦታዎች ላይ ተመሳሳይ አልነበረም እንዲሁም በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ያሉ የምርጫ ጣቢያዎች ከመጀመሪያው ጀምሮ የተከፈቱ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ዘግይተው ነበር የተከፈቱት። የሚያዝያ ወር መጀመሪያ አካባቢ በሥራ ላይ የነበሩት እና መራጮችን መመዝገብ ይችሉ የነበሩት ግማሽ ያህሉ የምርጫ ጣቢያዎች ብቻ እንደነበሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይፋ አድርጓል። መጀመሪያ ላይ የነበረው ዝቅተኛ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር በሁለተኛው የሚያዝያ ወር አጋማሽ ላይ እንዲመዘገቡ መራጮችን የማሰልጠን እና/ወይም የማነቃነቅ ሥራቸውን እንዲያጠናክሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን እና አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ያነሳሳ ነበር። መገናኛ ብዙሀን እንደዘገቡት ከሆነ የሀገሪቱ ፌዴራል መንግስትም እንዲሁ በራሱ ተነሳሽነት ከክልሎች ጋር አብሮ በመሥራት የመራጮች ምዝገባ አስተዳደርን ለማቀላጠፍ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ይህ ህዝብን የማነቃቃት ሥራ የፖለቲካ አድሎ ነበረበት የሚል ስጋት እንዳላቸው ገልጸዋል። የሚያዝያ ወር መጨረሻ አካባቢ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከ41,000 በላይ የምርጫ ጣቢያዎች ክፍት መሆናቸውን ገልጿል። ሚያዝያ 15 ላይ ሂደቱ እስከ ሚያዝያ አጋማሽ ድረስ ካልተጀመረባቸው አአካባቢዎች ውስጥ በነበሩት በአፋር እና በሱማሌ ክልሎች የመራጮች ምዝገባ እስከ ግንቦት 6 ድረስ በሦስት ሳምንታት ተራዝሟል እንዲሁም በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች እስከ ሚያዝያ 29 ድረስ በሁለት ሳምንታት ተራዝሟል። ያንን ተከትሎም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ምዝገባ በመላው ሀገሪቱ እስከ ግንቦት 6 ድረስ እንደሚራዘም አስታውቋል። እነዚህ ለውጦች ይፋ የተደረጉት ዘግይተው ነበር እንዲሁም ይፋ ከመደረጋቸው አስቀድሞ ሌሎች መዘግየቶች እንደሚኖሩ ሰፊ ግምቶች ነበሩ።

ግንቦት 6 ላይ የነበሩት የመጀመሪያ የመራጮች ምዝገባ አሀዞች ወደ 36 ሚሊዮን የሚጠጉ መራጮች (የመራጮች ምዝገባ ያልተደረገበትን ትግራይን ሳይጨምር) እንደመተዘገቡ ያሳያሉ። ከምርጫው ቀን አስቀድሞ ተሻሽለው የቀረቡ የምዝገባ አሀዞች ወደ 37 ሚሊዮን የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን ለመምረጥ እንደተመዘገቡ ገልጸዋል። ሆኖም ግን ሁለቱን አሀዞች በምናነጻጽርበት ጊዜ በአፋር እና በሱማሌ ክልሎች የተመዘገቡት መራጮች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እንደቀነሰ እና በአንጻሩ ደግሞ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ከ100 በመቶ በላይ ጭማሪ እንዳሳየ ለማስተዋል እንችላለን። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በይፋ ያስቀመጠው የምዝገባ ዒላማ ወይም ለመምረጥ የሚያስችል የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘውን ህዝብ ቁጥር የተመለከተ በይፋ የተቀመጠ የህዝብ ቆጠራ ግምት በሌበት ሁኔታ ብሔራዊ ወይም የክልል የምዝገባ መጠኖችንም ሆነ የዚያ ውጤት የሆኑትን የመራጮች መዝገቦች መገምገም የሚቻል አይደለም።

ሆኖም ግን ከህዝብ ግንኙነት ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የነበሩበት ድክመቶች እና የመራጮች ምዝገባ ቁጥሮች ላይ ከፍተኛ ለውጦች መታየታቸው አንዳንድ ባለድርሻ አካላት ስለ ሂደቱ ታማኝነት ስጋት እንዲገባቸው ምክንያት ሆኗል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በይፋ ያወጣው መረጃ ያልነበረ በመሆኑ በርካታ መገናኛ ብዙሀን ያልተረጋገጡ የምዝገባ አሀዞችን ሲዘግቡ የነበረ ሲሆን ይህም የመራጮች ምዝገባ በተጨባጭ ስለሚገኝበት ሁኔታ አሉባልታዎች እንዲናፈሱ ያበረታታ ነበር። የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ በ1,192 የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባን የታዘቡ 144 ታዛቢዎችን በመላው ሀገሪቱ አሰማርቷል። ታዛቢዎቹ ያቀረቡት ሪፖርት ለመራጮች ምዝገባ እንቅፋት የሆኑ የጸጥታ እና ከሎጂስቲክስ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶች እንደነበሩ የጠቆመ ነበር። በተጨማሪም የምርጫ ጣቢያዎች የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ተደራሽ ከመሆናቸው እና ሴቶች ያላቸው ውክልና ከሚገባው በታች ከመሆኑ እንዲሁም ከምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ጋር በተያያዘ ስጋቶችን እንዳሏቸው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መዘግየቶቹ ሊከሰቱ የቻሉት በከፊል በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ እንደሆነ ገልጿል፡- ማቴሪያሎችን ከማጓጓዝ ጋር የተያያዙ ችግሮች፤ ፌዴራል እና አንዳንድ የክልል ባለሥልጣን አካላት (በተለይም ደግሞ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ከመመዝገብ ጋር በተያያዘ) የነበራቸው ትብብር ደካማ መሆኑ፤ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የምርጫ ጣቢያዎች ሥራ የሚያስኬዱ ጥራት ያላቸው ሠራተኞችን ከመሳብ ጋር የተያያዙ ችግሮች፤ እና በርካታ ክልሎች ውስጥ ያለው እየተባባሰ ያለ የጸጥታ ሁኔታ። እነዚህ ችግሮች መኖራቸው በሌሎች አስተያየት ሰጪዎችም በስፋት የተረጋገጠ ነው። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ማስፈራራትን፣ አግባብ ያልሆነ መደለልን እና አግባብ ያልሆነ የሀብቶች አጠቃቀምን ወይም ኃላፊነትን ያለአግባብ መጠቀምን ጨምሮ የተለያዩ ጥሰቶች እና ግድፈቶች መኖራቸውን ገልጸዋል። የፖለቲካ ፓርቲዎች የመራጮች ምዝገባ ሂደቱን በተመለከተ በርካታ ቅሬታዎችን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያቀረቡ ሲሆን በሱማሌ ክልል የቀረቡትን ቅሬታዎች ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አጣሪ ጉባዔ አቋቁሟል እንዲሁም በመጨረሻም በክልሉ ምርጫው በአጠቃላይ ወደ ሌላ ጊዜ ተላልፏል።[26] በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሌሎች ቦታዎች ከመራጮች ምዝገባ ጋር በተያያዘ የነበሩ ግድፈቶችን ለመፍታት አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ወስዷል።

26 ቅሬታዎቹ በአዲስ አበባ ክፍለ ከተማዎች የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽ አልነበሩም ከሚለው አንስተው በአንድ የምርጫ ጣቢያ እንዲኖር የሚፈቀደውን የመራጮች ብዛት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አሠራር ደካማ መሆኑን እና ዕድሜያቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ተመዝግበዋል የሚሉትን ይጨምራሉ።

## የመራጮች ስልጠና

የመራጮች ስልጠና ኃላፊነቱ የሆነው ዋነኛው ተቋም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከየካቲት ወር 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በድምሩ በሦስት ዙር የመራጮች ስልጠና ዘመቻ አከናውኗል። የመጀመሪያው ዙር የመራጮች ምዝገባ ሥነ-ሥርዓቶች ላይ ያተኮረ ነበር፤ ሁለተኛው እና በጣም ረጅሙ ዙር ደግሞ የመራጮች ስልጠናን ዒላማ ያደረገ ነበር። የምርጫው ቀን ሲጠጋ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ስልጠና ይዘቱን በምርጫው ቀን ስለሚኖረው ሥነ-ሥርዓት ገለጻ ወደመስጠት ቀይሮታል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በእያንዳንዱ ክልል ሁለት የመራጮች ስልጠና ባለሞያዎችን መድቧል እንዲሁም በብሔራዊ፣ በክልል፤ እና በመንግስት እንዲሁም በግል ቴሌቪዥን እና ሬዲዮ እንዲሁም በህትመት፣ በበይነ መረብ እና በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ማስታወቂያችን ለህዝቡ በንቃት አስተላልፏል። ማስታወቂያዎች የቀረቡት በአምስት ዋና ዋና ቋንቋዎች ነበር እንዲሁም በአብዛኛው በማህበረሰብ ሬዲዮዎች አነስተኛ ተናጋሪ ወዳላቸው ቋንቋዎች ተተርጉመዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንደገለጸው ከሆነ በመራጮች ስልጠና ዙሪያ በሠራቸው ሥራዎች ወደ 32.7 ሚሊዮን አካባቢ ሰዎችን አዳርሷል። በዚህም ከመራጮች ስልጠና ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ሥራዎች የተሰሩ ቢሆንም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የህረተሰብ ክፍሎች ስለ ምርጫው በቂ መረጃ አልነበራቸውም የሚል ስጋት እንዳላቸው በርካታ አስተያየት ሰጪዎች ገልጸዋል።

ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ዕውቅና የተሰጣቸው ቢሆንም የመራጮች ስልጠና ለማከናወን የቻሉት ወደ ግማሽ ያህሉ ብቻ እንደሆኑ እና የማዳረስ ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደነበር አስተያየት ሰጪዎች ገልጸዋል። የገንዘብ እጥረት ለበርካታ ድርጅቶች ተግዳሮት የነበረ ሲሆን ምን አልባትም ዕውቅና ከማግኘት ጋር ተያይዞ የገንዘብ ድጋፍ ይኖራል የሚል እምነት የነበራቸውም ሊሆን ይችላል። አብዛኛዎቹ የመራጮች ምዝገባ ሂደቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሥራቸውን አልጀመሩም ነበር። አብዛኛዎቹ አስተያየት ሰጪዎች እንደገለጹት ከሆነ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች እንቅስቃሴዎች በአብዛኛው በአዲስ አበባ እና በሌሎች ትላልቅ የከተማ ማዕከላት የተወሰነ ነበር። ፊት ለፊት የሚደረጉ ስብሰባዎች (በሥራ ላይ በነበሩት የኮቪድ-19 መከላከያ እርምጃዎች የተነሳ በአንድ ክፍል ጊዜ ከ50 ሰዎች በላይ እንዳይሳተፉ የሚከለክል ገደብ ነበር)፣ የጎዳና ላይ ትዕይንቶች፣ በራሪ ወረቀቶችን እና አጫጭር ጽሁፎችን ማሰራጨት እንዲሁም አጭር የጽሁፍ መልዕክቶችን መላክ ከተከናወኑት ዋና ዋና የመራጮች ስልጠና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው። ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጡ በመሆናቸው በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን ለህዝብ የተላለፉ ማስታወቂያዎች በአንጻሩ ጥቂት ነበሩ። በመራጮች ስልጠና ላይ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን የማዳረስ ችሎታ ለማሳደግ ሲባል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሴቶችን፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችን፣ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚኖሩ መራጮችን እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ጨምሮ ርቀው በሚገኙ አካባቢዎች እና ለተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የመራጮች ስልጠና እንዲሰጡ ለ12 የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በድምሩ 4 ሚሊዮን ብር (95,000 የአሜሪካ ዶላር አካባቢ) የሆነ አነስተኛ የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።

## የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ

አዲሱ የምርጫ ሕግ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲ እንደገና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንዲመዘገብ ይጠይቃል። በተጨማሪም ለሀገር አቀፍ ፓርቲዎች የሚጠየቀውን የመስራች አባላት ቁጥር ወደ 10,000 እና ለክልል ፓርቲዎች የሚጠየቀውን ደግሞ ወደ 4,000 ከፍ ያደረገ እና ይህም አስቀድሞ በተመሳሳይ ቅደም ተከተል ከነበረው 1,500 እና 750 ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ጭማሪ ያሳየ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንደገለጸው ከሆነ እንደገና ከተመዘገቡት 53 አወቃቀሮች ውስጥ 46 የፖለቲካ ፓርቲዎች በዚህ ምርጫ ዕጩዎችን አሰማርተዋል (20 ሀገር አቀፍ እና 26 የክልል) ። ሕጉ ሀገር አቀፍ እና የክልል ፓርቲዎች ማድረግ የሚችሉትን እንቅስቃሴ ለይቶ የማያስቀምጥ ሲሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የክልል ፓርቲዎች በአንድ ክልል ብቻ እንዲወዳደሩ የሚገድብ ውሳኔ በመስጠት ይህን ክፍተት ደፍኗል።

አራት የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ ማለትም የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ህብረት (ኦዴህ)፣ የገዳ ሥርዓት ፓርቲ፣ የኦሮሞ ነጻነት እና አንድነት ግንባር እና ኦሮሞ አቦ ፓርቲ፤ እንደገና ለመመዝገብ ያቀረቡትን ማመልከቻ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውድቅ ማድረጉን በመቃወም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከራክረው አሸንፈዋል። የፖለቲካ ፓርቲዎቹ እንዳሉት ከሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔውን አልፈጸመም እንዲሁም ሥነ-ሥርዓቱን ተከትሎ ፎርማዎችን ለማረጋገጥ እና በመጨረሻም ፓርቲዎቹን ለመመዝገብ የወሰዳቸው እርምጃዎች የሌሉ ሲሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በበኩሉ ፓርቲዎቹ መስፈርቶቹን ያላሟሉ መሆኑን ገልጿል። በመጨረሻም ፓርቲዎቹ ወደ ፍርድ ቤት ተመልሰው በመሄድ የአፈጻጸም ክስ መስርተው ማመልከቻቸው እንደገና እንዲታይ ማድረግ ነበረባቸው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እነዚህን ፓርቲዎች ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ወደመመዝገብ የሄደውም ከዚያ በኋላ ነው።

## የዕጩዎች ምዝገባ

የሕግ ማዕቀፉ በተሻሻለበት ወቅት የዕጩዎች መምዝገባን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችም ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል። የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫን በተመለከተ የግል ዕጩዎች መሰብሰብ ያለባቸው የደጋፊዎች ፊርማ ወደ 5,000 ከፍ የተደረገ ሲሆን የፖለቲካ ፓርቲ ዕጩዎች ደግሞ 3,000 ፊርማዎችን መሰብሰብ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ ዕጩ ለመሆን የተቀመጡት መስፈርቶች የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የግል ዕጩ ከሆኑ ወደ 3,000 እና የፓርቲ ዕጩ ከሆኑ ደግሞ ወደ 1,500 ዝቅ ተደርገውላቸዋል።

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጸደቀውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔ ተከትሎ በፖለቲካ ፓርቲዎች የታጩ የፓርላማ ዕጩዎች ከ2013 ምርጫ አስቀድመው ፊርማዎችን እንዲሰበስቡ አይጠየቁም። ውሳኔው የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ከግምት ውስጥ በማስገባት ንክኪን ለመቀነስ እና ማህበራዊ ርቀትን ለመጠበቅ ሲባል የጤና ሚኒስቴር ያወጣውን መመሪያ መሰረት ያደረገ ነበር። ሆኖም ግን የግል ዕጩዎች ለመመዝገብ ፊርማዎችን ማሰባሰብ ነበረባቸው። መጀመሪያ ላይ ከየካቲት 8 እስከ 21 ድረስ እንዲሆን ታቅዶ የነበረውን የመራጮች ምዝገባ ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እስከ የካቲት 25 አራዝሞታል። አብዛኛዎቹ ፓርቲዎች በመራጮች ምዝገባ ሂደቱ ወቅት ተግዳሮቶች አጋጥመውናል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል እንዲሁም በርካታ ፓርቲዎች ይበልጥ ዕጩዎችን ማስመዝገብ ፈልገው የነበረ ቢሆንም ዛቻ እንደደረሰባቸው፣ እንደታሰሩ ወይም ሰነዶችን እንዳያቀርቡ እንቅፋት እንደተቀመጠባቸው ተናግረዋል።

በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ዋና ዋና ተቃዋሚ ፓርቲዎችን፣ አነግን እና ኦፌኮን ጨምሮ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው እንደማይሳተፉ በመጋቢት ወር ገልጸዋል። የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ካልተፈቱ፣ የፓርቲዎቻችን ጽ/ቤቶች ካልተመለሱልን፣ ሁሉን አቀፍ የሆነ ድርድር ካልተደረገ እና የፖለቲካ ውይይት ካልተደረገ በምርጫው አንሳተፍም የሚሉ ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀምጠዋል። በተጨማሪም በፓርቲው ውስጥ የተከሰቱ ክስተቶች በአነግ ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደሩበት ተገልጿል። በመሆኑም ሰኔ 14 ምርጫ ከተደረገባቸው በኦሮሚያ የሚገኙ 170 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልሎች ውስጥ በ104 የምርጫ ክልሎች ለምርጫው የተወዳደረው አንድ ዕጩ ብቻ ነው።

ሰኔ 11 ቀን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 9,357 የፖለቲካ ፓርቲ ዕጩዎችን እና 148 የግል ዕጩዎችን ጨምሮ 9,505 ዕጩዎች በምርጫው እንደሚወዳደሩ ገልጿል።[27] የዕጩ ምዝገባ ሂደቱ ግልጽነት የሰፈነበት አልነበረም እንዲሁም ምርጫ ከመደረጉ ከአንድ ወር በፊት ጀምሮ ለውጦች እንዳይደረጉ የሚከለክል የሕግ ድንጋጌ ቢኖርም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንደገለጸው ከሆነ ምትክ የማድረግ እና ከምርጫው ራስን የማግለል እንቅስቃሴዎች እስከ ግንቦት ወር መጨረሻ ድረስ አካባቢ ሲደረጉ ነበር። በበርካታ መቶዎች የሚቆጠሩ ምትክ የማድረግ እና ከምርጫው ራስን የማግለል ተግባራት ምንም ዓይነት ማብራሪያ ሳይሰጥባቸው ተከናውነዋል። ቦርዱ የዕጩዎችን ዝርዝር በምርጫ ክልል ከፋፍሎ ይፋ ያደረገውም ድምጽ የመስጠት ሂደቱ ከመጀመሩ አምስት ቀናት አስቀድሞ ሰኔ 9 ድረስ ዘግይቶ ነው።[28] የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ ተወዳዳሪዎች የሚቀመጡበትን መንገድ ለመሰን ዕጣ አውጥቷል። መጨረሻ ላይ የታተሙት የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ላይ የተዘለሉ እና በትክክል ያልተጻፉ ነገሮች እንደነበሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አረጋግጧል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በእስር ላይ የነበሩ አራት የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ ዕጩዎችን አልመዘግብም ማለቱን ተከትሎ ፓርቲው ለፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቦ አሸንፏል። ሆኖም ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የዕጩዎች ምዝገባ ሂደቱ ተጠናቋል የሚል ክርክር በማቅረብ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ አላከበረም። ከዚያም ፓርቲው ወደ ፍርድ ቤት በመመለስ የቀድሞው የፍርድ ቤቱ ውሳኔ እንዲፈጸምለት የከሰሰ ሲሆን በድጋሚ አሸንፏል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድም ውሳኔውን በማክበር የአራቱን ዕጩዎች ስም በምርጫ ካርዶቹ ላይ አኑሯል። ያንን ተከትሎ ዕጩዎቹን ከእስር ለማስፈታት የፍርድ ቤት አቤቱታ ቀርቦ ውድቅ ተደርጓል።

# የምርጫ ቅስቀሳው ምህዳር

የምርጫ ቅስቀሳው ጊዜ በይፋ የካቲት 8 ጀምሮ ከምርጫው ቀን ሰኔ 14 አምስት ቀናት አስቀድሞ ተጠናቋል። የኑሮ ውድነት፣ ሥራ አጥነት፣ የብሔር ግጭቶች እና ጸጥታ በምርጫ ቅስቀሳ ላይ ገነው ከወጡ ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው። ቅስቀሳዎችን ለማድረግ ፓርቲዎች እና ዕጩዎች ተሸከርካሪዎች ላይ የተገጠሙ ድምጽ ማጉያዎችን ተጠቅመዋል፣ የድጋፍ ሰልፎችን እና ከመራጮች ጋር የሚደረጉ ስብሰባዎችን አዘጋጅተዋል፣ የቤት ለቤት እና የመንደር ለመንደር ቅስቀሳዎችን አድርገዋል እንዲሁም አጫጭር ጽሁፎችን ከመበተናቸውም በተጨማሪ ባነሮችን እና ፖስተሮችን ተጠቅመዋል። በተጨማሪም በህትመት፣ በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን በከፊል ለዕጩዎች የተሰጠውን ነጻ የአየር ሠዓት በመጠቀም እንዲሁም በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት ቅስቀሳዎች ተደርገዋል።

ፓርቲዎች ለውይይት እና ልዩነቶችን ለመፍታት እንደ የጋራ መድረክ የሚያገለግል የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ጉባዔ የመሰረቱ ሲሆን ይህም ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። በመጋቢት ወር 2011 ዓ.ም. የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ጉባዔው አባላት የሥነ ምግባር ደንብ ፈርመዋል እንዲሁም ደንቡ ተግባራዊ የሚደረግበትን እና የጉባዔው አካላት ሥራቸውን የሚሠሩበትን የሥነ-ሥርዓት ደንብ አጽድቀዋል።[29] የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ጉባዔው ቢሮ እና ጽ/ቤት ሰጥቶታል። የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ጉባዔው ጽ/ቤት ለሚሰራቸው ሥራዎች አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዕውቅና የሰጡ ሲሆን ጽ/ቤቱ ግጭቶችን ለመፍታት ወደ ክልሎችም እንዲሁ ተልዕኮዎችን አከናውኗል። በተጨማሪም በክልል ደረጃ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ጉባኤዎች ተቋቁመዋል።

ምንም እንኳን በዚህ ምርጫ ወቅት የመሰብሰብ እና ሀሳብን የመግለጽ ነጻነቶችን ከማግኘት አንጻር ከፍተኛ መሻሻሎች የታዩ ቢሆንም አጠቃላይ ምህዳሩ ማስፈራራት ስለመኖሩ እና የመጨወቻ ሜዳው ያልተስተካከለ ስለመሆኑ በስፋት የተነሱ ቅሬታዎች ችላ የተባሉበት ነበር፤ ይህም እንደ ዕጩ እንዲሁም እንደ መራጭ በሴቶች እና የሌሎች የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች አባል በሆኑ ግለሰቦች ላይ በአንጻሩ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደረ ነበር። ሆኖም ግን በተደጋጋሚ ዕጩዎች እንደሚታሰሩ፣ አባላቶቻቸው አካላዊ ጥቃቶች እንደሚደርስባቸው፣ የፓርቲ ቢሮዎች ጥቃት እንደሚፈጸምባቸው እና የቅስቀሳ ማቴሪያሎችን ማውደም እንደሚፈጸም ተቃዋሚ ፓርቲዎች የገለጹ ሲሆን ይህም ዕጩዎች በቅስቀሳ ወቅት ከእስር ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል የሚሉ የሕግ ድንጋጌዎችን የሚጻረር ነው።

ግንቦት 19 ትልቁ ተቃዋሚ የሆነው ኢዜማ ዕጩዎቹ እና አባላቱ በአማራ እና በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል እንደታሰሩ እና አካላዊ ጥቃት እንደተፈጸመባቸው በመግለጽ እንዲህ ያሉት ጥሰቶች በሚፈጸሙበት ከባቢ ሁኔታ ውስጥ ነጻ እና ፍትሀዊ ምርጫ መደረግ ስለመቻሉ ጥያቄ አንስቷል። በአማራ ክልል በስልጣን ላይ ያለው ብልጽግና ፓርቲ ጠንካራው ተፎካካሪ የሆነው አብንም እንዲሁ በአሶሳ (ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ) ሰባት ዕጩዎቹ እንዲሁም አንድ ዕጩው በድሬ ዳዋ እንደታሰሩ የገለጸ ሲሆን ፓርቲው ይህን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሪፖርት ካደረገ በኋላ ከዕጩዎቹ ውስጥ የተወሰኑት ተለቀዋል። የብልጽግና ፓርቲ ሚሊሻዎች ተቃዋሚዎችን ለማስፈራራት በቀበሌ ደረጃ ተደራጅተዋል የሚል እናት ፓርቲ መግለጫ ያወጣ ቢሆንም በጸጥታ ኃይሎች የተወሰደ ምንም እርምጃ የለም። በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የሚወደደሩ አንድ የግል ዕጩ የግል ዕጩዎች በህገ ወጥ መንገድ ታስረዋል ብለዋል። ግልጽ የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት የሌለ በመሆኑ ከምርጫው ቀን አስቀድመው የፖለቲካ ፓርቲዎች የተናገሩትን መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቅሬታዎቹን በብዛት እና በስፋት ለማተናገድ አልቻለም ማለት ይቻላል።

ግንቦት 27 አብንን፣ ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲን፣ እናት ፓርቲን፣ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲን (መኢአድ) እና ህብር ፓርቲን ጨምሮ የአምስት የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብስብ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቅሬታ ደብዳቤ አቅርቧል። በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ የፓርቲዎቻቸው ዕጩዎች፣ አመራሮች እና ደጋፊዎች ላይ ግድያዎችን፣ የግድያ ሙከራዎችን፣ እስሮችን እና ማስፈራራቶችን ፈጽሟል ካሉት ከመሪው ፓርቲ እና ከፖለቲካ እና የጸጥታ ኃይሎቹ ጋር በተያያዘ ያሉባቸውን ስጋቶች ገልጸዋል። ፓርቲዎቹ ተፈጽመዋል ያሏቸው እነዚህ ድርጊቶች እንዲቆሙ ጠይቀዋል እንዲሁም ሰላማዊ ምርጫ እንዲኖር በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ያሉ የጸጥታ ኃይሎች ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

27 ከ148 የግል ዕጩዎች ውስጥ 86ቱ ወይም ወደ 60 በመቶ የሚጠጉት የሱማሌ ክልል የክልል ምክር ቤት ምርጫ ላይ የሚወዳደሩ ናቸው።

28 በጣም ብዙ ዕጩዎችን ያስመዘገቡት ፓርቲዎች ብልጽግና ፓርቲ (ብፓ፣ 2,799)፣ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ እና ዴሞክራሲ ፓርቲ (ኢዜማ፣ 1,540)፣ እናት (605)፣ ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ (578)፣ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን፣ 510) እና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (466) ነበሩ። የኢትዮጵያ ማህበራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲን፣ ህዳሴ ፓርቲን፣ የአዲሱ ትውልድ ፓርቲን፣ የሲዳማ አንድነት ፓርቲን፣ የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ንቅናቄን፣ የጋምቤላ ህዝብ ነጻነት ንቅናቄን፣ የሲዳማ ህዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ድርጅትን፣ የኢትዮጵያ ህብረት ዴሞክራሲያዊ ፓርቲን፣ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲን፣ የአፋር ህዝብ ፓርቲን፣ ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲን እና የወላይታ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባርን ጨምሮ በርካታ ፓርቲዎች ያስመዘገቡት ከ100 እስከ 250 ዕጩዎችን ነው። የተቀሩት 28 ፓርቲዎች ሁላቸውም ያስመዘገቡት ከ100 ያነሱ ዕጩዎችን ነው።

29 የሥነ-ምግባር ደንቡ አንቀጽ 5 የጾታ አገላለጽ ድንጋጌን ያካተተ ሲሆን በደንቡ ውስጥ በወንድ ወይም በሴት ጾታ የተገለጸው ሌላኛውን ጾታም እንደሚመለከት ይገልጻል። የሥነ-ምግባር ደንቡ የወሲባዊ ትንኮሳ ጉዳዮችን የማይጠቅስ ቢሆንም አዋጅ ቁጥር 1162/2011ን አንቀጽ 134 በማጣቀስ ማስፈራራት እና አመጽ መቀስቀስ ክልክል መሆኑን ይገልጻል።

እንደ ሞቻ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ የቁጫ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ የዶንጋ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እና የአገው ብሔራዊ ሸንጎ ያሉ የክልል እና ብሔርን መሠረት ያደረጉ ፓርቲዎች በአጠቃላይ ምርጫው ወቅት ከብልጽግና ፓርቲ ጋር ተቀናጅተው በሚሰሩ የአካባቢ ባለስልጣን አካላት ትንኮሳ እና መድሎ ተፈጽሞብናል በማለት ቅሬታ አቅርበዋል። አስተያየት ሲጪዎች እንዳሉት ከሆነ ዒላማ የሆኑበት ምክንያት በከፊል በዞን ደረጃ ራሳቸውን የማስተዳደር ፍላጎት ስላላቸው ነው።

በተጨማሪም አንዳንድ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የዘር ወቅት መሀል ላይ የምርጫውን ቀን ከቅዳሜ ወደ የሥራ ቀን (ሰኞ) በመቀየሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ተችተዋል።[30] ኋላ ላይ ግን ባለስልጣን አካላት በምርጫው ቀን ሥራ ዝግ እንዲሆን አድርገዋል። በተጨማሪም የምርጫው ቀን ላይ ሊዘንብ ይችላል የሚል ስጋት የነበረ ሲሆን ይህም መራጮች በምርጫ ጣቢያዎች ለመሰለፍ ትዕግስቱ ይኖራቸዋል ወይ የሚል ጥያቄን አስነስቷል።

## ለምርጫ ቅስቀሳ የሚውል ገንዘብ

የምርጫ አዋጁ በፖለቲካ ፓርቲዎች ገቢ እና ሀብት ምንጭ ላይ ቁጥጥር ያደርጋል እንዲሁም ግልጽነትን እና የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የምርጫ ቅስቀሳ ገንዘብ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዱ የተወሰኑ ድንጋጌዎችን ያካተተ ነው።[31] አዲሱ ሕግ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሀብት እና ዕዳ ዓመታዊ ሪፖርት ኦዲት ተደርጎ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መቅረብ እንዳለበት የሚያዝ ቢሆንም ይፋ እንዲደረጉ አያስገድድም። ከውጭ ሀገር ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ መቀበል የተከለከለ ሲሆን ከግለሰቦች መቀበል ግን ክልክል አይደለም። የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢያንስ ለአሥር ዓመታት ዓመታዊ የፋይናንስ ኦዲታቸውን መዝግበው የማስቀመጥ ግዴታ አለባቸው።

ኢዜማን፣ አብንን እና መኢአድን ጨምሮ ዋና ዋና የሚባሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮችን እንዲሁም በርካታ ሌሎች ፓርቲዎች እና የግል ዕጩዎች መሪው ፓርቲ በስልጣን ላይ ከመሆን ጋር ተያይዞ ከሚገኙት መደበኛ ጥቅሞች በላይ ተጠቃሚ መሆኑን ጨምሮ የምርጫ ቅስቀሳ መጫወቻ ሜዳው የተዛባ መሆኑን የገለጹ ሲሆን ለዚህም በከፊል ምክንያቱ የሀገሪቱ የፖለቲካ ታሪክ ነው። መጋቢት 6 ቀን በሚሌኒየም አዳራሽ በብልጽግና ፓርቲ የተዘጋጀውን እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ አብዛኛዎቹ የካቢኔ አባላት፣ የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ የብልጽግና ፓርቲ አመራሮች እና በርካታ የተለያዩ ነጋዴዎች በተገኙበት ፓርቲው ከ1.5 ቢሊዮን ብር (34 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር) በላይ ያሰባሰበበትን የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት እንደ ምሳሌ በመጥቀስ የንግዱ ማህበረሰብ የሚያደርገው ድጋፍ የተዛባ እንደሆነ ገልጸዋል። በተጨማሪም የንግዱ ማህበረሰብ የበቀል እርምጃ ይወሰድብኛል የሚል ፍራቻ ያለበት በመሆኑ በግልጽ ሊደግፋቸው እንደማይችል ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገልጸዋል።

አብዛኛዎቹ ፓርቲዎች በስልጣን ላይ ያለው ብልጽግና ፓርቲ ከቀበሌ አንስቶ እስከ ፌዴራል ደረጃ የመንግስት ሀብትን እና ስልጣኑን ለምርጫ ቅስቀሳ ያለአግባብ መጠቀሙን በመግለጽ ቅሬታ ቅርበዋል። የመንግስት ሀብትን ካለምንም ቅጣት ያለአግባብ መጠቀም ከዚህ ቀደም በነበሩ ምርጫዎች እንዲሁም በአሁኑ ምርጫ የተለመደ ችግር መሆኑ ይገለጻል።

የሕግ ማዕቀፉ ቅስቀሳ ማድረግ በማይቻልበት የጥሞና ወቅት ትላልቅ የመሰረተ ልማት እና የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ማስመረቅን ወይም ይፋ ማድረግን በግልጽ አይከለክልም፤ በተጨማሪም መንግስት የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች በማስተዋወቅ እና የምርጫ ቅስቀሳ በማድረግ መካከል መስመሩ የቱ ጋር እንደሚሰመር መለየት ቀላል አይደለም። እንዲህ ያሉት ዝግጅቶች የምርጫ ቅስቀሳው የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ በተደጋጋሚ ይከሰቱ የነበረ እና አብዛኛውን ጊዜ ይዘጋጁ የነበረውም የሳምንት የእረፍት ቀናት ላይ የነበረ ሲሆን የአካባቢ ታዳሚዎችን ያካተቱ እና በመገናኛ ብዙሀን በስፋት የተዘገቡ ነበሩ። ሌሎች ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ያክል ሰኔ 10 ቀን በአማን (ደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል) አየር ማረፊያ እና በምርጫው ዕለት በአዲስ አበባ በአንድ አውራ ጎዳና እና በዳቦ ፋብሪካ የተደረገውን ጨምሮ በዕጩነት የሚወዳደሩ አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት የምርጫ ቅስቀሳ በማይደረግበት የጥሞና ወቅት ፕሮጀክቶችን አስመርቀዋል እንዲሁም ጎብኝተዋል። በመሆኑም በስልጣን ላይ ባለው ፓርቲ እና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ከሀብት እና ከአቅም አንጻር ከፍተኛ ግፍተት አለ። አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች 2010 እና 2011 ላይ ገና ሙሉ በሙሉ ሥራ ያልጀመሩ ወይም እንደ አዲስ የተቋቋሙ ነበሩ።

በተጨማሪም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለተወዳዳሪዎች ከመንግስት የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ በቂ እንዳልነበረ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለምርጫ ቅስቀሳ ከመንግስት የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ ዘግይቶ እንዳከፋፈለ በመጥቀስ ቅሬታቸውን ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በድምሩ 98 ሚሊዮን ብር (2.2 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር) በሁለት ዙር ለፖለቲካ ፓርቲዎች አከፋፍሏል።[32] የመጀመሪያው የ483,452 ብር (10,998 የአሜሪካ ዶላር) ክፍያ ከሚያዝያ ወር አጋማሽ ጀምሮ በምርጫው ላይ ለሚሳተፍ ለእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ተላልፏል፤ ሁተኛው ዙር እና የተቀረው የገንዘብ ድጋፉ ሁለት ሦስተኛ በእያንዳንዱ የተመዘገበ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዕጩ እና የክልል ምክር ቤት (ብር 2,643 ወይም 60 የአሜሪካ ዶላር)፣ በእያንዳንዷ ሴት ዕጩ (ብር 9,982 ወይም 227 የአሜሪካ ዶላር)፣ በእያንዳንዱ የአካል ጉዳት ያለበት ዕጩ (ብር 155,722 ወይም 3,542 የአሜሪካ ዶላር) እና በእያንዳንዷ የፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኃላፊነት ላይ ያለች ሴት (ብር 255,062 ወይም 5,802 የአሜሪካ ዶላር) የሚሰጡ ቦነሶችን ባካተተው ቀመር መሠረት የግንቦት ወር አጋማሽ ላይ ተከፍሏል።[33] ብልጽግና ፓርቲ (23.2 ሚሊዮን ብር ወይም ወደ 528,000 የአሜሪካ ዶላር አካባቢ) እንዲሁም ኢዜማ (11.3 ሚሊዮን ብር ወይም 257,000 የአሜሪካ ዶላር) ከፍተኛውን ድርሻ ያገኙ ሲሆን ያንን ተከትሎ ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ (4.6 ሚሊዮን ብር ወይም 105,000 የአሜሪካ ዶላር)፣ እናት ፓርቲ (3.5 ሚሊዮን ብር ወይም 80,000 የአሜሪካ ዶላር)፣ የኢትዮጵያ ህብረት ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት እና አብን ይገኛሉ። የግል ዕጩዎች መጀመሪያ ላይ ያልተካተቱ የነበረ ቢሆንም የምርጫ ቅስቀሳ የማይደረግበት የጥሞና ወቅት ዋዜማ ላይ እያንዳንዳቸው 50,000 ብር (1,137 የአሜሪካ ዶላር) እንደተሰጣቸው ተገልጿል። ሆኖም ግን ሕጉ በሚጠይቀው መሠረት የገንዘብ ድጋፉን ለመቆጣጠር የወጣ ምንም ዓይነት መመሪያ የለም።

30 በአማራ ክልል ለምሳሌ አብዛኛዎቹ ኦርቶዶክስ ክርስትያን የገጠር አርሶ አደሮች ሀይማኖታቸው በሚያዘው መሠረት በወር ውስጥ የተወሰኑ ቀናት ላይ ሥራ አይሠሩም። ነገር ግን እንደዚያ ካላደረጉ ሳይሰሩ ያሳለፉት ቀን ምርታማነታቸውን እና ገቢያቸውን የሚቀንሰው በመሆኑ ኪዚያ ውጭ ባሉት ቀናት እርሻቸው ላይ መሥራትን እንደሚመርጡ የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ። ቅሬታቸውን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያቀረቡት አምስት ዋና ዋና ፓርቲዎች ከዚያ ይልቅ ምርጫው እሁድ ሰኔ 20 ቀን እንዲደረግ ሀሳብ አቅርበዋል።

31 ከአንቀጽ 100-113።

32 ግንቦት 19 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ ክፍፍል ዝርዝር መረጃ የፌስቡክ ገጹ ላይ አውጥቷል።

33 ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተገኘው መረጃ መሠረት ብልጽግና ፓርቲ 11.7 ሚሊዮን ብር በሴት ዕጩዎች (1,171)፣ 2.3 ሚሊዮን ብር የአካል ጉዳት ባለባቸው ሰዎች (15) እና 1.3 ሚሊዮን ብር የምርጫ ሥራ አስፈጻሚ ኃላፊነት ላይ ባሉ ሴቶች (5) አግኝቷል። በአንጻሩ ትልቁ የተቃዋሚ ፓርቲ የሆነው ኢዜማ በተመሳሳይ ቅደም ተከተል 1.8 ሚሊዮን ብር (183)፣ 3.4 ሚሊዮን ብር (22) እና 1.5 ሚሊዮን ብር (6) አግኝቷል።

# ከምርጫው ጋር በተያያዘ ያለው የጸጥታ ሁኔታ እና ግጭቶች

ኢትዮጵያ በርከታ የጸጥታ ቀውሶች እያጋጠሟት ያለች ከመሆኑም በላይ በማያቋርጡ የጸጥታ ችግሮች ስትጠቃ ቆይታለች። የግጭቶቹ መንስኤዎች ዘርፈ ብዙ ሲሆኑ ይህም የኢትዮጵያን ስር የሰደዱ የብሔር ክፍፍሎች እና የኃይል ክፍፍል የሚያንጸባርቅ ነው። በግጭቶች እና በግጭት ስጋቶች የተነሳ የተፈጠሩት የጸጥታ ችግሮች በሴቶች፣ በቁጥር አናሳ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ በወጣቶች፣ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና በሌሎች የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ላይ የተለዩ እና በአንጻሩ በጣም ከፍተኛ የሆኑ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን አሳድረዋል እንዲሁም ከምርጫው ጋር በተያያዘ እንዲሁም ከዚያ ውጭ የሰብአዊ እና የፖለቲካ መብት ጥሰቶች ሊፈጸሙ ይችላሉ የሚል ፍተኛ ስጋትን የፈጠሩ ናቸው።

በግንቦት ወር 2012 ዓ.ም. ምርጫው መተላለፉን ተከትሎ የነበሩት ውጥረቶች እና ግጭቶች ቀስ በቀስ ጨምረዋል። በትግራይ ከተፈጠረው ጦርነት በተጨማሪ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እና በኦሮሚያ አመጾች ተጠናከረዋል እንዲሁም በአማራ፣ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እና በአፋር-ሱማሌ ድንበር አካባቢዎች የብሔር ውጥረቶች ጨምረዋል። ሆኖም ግን (ምንም እንኳን በትግራይ ከምርጫው በኋላ ብዙም ሳይቆይ ግጭቱ የጨመረ ቢሆንም) የምርጫው ቀን በከፍተኛ የጸጥታ ጥበቃ በሰላማዊ ሁኔታ ተጠናቋል።

ጥቅምት 25 በትግራይ ከታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በተጨማሪ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እና በአማራ ክልል በብሔሮች መካከል የነበሩ ውጥረቶች ተባብሰው ህይወትን ወደቀጠፉ ግጭቶች መቀየራቸውን ተከትሎ የአመጽ እንቅስቃሴዎችን ለመዋጋት እና ሕግ እና ርዓትን ለማስከበር ሲባል ከጥር 14 እስከ ሚያዝያ 21 ባለው ጊዜ ውስጥ በክልሎቹ ሦስት ኮማንድ ፖስቶች ተቋቁመዋል። የኦሮሞ ነጻ አውጪ ሰራዊት (“ሸኔ”) በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት አሸባሪ ቡድን ተብሎ በባለሥልጣን አካላት ታውጇል። በኦሮሚያ ልዩ ዞን አንዳንድ ወጣቶች በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሲሆን በቁጥጥር ሥር የዋሉትም ለጽንፈኛ ኃይሎች ድጋፍ ሲያደርጉ እና ምርጫውን ለመረበሽ ጥረት ሲያደርጉ የነበረበት ቦታ ላይ ነው ተብሏል። የኦሮሞ ነጻ አውጪ ሰራዊት ሰኔ 11 ቀን ባወጣው መግለጫ በምርጫው ያለመሳተፍ ጥሪውን እንደገና አስተላልፏል። የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በገለጹት መሰረት በምርጫው ቀን በተፈጸሙ አምስት ጥቃቶች ቢያንስ 25 ሰዎች ህይወታቸው አልፏል።

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 መሠረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አባል የሆነበት ብሔራዊ የጸጥታ ግብረ ኃይል ሰፋ ያሉ የምርጫ ጸጥታ ጉዳዮችን የሚቆጣጠር ሲሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ ጣቢያዎች እና በጽ/ቤቶቻቸው ጸጥታ የማስጠበቅ ኃላፊነት አለበት። የምርጫ ጸጥታ አካላት መመሪያ ቁ. 12/2013 በምርጫ መገልገያ ስፍራዎች እና እንቅስቃሴዎች ላይ የተመደቡ የጸጥታ ሠራተኞችን ኃላፊነቶች፣ ሥነ-ሥርዓቶች እና የሥነ-ምግባር ደንብ ይበልጥ በዝርዝር ያስቀምጣል። የቁጥጥር ማዕቀፉ በኢትዮጵያ በዓይነቱ የመጀመሪያ ሲሆን ምንም እንኳን የሚሳተፉ ኤጀንሲዎችን እና በሥራ ላይ ያሉ አባላት የሚለዩበትን መንገድ በተመለከተ በተወሰነ መልኩ ግልጽነት የሚጎድለው ቢሆንም ከፍተኛ መሻሻል መኖሩን የሚጠቁም ነው። ከላይ እስከታች ከተሰጡ የምርጫ ጸጥታ ማስከበር ስልጠናዎች ጋር ተጣምሮ ማዕቀፉ የምርጫ ጸጥታ ሠራተኞች ኃላፊነታቸውን እንዲገነዘቡ እና ሕጉን እንዲያከብሩ አግዟል። ሰኔ 14ን ጨምሮ በዚያ ሰሞን ለሰባት ተከታታይ ቀናት በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃዎ ላይ በጋራ የተሰማሩ የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ አባላት ቡድኖች ከጸጥታ ጋር የተያያዙ የሕግ ድንጋጌዎች አፈጻጸም ላይ ቁጥጥር አድርገዋል።

በሕጉ መሠረት የምርጫ ጸጥታ ማስከበር አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት በሕግ የተቋቋሙ የጸጥታ አካላት ብቻ ናቸው። ሆኖም ግን በተለያዩ የአማራ፣ የድሬ ዳዋ እና የኦሮሚያ ክፍሎች ሚሊሻዎች ለምርጫ እንቅስቃሴዎች የጸጥታ ጥበቃ እንዲያደርጉ ስልጠና የተሰጣቸው መሆኑን የክልል እና የዞን አስተዳደሮች ለህዝብ ያወጧቸው መግለጫዎች ይጠቁማሉ።[34] ከጋምቤላ እና ከሲዳማ በስተቀር በሁሉም ክልሎች ሚሊሻዎች ከምርጫ ጋር የተያያዙ ኃላፊነቶችን እንደተወጡ የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ብሔራዊ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ገልጸዋል። በተጨማሪም በአማራ ክልል በከተማ ማዕከላት ሚሊሻዎችን አስተውለዋል። ሚሊሻዎችን በምርጫ ላይ ማሳተፍ ከፖለቲካ እና ከብሔር አንጻር ወገንተኛ ተደርገው የሚታዩ እና ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጥቃቶችን በመፈጸም የሚታወቁ ቡድኖችን የምርጫው ቀን ላይ ትክክል እንደሰሩ ተደርገው እንዲታዩ የማድረግ አደጋ አለው።

የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሪፖርቶች፣ ቅሬታዎች፣ ጋዜጣዊ መግለጫዎች እና የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን ሪፖርቶች መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ከንዑስ-ብሔራዊ የክልል ተዋንያን/ከክልል እና ከአካባቢ ባለሥልጣን አካላት ጋር ግንኙነት ባላቸው አካላት ተፈጽመዋል የተባሉ ከ230 በላይ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጥቃቶችን የሰበሰበ ሲሆን ይህም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ዕጩዎችን፣ ወኪሎችን፣ አባላትን፣ ደጋፊዎችን እና የቤተሰብ አባላትን፣ መራጮችን እና የምርጫ ኃላፊዎችን ዒላማ ማድረግን ጨምሮ ወደ 150 የሚጠጉ በመራጮች ምዝገባ ወቅት የተፈተሙ ጥቃቶችን ያካትታል። ከክስተቶቹ ውስጥ ትንኮሳ፣ ማስፈራራት፣ ማስገደድ፣ አስተዳደራዊ መዘግየቶች፣ ሕገ ወጥ እስር፣ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተደረጉ የቤት ብርበራዎች፣ ድብደባ፣ የግድያ ሙከራዎች እና ግድያ ይገኙበታል። የአካባቢ የቀበሌ አስተዳደር፣ የአካባቢ ፖሊስ ኃይሎች እና የገጠር ሚሊሻዎች በተለይም ደግሞ በምርጫው ዕለት ተቀናጅተው መሥራታቸውን በተዘዋዋሪ የሚጠቁሙ በርካታ መረጃዎች አሉ። እነዚህ የኃይል ጥቃቶች ተፈጽመዋል የተባለው በአብዛኛው በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል እንዲሁም በሱማሌ እና በአፋር ክልል ውስጥ በሚገኙ የተወሰኑ አካባቢዎች ነው። ምርጫ በሂደት ላይ እያለ የሚፈጸሙ የኃይል ጥቃቶች በተወዳዳሪዎች መካከል የተስተካከለ መጫወቻ ሜዳ እንዳይኖር ያደርጋሉ እንዲሁም ሂደቱ ተአማኒነት ያለው ስለመሆኑ ስጋቶችን ይፈጥራል። በተጨማሪም ሴቶች እና በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሔረሰቦች በሁሉም ደረጃዎች ላይ በምርጫው ለመሳተፍ ያላቸው ተነሳሽነት እንደዲቀንስ ሊያደርግ ይችላል።

በምርጫው ዕለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተለያዩ ጋዜጣዊ መግለጫዎች አንዳንድ ከጸጥታ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ሰጥቷል። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የክልል ቅርንጫፎች እና በፖሊስ ኮሚሽኖች መካከል የነበረው ቅንጅታዊ አሠራር በአብዛኛዎቹ ክልሎች ውስጥ ሲገመገም አዎንታዊ ነበር። ሆኖም ግን ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የክልል ጽ/ቤቶች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተከናወነው የስጋት ምዘና ውስጥ ያልተሳተፉ በመሆኑ በጸጥታ ዙሪያ የነበራቸው መረጃ ውስን ነበር። የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮውም እንዲሁ የምርጫ ጸጥታን የተመለከተ መረጃ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከማግኘት ጋር በተያያዘ ተግዳሮቶች ገጥመውታል። በተጨማሪም የፖሊስ ኮሚሽኑ የኢትዮጵያን ምርጫ ለመታዘብ ውስን ተልዕኮው የሰጠው መረጃ ግልጽ አልነበረም፤ በተመሳሳይ መልኩ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የክልል ቅርንጫፎች ፖሊስ ስላብራራው ዝርዝር የጸጥታ ስምሪት ዕቅድ የሚያውቁት ነገር አልነበረም።

ከምርጫ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ የግጭት ስጋቶችን ለመፍታት በርካታ የስጋት ቅነሳ ሥራዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፤ ሆኖም ግን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰቱን እና ምርጫው መራዘሙን ተከትሎ በነበሩ የበጀት ውስንነቶች የተነሳ እነዚህ ሥራዎች ተቀንሰዋል። በብሔራዊ ደረጃ እንዲሁም በክልሎች የተቋቋመ ብዙ ባለድርሻ አካላትን

34 ለምሳሌ የድሬ ዳዋ መንግስት ግንኙነት ጉዳዮች ቢሮ ሰኔ 13፣ እንዲሁም የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ሰኔ 11 በደቡብ ወሎ ዞን “ሚሊሻዎች ምርጫው በሰላም እንዲከናወን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ በቁርጠኝነት ይሠራሉ” በሚል ርዕስ ፌስቡክ ላይ የለጠፉትን ይመልከቱ። በተጨማሪም በሌሎች የአማራ ክልል ክፍሎች የከተማ ማዕከላትን ጨምሮ ሚሊሻዎች መሰማራታቸውን አንድ የዞን አስተዳደር ባለስልጣን አረጋግጠዋል። አዲስ ስታንዳርድ፣ ግንቦት 12፣ “በኦሮሚያ ክልል የጉጂ ዞን 982 የአካባቢውን ሚሊሻዎች አስመረቀ”፣ ትዊተር ላይ ከተለጠፉ ፎቶዎች ጋር።

ያቀፈ መዋቅር የሆነው ጥምር የምርጫ ግጭት መከላከያ መድረክ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተመራ ነበር። ነገር ግን አንዳንደድ ጥምር የምርጫ ግጭት መከላከያ መድረኮች የተቋቋሙት ዘግይተው የነበረ ሲሆን ለዚህም በከፊል ምክንያቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለክልል ጽ/ቤቶች የገንዘብ ድጋፍ ዘግይቶ ማስተላለፉ እንደሆነ ተገልጿል። የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ቀድሞ ማስተንቀቂያ ዩኒቶች እንዲሁም እንደ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት፣ የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች፣ የሀይማኖቶች የጋራ ጉባዔ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ባሉ ተቋማት ከምርጫው ቀን አስቀድመው የተላለፉ የሰላም እና ሊፓርቲ ያለመወገን ጥሪዎች ስጋቱን ለመቀነስ ከተወሰዱ ሌሎች እእርምጃዎች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው። በአንጻሩ ረዘም ያለ ጊዜን ታላሚ ያደረጉ ሰላምን የማረጋገጥ ሥራዎችም እንዲሁ በመከናወን ላይ የነበሩ ቢሆንም ዘላቂ ሰላምን እና ዕርቅን ዕውን ለማድረግ የሚያስፈልገው ሀብት እና የፖለቲካ ቁርጠኝነት እንደሚጎድላቸው ተገልጿል።

# የመገናኛ ብዙሀን ምህዳር

በ1987 ዓ.ም. የወጣው ሕገ መንግስት ሀሳብን የመግለጽ፣ የፈለጉትን አመለካከት የመያዝ እና የመገናኛ ብዙሀን ነጻነትን እንዲሁም መረጃ የማግኘት መብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች አሉት። የመገናኛ ብዙሀን አዋጁ እንዲሁም በርካታ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለስልጣን መመሪያዎች በምርጫው ወቅት መገናኛ ብዙሀን የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ያስተዳድራሉ።[35] የመገናኛ ብዙሀን አዋጁ የመንግስት ብሮድካስተሮችን ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የሚከላከሉ ድንጋጌዎች አሉት እንዲሁም ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነ ነጻ ተቆጣጣሪ አካል የሆነውን የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን አቋቁሟል። ነገር ግን የጸደቀው ዘግይቶ በመሆኑ በ2013 ዓ.ም. ከሚደረገው ምርጫ አስቀድሞ ትርጉም ባለው መልኩ ተግባራዊ ሊደረግ አልቻለም።

አዎንታዊ በሆነ መልኩ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን ሕጉ ባስቀመጠው ቀመር መሠረት ለ46 ፓርቲዎች እና 143 የግል ዕጩዎች ነጻ የዜና ህትመት እና ወደ 1,414 አካባቢ ነጻ የአየር ሠዓታትን 57 የመንግስት እና የንግድ መገናኛ ብዙሀን ላይ መድቧል።[36] አብዛኛዎቹ አስተያየት ሰጪዎች በተመደበው ነጻ የአየር ሠዓት ደስተኛ መሆናቸውን የገለጹ እና ይህም ሁሉም ፓርቲዎች ዓላማቸውን እንዲያስተዋውቁ እና በፖለቲካ ክርክር ውስጥ እንዲሳተፉ ዕድሉን የሰጠ እና ፓርቲዎቹም የተጠቀሙበት ቢሆንም በስልጣን ላይ ባለው ብልጽግና ፓርቲ የታጩ ዕጩዎችን ጨምሮ በዚህ ረገድ ዕጩዎች የቀረበላቸውን ግብዣ ያልተቀበሉባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ።[37]

በምርጫው ወቅት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን ገለልተኛ መገናኛ ብዙሀንን ጂኦግራፊያዊ ሽፋን በተመለከተ ከፖለቲካ ፓርቲዎች አምስት መደበኛ ቅሬታዎች ቀርበውለታል።[38] እንደዚያም ሆኖ ግን ፓርቲዎች እና ዕጩዎች ከተመደበው ነጻ የአየር ሠዓት ውስጥ በድምሩ ወደ 65 በመቶውን ተጠቅመዋል።[39] በአንጻሩ አነስተኛ የሆኑ ፓርቲዎች ነጻ የመገናኛ ብዙሀኑን የመጠቀም ዝቅተኛ ዕድል የነበራቸው ወይም ምንም ዕድል ያልነበራቸው ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ የአቅም ማነስ ወይም የቀረጻዎችን ዝግጅት ወጪ መሸፈን ያለመቻል ነው ተብሏል። በርካታ መገናኛ ብዙሀን ካልተጣራ መረጃ ወይም ከቋንቋ ጋር በተያያዙ ችግሮች የተነሳ ከፖለቲካ ፓርቲዎች የቀረቡላቸውን ይዘቶች የመለሱባቸው አጋጣሚዎች እንደነበሩ የኢትዮጵያን ምርጫ ለመታዘብ ውስን ተልዕኮው ያሳወቁ ሲሆን መገናኛ ብዙሀን ለሚያስተላልፉት ይዘት ኃላፊነት እንዳለባቸው ገልጸዋል። የተመደበውን ነጻ የአየር ሰዓት በፓርቲ እና በሚዲያ ከፋፍሎ የሚያሳይ መረጃ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን ድረገጽ ላይ የለም። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጠን ያደረጓቸውን ምክክሮች እና ስልጠናዎች የመገናኛ ብዙሀን ተወካዮች ያደነቁ ቢሆንም የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን ሥልጣን ላይ ላለው ፓርቲ ያደላል ተብሎ በመታሰቡ እና በጋዜጠኞች ሥራ ውስጥ በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ በግልጽ ጣልቃ በመግባቱ የተነሳ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጠንካራ ትችት ተሰንዝሮበታል።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን የመገናኛ ብዙሀንን የምርጫ ቅስቀሳ ሽፋን እንደማይከታተል እና በዚህም የተነሳ ሕጉ በሚጠይቀው መሠረት ምን ያህል ፍትሐዊ፣ ሚዛናዊ፣ ተመጣጣኝ ወይም ሁሉን አቀፍ እንደሆነ መገምገም እንደማይችል የገለጸ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ የአቅም ችግር ነው ብሏል። የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣንም ሆነ ሌላ ማንኛውም ቡድን በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ስላከናወኗቸው መገናኛ ብዙሀንን የመከታተል ሥራዎች ለህዝብ ያወጧቸው ሪፖርቶች የሉም። የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሞያዎች ማህበር በየወሩ አሀዛዊ መረጃዎችን ያወጣ ሲሆን ይህም ከመንግስት ወይም ከአንዳንድ የግል ብሮድካስተሮች ይልቅ ገለልተኛ መገናኛ ብዙሀን ይበልጥ ሚዛናዊ የሆነ ሽፋን እንደነበራቸው አስረግጦ የሚያሳይ ነበር።

የምርጫ ቅስቀሳ በማይደረግበት የጥሞና ጊዜ ላይ በተደጋጋሚ ጥሰቶች መፈጸማቸውን እና ኢዜማን ጨምሮ በርካታ ፓርቲዎች መደበኛ ቅሬታዎችን ማቅረባቸውን ተከትሎ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን (የጠቅላይ ሚኒስትሩን ቃለ መጠይቅ ለማስተላለፍ አቅደው ለነበሩ) የመንግስት እና የግል ብሮድካስተሮች ፖለቲካን በተመለከተ ገለልተኛ የመሆን ሕጋዊ ግዴታ እንዳለባቸው አሳስቧል። ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ቢሆንም መደበኛ መገናኛ ብዙሀን በመገናኛ ብዙሀን የጥሞና ጊዜው እና በምርጫው ዕለት ጭምር የብልጽግና ፓርቲ የበላይ አመራሮችን ወይም በስልጣን ላይ ያሉትን ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመለከቱ የዜና ይዘቶችን ማስተላለፋቸውን ቀጥለዋል፤ ይህም ከምርጫ ቅስቀሳ ጋር የተያያዙ ሁነቶችን እና የመንግስት እንቅስቃሴዎችን ለይቶ ለማየት አዳጋች አድርጎታል። የምርጫው ወጤት ይፋ የተደረገበት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሊቀ መንበር መገናኛ ብዙሀን ለምርጫ ቅስቀሳው ሽፋን የሰጡበት መንገድ በከፍተኛ ሁኔታ በሥልጣን ላይ ላለው ፓርቲ ያደላ እና በምርጫ ሂደቱ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ነበር በማለት ወቅሰዋል። ይህ በሚዲያው ላይ የተሰነዘረ ወቀሳ እና በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ስልጣኑን መጠቀሙን ማውገዝ ያልተለመደ እና ተቋሙ እና የተቋሙ ሊቀ መንበር ገለልተኛ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ጋዜጠኞች እና የመገናኛ ብዙሀን ባለሞያዎች ላይ ያለው ስጋት ይበልጥ እየጨመረ እንደመጣም አስተያየት ሰጪዎች ገልጸዋል። በመንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት ኢንተርኔት ላይ እንዲሁም ከኢንተርኔት ውጭ በሚሰሩ ጋዜጠኞች ላይ የሚፈጸሙ ሕገ ወጥ እስሮች፣ ዛቻዎች እና አካላዊ እና የቃል ጥቃቶች

35 የመገናኛ ብዙሀን ዕውቅና አሰጣጥ፣ አሠራሮች እና የሥነ-ምግባር መመሪያ ቁ. 2/2012፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል ዕጩዎች የመገናኛ ብዙሀን አጠቃቀም እና አመዳደብ መመሪያ፤ የምርጫ ቅስቀሳ ሥነ-ምግባር መመሪያ።

36 በመገናኛ ብዙሀን አዋጁ መሠረት ነጻ የአየር ሠዓት የሚመደበው የሚከተሉትን አራት ነገሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡- ፓርቲዎች በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና በክልል ምክር ቤቶች ውስጥ ያሏቸውን ወንበሮች፤ በምርጫው ላይ ያሉትን ዕጩዎች/የፖለቲካ ፓርቲዎች ብዛት፤ በምርጫው ላይ የሚወደደሩ ሴቶችን እና የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችን ብዛት፤ እና በምርጫው ላይ ለሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሙሉ ዕኩል የአየር ሠዓት መመደብን።

37 ሰኔ 11 ቀን የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን 14 መገናኛ ብዙሀን ላይ 142 ክርክሮች እንደተካሄዱ አስታውቋል።

38 የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን ሠዓት እንዲያገኙበት በተመደበላቸው መገናኛ ብዙሀን ጂኦግራፊያዊ የስፋት ወሰን ደስተኛ ስላልሆንን ሌላ መገናኛ ብዙሀን ላይ ሠዓት ይመደብልን በማለት ከፓርቲዎች የቀረቡ አራት ጥያቄዎችን መልሷል፤ በሌላ አምስተኛ አጋጣሚ ምንም እንኳን ጥያቄው የቀረበው በፓርቲው እና በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን መካከል ያለመግባባት መኖሩን መሠረት በማድረግ ቢሆንም የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን ሌላ መገናኛ ብዙሀን ላይ ሠዓት ለመመደብ አልተስማማም። በመጨረሻም ሚዲያው ክርክር ያስነሳውን ይዘት ለማስተላለፍ ፈቃደኛ ቢሆንም የአገው ብሔራዊ ሸንጎ ፓርቲ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል።

39 በድምሩ ከተመደበው ነጻ የሬዲዮ የአየር ሠዓት ውስጥ 65.6 በመቶው እንዲሁም ቴሌቪዥን ላይ ከተመደበው ነጻ የአየር ሠዓት ውስጥ 64.1 በመቶው ጥቅም ላይ ውሏል። የህትመት ጋዜጦች ላይ ከተሰጠው ነጻ ቦታ ውስጥም ወደ 34.3 በመቶ አካባቢው ጥቅም ላይ ውሏል (የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን)።

ጨምረዋል። በሰኔ ወር 2012 ዓ.ም. ጋዜጠኞች በፖሊስ ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ሠራዊት የታሰሩባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው[40] እና በ2013 ዓ.ም. ሁለት ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች መገደላቸው ከሚዲያ ባለሞያዎች ጋር በተያያዘ ያለውን የጸጥታ ከባቢ ሁኔታ አጠልሽቶታል እንዲሁም በኢትዮጵያ ከመናገር ነጻነት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ስጋቶችን ፈጥሯል። ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. ከተደረገው ምርጫ በኋላ ብዙም ሳይቆይ አሥራ ሁለት ጋዜጠኞች በይፋ ምንም ክስ ሳይመሰረትባቸው ወይም ካለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታሰሩ ሲሆን ይህም ፍርሀት እና ራስን በራስ ሳንሱር ማድረግ የሰፈነበት ምህዳር እንዲኖር አስተዋጽኦ አድርጓል።[41]

## ማህበራዊ ሚዲያ

በኢትዮጵያ የኢንተርኔት ሽፋን፣ ተደራሽነት እና የዋጋው ተመጣጣኝነት (በተለይም ደግሞ ለሴቶች) አሁንም በአፍሪካ በጣም ዝቅተኛ ከሚባሉት ውስጥ ነው።[42] እንደዚያም ሆኖ እንደ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን ያሉ ተቋማት የአማርኛ የፌስቡክ ገጾች ያሏቸው ሲሆን ከድረገጾቻቸው ጋር ሲነጻጸሩ ይበልጥ ቶሎ ቶሎ ወቅታዊ መረጃዎች ይደረጉባቸዋል። ሚያዝያ 15 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ የለጠፏቸውን አንዳንድ ችግር ያለባቸው ይዘቶች ለይቶ በማስቀመጥ የጥላቻ ንግግርን መጠቀምን እና አመጽ ማነሳሳትን በተመለከተ ሕጉ ምን እንደሚል ለአብን፣ ለብልጽግና ፓርቲ፣ ኢዜማ፣ ለኦፌኮ እና ለሌሎች ፓርቲዎች አሳስቧል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫው ወቅት የሀሰተኛ መረጃ ችግርን ለመፍታት እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ገጾችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከፌስቡክ ጋር እየሠራ እንደነበር ገልጿል።

በሚያዝያ እና በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም. ፌስቡክ ግንባር ቀደም ፕላትፎርሞቹ በሆኑት ፌስቡክ እና ኢንስታግራም ላይ በኢትዮጵያ ተጠቃሚዎች ላይ ያነጣጠሩ ሀሰተኛ እንቅስቃሴዎችን ተቀናጅተው ፈጽመዋል ያላቸውን የአካውንት መረቦች እንደሰረዘ አስታውቋል።[43] መነሻቸው ኢትዮጵያ በሆኑ አካውንቶች እና ኢትዮጵያ ከሚገኘው የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (INSA) ጋር ግንኙነት ባላቸው ግለሰቦች መካከል ግንኙነቶች እንደነበሩ የፌስቡክ ምርመራ ግኝት ጠቁሟል። በተጨማሪም ፕላትፎርሙ ከመጋቢት ወር 2012 ዓ.ም. እስከ መጋቢት ወር 2013 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ 87,000 የጥላቻ ንግግሮችን እንደሰረዘ ያስታወቀ ቢሆንም ስለ ይዘቶቹ እና በምን መልኩ እነሱን ለመሰረዝ ውሳኔ ላይ እንደደረሰ የሚገልጽ ተጨማሪ መረጃ ይፋ አላደረገም። ምንም እንኳን ከስፋት ወሰን እና ከማዳረስ አንጻር ውስን ቢሆንም ኢትዮጵያ ቼክን (Ethiopia Check) እና ሀቅቼክን (HaqCheck) ጨምሮ ገለልተኛ ሀቅን የማጣራት ሥራዎች በከፍተኛ ሁኔታ ሞያን የተላበሱ ሆነው ተገኝተዋል።

ከመጋቢት 23 እስከ ሰኔ 22 የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው 120 የፌስቡክ ገጾችን፣ 10 የቴሌግራም ቻናሎችን እና ስድስት የትዊተር አካውንቶችን መርምሯል።[44] የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ግኝት እንደሚያሳየው ከሆነ አብዛኞዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች የፌስቡክ ገጾች ያሏቸው ቢሆንም አብዛኞዎቹ አስፈላጊ የሆኑ የፖለቲካ እና ሲቪክ ገጾች አብዛኛውን ጊዜ የተረጋገጡ አይደሉም፤ ይህም የሀሰት የፖለቲካ ፓርቲ ገጾች የተለመዱ ከመሆናቸው አንጻር መራጮች እነሱን ትክክለኛዎቹን ገጾች እንዳይችሉ ሁኔታውን አወሳስቦታል። ፌስቡክ ላይ በክፍያ የተደረጉ ማስታወቂያዎች በሂደቱ ውስጥ የተወሰነ ሚና ተጫውተዋል። ፌስቡክ ላይ በክፍያ ከተደረጉት ማስታወቂያዎች ውስጥ አብዛኞዎቹ ምንጫቸው ከየት እንደሆነ የሚገልጽ ማስተባበያ አልነበራቸውም፤ ይህም ፌስቡክ ማስታወቂያን በማጽደቅ ሂደት ውስጥ ካስቀመጣቸው መስፈርቶች ውስጥ አንዱ ነው።

ብልጽግና ፓርቲ ፌስቡክ ላይ በሚገባ የተዋቀረ እና ገናና ሆኖ የሚገኝ ሲሆን ለዚህም በከፊል ምክንያቱ ብሔራዊ እንዲሁም የክልል ገጾች ያሉት መሆኑ ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ የግል የፌስቡክ ገጽ በኢትዮጵያ በጣም ዝነኛው የፖለቲካ ገጽ የነበረ እና በርካታ የሦስተኛ ወገን ገጾች ጠቅላይ ሚኒስትሩን የሚደግፉ ማስታወቂያዎችን ሲያደርጉ የነበሩ ሲሆን አንዳንዶቹ ከምርጫው በኋላ የተሰረዙ መሆኑን ለማስተዋል ተችሏል።

ኢዜማ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ማስታወቂያዎችን ያደረገው ብቸኛው ፓርቲ ቢሆንም በይፋ የምርጫ ቅስቀሳ በማይደረግበት የጥሞና ጊዜም ጭምር ማስታወቂያዎችን አድርጓል። ኢዜማ የማህበራዊ ሚዲያ ይዘቱ በዓይነቱ በከፍተኛ ሁኔታ ፖለቲካዊ የሆነው እና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚጠጋ ደረጃ ዝና የነበረው ብቸኛው ፓርቲ ነበር። በተጨማሪም ኢዜማ ፌስቡክ ላይ ያሉትን የመስተጋብር መገልገያዎች በመጠቀም #ኢዜማንይጠይቁ (#askEZEMA) በተሰኘው ዘመቻ አማካኝነት ከተጠቃሚዎች ጋር ለመገናኘት ችሏል። ምንም እንኳን ሌሎች ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳው የመጨረሻ ሳምንቶች ላይ ፌስቡክ ላይ የሚለጥፏቸውን ይዘቶች የጨመሩ ቢሆንም ትምህርታዊ ባህሪ ያላቸው ይዘቶች የታዩት በጣም አልፎ አልፎ ነበር እንዲሁም የደጋፊዎችን ስሜት ለመኮርኮር ታስበው የተቀረጹ ነበሩ።

በአብን፣ በኦፌኮ እና በአጋሮቻቸው የተለጠፉ የፌስቡክ ይዘቶች አንዳንድ ጊዜ ደጋፊዎቻቸው በሂደቱ ውስጥ እንዳይሳተፉ ጥሪ ያስተላለፉ ወይም የሚመርጡ ሰዎችን "ባንዳ" ብለው የጠሩ ነበሩ። ሂደቱን "የውሸት ምርጫ" በማለት ያጣጣለ ሌላ ትርክትም ነበር። ነጻነት እና እኩልነት እና ባልደራስ ለዕውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለመሪው ፓርቲ ያደላል በማለት በተደጋጋሚ ወቀሳ አቅርበዋል። በኦሮሚያ እና በትግራይ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች ላይ የሚለጠፉ የተጋነኑ ትርክቶች በምርጫው ዕለት ጭምር የቀጠሉ ከመሆኑም በላይ የውጤት ቅጾችን በማስመሰል የተቀነባበሩ ፎቶዎችን ጨምሮ ማስፈራራት፣ የኃይል ጥቃቶች እና ማጭበርበር ተፈጽመዋል የሚሉ ይዘቶች በምርጫው ዕለት እንዲሁም ልክ ከምርጫው በኋላ ሲሰራጩ ነበር።

40 ምንም እንኳን አብዛኞዎቹ በዋስ የተለቀቁ ቢሆንም በርካታ የፍርድ ቤት ጉዳዮች የሀሰት መረጃ ማሰራጨት ተፈጽሟል በሚል የተመሰረቱትን ጨምሮ አሁንም በሂደት ላይ ናቸው።

41 በተመሳሳይ ቅደም ተከተል ዩቲዩብን መሠረት ካደረጉት አውሎ ሚዲያ እና ኢትዮ ፎረም አሥር እና ሁለት ጋዜጠኞች። ሁለት የኢትዮ ፎረም ጋዜጠኞች በምርጫው ዕለት ለተወሰነ ጊዜ ማንነታቸው በማይታወቅ ሰዎች ታፍነው ተወስደው ተደብድበዋል።

42 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ተቋም (UNESCO) እ.ኤ.አ. በ2017 ባወጣው መረጃ መሠረት ማንበብ እና መጻፍ የሚችሉ ወንዶች 59.24 በመቶ ሲሆኑ ማንበብ እና መጻፍ የሚችሉ ሴቶች ደግሞ 44.42 በመቶ ናቸው።

43 የፕሮፋይሎቹን መሰረዝ በተመለከተ ፌስቡክ ያወጣውን መግለጫ ይመልከቱ።

44 ጥናቱ የተከናወነው በተወሰነ የክትትል ባለሞያዎች ቡድን ነው እንዲሁም ይዘቶችን ስልታዊ በሆነ መንገድ ኮድ ማድረግን (coding) ያካተተ አልነበረም። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ፌስቡክ ላይ ካለው ገጽ በተጨማሪ 19 የፖለቲካ ፓርቲ/የዕጩዎች ገጾች፣ 51 የመገናኛ ብዙሀን ገጾች፣ 14 የመንግስት ተቋማት ገጾች፣ 23 የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ገጾች፣ ሰባት የተጽዕኖ ፈጣሪዎች (influencers) እና አምስት የዳያስፖራ ገጾች ክትትል ተደርጎባቸዋል።

የጥላቻ ንግግር፣ ክብርን የሚነካ ቋንቋ፣ የተሳሳተ የሥርዓተ-ጾታ አመለካከት እና አመጽ የመቀስቀስ ተግባራት ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በተጨማሪ ጋዜጠኞችን ዒላማ በማድረግ ተፈጽመዋል (ሉሲ ካሳ እና ያየሰው ሺመልስ ተጠቃሽ ናቸው)። በተጨማሪም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ድምጽ የያዘ እና አምልጦ የወጣ የተባለ ግንቦት 23 ቀን በኬሎ ሚዲያ የተለቀቀ የድምጽ ፋይል ወዲያውኑ በከፍተኛ ሁኔታ ከተሰራጨ በኋላ ሌሎች ሚዲያዎች የተቀነባበረ መሆኑ አጋልጠዋል።[45] ግንቦት 9 ቀን ፌስቡክ፣ ዋትሳፕ እና ኢንስታግራም ለተወሰነ ጊዜ መጠቀም የማይቻል የነበረ ቢሆንም በምርጫው ወቅት ምንም ዓይነት የኢንተርኔት ወይም የቴሌኮሚዩኒኬሽን ማቋረጥ አልነበረም።[46]

# የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማካተት

## ሴቶችን ማካተት

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ወንዶች እና ሴቶች እኩል መብቶች እንዳሏቸው በግልጽ የሚደነግግ ቢሆንም በስፋት የሚስተዋል ወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃትን፣ ጎጂ ማህበራዊ ልማዶችን እና ሥርዓተ-ጾታን መሠረት ያደረጉ የኃላፊነት ክፍፍሎችን እና አጠቃላይ ግጭትን እና የጸጥታ ችግርን ጨምሮ ሴቶች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ትርጉም ባለው መልኩ እንዳይሳተፉ እና ተጽዕኖ እንዳያደርጉ የሚከለክሉ ከፍተኛ እንቅፋቶች አሁንም አሉ። ግጭት እና የጸጥታ ችግር ሴቶች በምርጫ ውስጥ እንደ ዕጩም ሆነ እንደ መራጭ እንዳይሳተፉ የሚከለክሉ ተብለው በስፋት የተጠቀሱ ከባድ እንቅፋቶች ናቸው። የኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያ ሴቶች ማህበር በምርጫ ሂደት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ላይ ክትትል ከማድረጉም በተጨማሪ በሴት የምርጫ ኃላፊዎች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ላይ ክትትል አድርጓል።[47] በምርጫ ሂደት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ፖለቲካ ውስጥ በማንኛውም ደረጃ ላይ በሚገኙ ሴቶች ላይ ካለማቋረጥ በሚደረግ ትንኮሳ፣ በስነ ልቦና ጥቃት፣ በአካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት መልኩ ሊከሰት የሚችል ከመሆኑም በላይ ሴቶች በአጠቃላይ ያላቸውን ዕምቅ አቅም የማዳከም ውጤትን ያስከትላል እንዲሁም ለዴሞክራሲም ጭምር ተግዳሮት ነው።

ቢያንስ የተወሰነ በመቶ ሴት ዕጩዎችን ላስመዘገቡ ወይም ሴት የፓርቲ አመራሮች ላሏቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ተጨማሪ ድጎማ መስጠትን እና ለፖለቲካ ፓርቲዎች ነጻ የአየር ሠዓት መመደብን ጨምሮ የሴቶን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሻሻል ሲባል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተደረጉ የሕግ እና ተቋማዊ ለውጦች በተወሰነ መልኩ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲጨምር አትግተዋል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንትን፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትን እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሊቀ መንበርን ጨምሮ ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ እንዲቀመጡ ሴቶች መሾማቸው እና መመረጣቸው ሴቶች በህዝባዊ ጉዳዮች ውስጥ ሊጫወቱ የሚገባውን ወሳኝ ሚና እና ፖለቲካው ከሥርዓተ-ጾታ አንጻር ይበልጥ አካታች መሆኑን የሚጠቁሙ አዎንታዊ ምልክቶች ተደርገው የሚታዩ ናቸው። ሆኖም ግን ከተመዘገቡት 53 የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ በሴት የሚመራው አንዱ ብቻ ነው እንዲሁም በፓርቲዎቹ መዋቅሮች ውስጥ የአመራር ቦታዎች ላይ ያሉት ሴቶች ቁጥር አሁንም 58 ብቻ በመሆኑ ዝቅተኛ ነው። ከዚህ ቀደም በነበረው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ሴቶች የነበራቸው ውክልና (39 በመቶ) በክልል ደረጃ በአማካይ ከነበረው (24 በመቶ) የበለጠ ቢሆንም ምክንያቱ ኢህአዴግ ያስቀመጠው ኢ-መደበኛ የኮታ ሥርዓት ሊሆን ይችላል።

በ2013 ምርጫ ላይ ያለው የሴት ዕጩዎች ተሳትፎ በ2007 ከነበረው ጋር ሲነጻጸር ከ29 በመቶ ወደ 21 በመቶ ወርዷል። አብዛኛዎቹ አስተያየት ሰጪዎች ለሴት ዕጩዎች ተሳትፎ መቀነስ በምክንያትነት የጠቀሱት እንደ የዛቻዎች እና ማስፈራሪያዎች መበራከት ያሉ የጸጥታ ስጋቶች መጨመራቸውን (ሴት ዕጩዎች ለእነዚህ ስጋቶች ይበልጥ ተጋላጭ ናቸው) እንዲሁም ከፍተኛ ያለመረጋጋት ያለበት የጸጥታ ሁኔታ መኖሩን ነው። የገንዘብ እና የሀብት እጥረት እና ሴቶች በህዝባዊ ጉዳዮች እና በፖለቲካ ውስጥ መሳተፋቸውን በተመለከተ ያሉ ልማዳዊ የተሳሳቱ የሥርዓተ-ጾታ አመለካከቶችም እንዲሁ ለሴቶች ተሳትፎ እንቅፋት ሆነዋል።

በድምሩ 1,976 ሴቶች ለፖለቲካ ፓርቲዎች በዕጩነት የተመዘገቡ ሲሆን ስድስት ደግሞ በግል ዕጩነት ተመዝግበዋል። አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤት ምርጫዎች ለሚወዳደሩ ዕጩዎች ያስቀመጧቸው የብቃት መስፈርቶች የተለያዩ ናቸው። በመሆኑም ሴቶች በይበልጥ የተመዘገቡት ለክልል ምክር ቤት ምርጫዎች ነው (ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተመዘገቡት 16 ሲሆኑ ለክልል ምክር ቤት የተመዘገቡት ደግሞ 22 ናቸው)። ብልጽግና ፓርቲ በአጠቃላይ ካሉት ዕጩዎች ውስጥ ወደ 42 በመቶው ሴቶች ቢሆኑም አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በዝርዝሮቻቸው ውስጥ ሴት ዕጩዎችን ማካተት ፈተና እንደሆነባቸው ይነገራል። አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዝርዝር የሥርዓተ-ጾታ ፖሊሲዎችን ያጸደቁ ቢሆንም ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የሚጠየቀውን 20 በመቶ ሴት ዕጩዎችን የማስመዝገብ መስፈርት ያሟሉት 13 ፓርቲዎች ብቻ ናቸው።[48]

ሴት ዕጩዎች በሙሉ በምርጫ ከመወዳደር ጋር በተያያዘ በአንጻሩ ከፍተኛ እንቅፋቶች የሚያጋጥሟቸው ቢሆንም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሴት ዕጩዎች እና ሴት የግል ዕጩዎች ተጨማሪ ተግዳሮቶች እንዳጋጠሟቸው ይነገራል። በጸጥታ ኃይሎች እንዲሁም በመሪው ፓርቲ አባላት የተፈጸሙ ማስፈራራቶች፣ ዛቻዎች እና የምርጫ ቅስቀሳ ጣልቃ ገብነቶች በአንጻሩ በብዛት ዒላማ ያደረጉት ሴት የተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩዎችን እንደነበረ በርካታ አስተያየት ሲጪዎች ገልጸዋል። ሴት የግል ዕጩዎች ፊርማዎችን ከመሰብሰብ እና ከመንግስት ለምርጫ ቅስቀሳ የሚሰጠው ድጎማ ዘግይቶ በመከፋፈሉ የተነሳ ከተፈጠሩ የገንዘብ ችግሮች ጋር የተያያዙ የተለያዩ ተጨማሪ ተግዳሮቶች አጋጥመዋቸዋል።[49]

በድምሩ 17,091,128 ሴቶች ለመምረጥ ተመዝግበዋል፤ ይህም በአጠቃላይ ከተመዘገቡት መራጮች ውስጥ 45 በመቶው ማለት ነው። ሁሉም ክልሎች ከሞላ ጎደል ያላቸው የሴት መራጮች ድርሻ ተመሳሳይ ቢሆንም በአፋር ክልል ከተመዘገቡት መራጮች ውስጥ ሴቶች ሰባት በመቶ ብቻ ነበሩ። ምንም እንኳን ክልሉ በተለምዶ ዝቅተኛ የመምረጥ ፍላጎት ሪፖርት የሚደረግበት ቢሆንም እንደ ደካማ የመራጮች ስልጠና እና ከጸጥታ ጋር የተያያዙ ስጋቶች ያሉ ተጨማሪ ምክንያቶች ሴቶች በህዝባዊ ጉዳዮች ውስጥ መሳተፍ የለባቸውም ከሚሉ የተሳሳቱ ባህላዊ አመለካከቶች ጋር ተደምረው ብቁ የሆኑ ሴት መራጮች ከ2013 ምርጫ እንዲገለሉ ምክንየት ሆነው ሊሆን ይችላል።

---

45 የድምጽ ፋይሉ ላይ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው የተባለው ድምጽ ገና ያልተደረገውን ምርጫ አሸንፈናል ሲል እንዲሁም ተቃዋሚዎችን በመደምሰስ ብልጽግና ፓርቲ ከምዕተ አመት በላይ የበላይ ሆኖ እንደሚቆይ እንደሚያረጋግጥ ቃል ሲገባ ይደመጣል። በተጨማሪም ንግግሩን የሚያደርገው ሰው የኃይል እርምጃን ጨምሮ ሥልጣን ላይ ለመቆየት ምንም ነገር ከማድረግ ወደ ኃላ እንደማይል ይናገራል።

46 ሆኖም ግን ትግራይ ውስጥ ኢንተርኔት እና ግንኙነት ተቋርጦ ነበር።

47 የኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያ ሴቶች ማህበርን በምርጫ ሂደት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ክትትልን የተመለከተ የመጀመሪያ መግለጫ ይመልከቱ።

48 አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የጾታ ኮታዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ሞክረው ነበር፤ ሆኖም ግን ሁል ጊዜም ስኬታማ ነበሩ ለማለት አይቻልም። ለምሳሌ፡- ኢዜማ 20 በመቶ ሴት ዕጩዎች ላይ አልደረሰም። አንዳንድ ሴቶች ፓርቲያቸው በስልጣን ላይ ካለው ብልጽግና ፓርቲ ጋር ከተቀላቀለ በኋላ የተሻለ ቦታ ላይ ደርሰዋል፡- ለምሳሌ የቀድሞ የደኢህዴን (የኢህአዴግ አካል) መሪ የነበሩት ሙፈሪያት ካሚል የሰላም ሚኒስትር ተደርገው ተሹመዋል፤ አሁን የጠፋው የአብዴፓ መሪ የነበሩት አያሸ መሀመድ የመከላከያ ሚኒስትር እንዲሁም በኋላ ላይ የልማት እና ኮንስትራሽን ሚኒስትር ሆነዋል። ሁለቱም ፓርቲዎች ብልጽግና ፓርቲን የተቀላቀሉት በታህሳስ ወር 2012 ዓ.ም. ነው።

49 መንግስት ለግል ዕጩዎች ድጎማ ያደረገው የምርጫ ቅስቀሳ የማይደረግበት የጥሞና ጊዜ ዋዜማ ላይ ሰኔ 9 ነው።

## በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሔሮችን እና ቋንቋዎችን ማካተት

ኢትዮጵያ ወደ 80 ለሚጠጉ ብሔሮች እና ቋንቋዎች ዕውቅና የሚሰጥ የብሔር ፌዴራሊዝም ሥርዓት ያላት ሀገር ናት። በ1987 ዓ.ም. በወጣው የሀገሪቱ ሕገ መንግስት መሠረት ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ቢያንስ 20 ልዩ የምርጫ ክልሎች ወይም ወንበሮች በብሔራዊ ደረጃ ዕውቅና ለተሰጣቸው በቁጥር አናሳ የሆኑ "ብሔረሰቦች እና ህዝቦች" የተያዙ ናቸው።[50] አስተያየት ሰጪዎች እንዳሉት ከሆነ የትኞቹ ብሔሮች እና ቋንቋዎች ወይም ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎች ልዩ ወንበር ለማግኘት ብቁ እንደሆኑ ለመወሰን የሚያገለግሉ በጽሁፍ የተዘጋጁ መስፈርቶች ኖረው አያውቁም። በተመሳሳይ መልኩ ልዩ የምርጫ ክልል ለመጨመር ወይም ለመሰረዝ የሚያገለግል ምንም ዓይነት ግልጽ ሂደት የለም እንዲሁም ሕገ መንግስቱ በ1987 ዓ.ም. ከወጣበት ጊዜ አንስቶ የልዩ ወንበሮች ዝርዝሩ ተሻሽሎ የሚያውቅ ይሁን ወይም አይሁን ግልጽ አይደለም። በተጨማሪም በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 31 ውስጥ ከተገለጹት ባለፈ ልዩ የምርጫ ክልሎች ውስጥ ለሚወዳደሩ ዕጩዎች የተቀመጡ የጽሁፍ መስፈርቶች የሉም።

በ2013 ካሉት 22 ልዩ ወንበሮች ውስጥ 15 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል፣ ሁለቱ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እንዲሁም በአማራ፣ በጋምቤላ እና በሀረሪ በእያንዳንዳቸው ክልሎች ውስጥ አንድ አንድ የሚገኙ ናቸው።[51] ልዩ ወንበሮች ላይ የሚቀመጡ ተወካዮች የሚመረጡት ከመደበኛዎቹ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ነው፡- ባገኙት ድምጽ ብዛት። ሆኖም ግን ሰኔ 14 ከ20ዎቹ ልዩ የምርጫ ክልሎች ውስጥ ምርጫ የተደረገው በ13ቱ ብቻ ነው (የሌሎቹ ልዩ የምርጫ ክልሎች ምርጫ ጳጉሜ 1 ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል)። ከእነሱም ውስጥ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ የሚገኘው ማኦ ኮሞ ልዩ እና በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የሚገኘው ዳሰነች ውድድር አልነበረባቸውም። የተቀሩት 11 የምርጫ ክልሎች ቢያንስ ሁለት ተወዳዳሪ ፓርቲዎች የነበሩባቸው ናቸው። በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል እንዲህ ባሉት ሁኔታዎች ውስጥ ዕጩዎችን ያሰማሩት ብሔራዊ ፓርቲዎች ብቻ ናቸው እንዲሁም የተወዳደሩ የክልል ወይም ብሔርን መሠረት ያደረጉ ፓርቲዎች የሉም።

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል በሚገኘው ዘይሴ ልዩ የምርጫ ክልል ኢዜማ ማሸነፉ ከዚህ ቀደም ኢህአዴግ እና የክልል አጋሮቹ የሚወዳደሩባቸው በነበሩት በልዩ የምርጫ ክልሎች ውስጥ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መሳተፋቸው ይበልጥ ትርጉም ያለው ፉክክር እንዲኖር እንደሚጠቅም የጠቆመ ነበር። ነገር ግን የሀረሪ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እና የአርጎባ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ልዩ የምርጫ ክልል ወንበሮች በቁጥር አናሳ ለሆኑ ብሔሮች እና ቋንቋዎች የተያዙ ናቸው በማለት እና ተፎካካሪዎቻቸው የሆኑት ሀገር አቀፍ ፓርቲዎች በልዩ የምርጫ ክልሎቹ ውስጥ የመወዳደር መብት የላቸውም ብለው በመከራከር ለትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቅሬታዎችን አቅርበዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለአርጎባ ልዩ እና ለሀረሪ ልዩ የምርጫ ሥነ-ሥርዓት እንዳዘጋጀ እና ምርጫዎቹ ጳጉሜ 1 እንደሚደረጉ ገልጿል። አስፈላጊ የሆኑ የምርጫ ማቴሪያሎችን ከአማርኛ ውጭ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች እና እንደ አዲስ በቅርቡ ወደተጨመሩት አራት ሌሎች ቋንቋዎች ለመተርጎም የተደረጉት ጥረቶች ውስን መሆናቸው አንዳንድ ብሔረሰቦች በተለይም ደግሞ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል እንዳይሳተፉ እንቅፋት ሆኗል።[52] ማህበረሰብ ሬዲዮዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን የመራጮች ስልጠና መልዕክቶች በየአካባቢው ባሉ ቋንቋዎች ተርጉመው ማስተላለፋቸው የገጠር ማህበረሰቦችን በተወሰነ መልኩ ለማዳረስ አስችሏል።

በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሔረሰቦችን እና ቋንቋዎችን ለማዳረስ ስትራቴጂ የቀረጸ ሀገር አቀፍ ፓርቲ የሌለ ሲሆን ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ያላቸውን ጠባብ ድጋፍ ለማስፋት የህብት እጥረት ያለባቸው መሆኑ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ያላቸው የገንዘብ ድጋፍ ውስን በመሆኑ እና ደካማ የመሠረተ ልማት መዋቅር በመኖሩ የተነሳ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዕውቅና የሰጣቸው የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ከከተማ አካባቢዎች በመውጣት በአካል የመራጮች ስልጠና እንቅስቃሴዎችን የሚያከናውኑባቸው አጋጣሚዎች ውስን ሲሆን ይህም በርካታ በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሔረሰቦች እንዳይካተቱ ምክንያት ሊሆን የሚችልበት ዕድል አለ።

## ወጣቶን ማካተት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ወጣቶች የሚለውን ቃል የሚተረጉመው ከ15 እስከ 29 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ብሎ ሲሆን መምረጥ የሚችልበት የዕድሜ ክልል ውስጥ ካለው ህዝብ ውስጥ ከ18 አስከ 29 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣቶች ወደ 40 በመቶ የሚጠጋውን ቦታ ሊይዙ እንደሚችሉ የህዝብ ቆጠራ ግምቶች ይጠቁማሉ። የተመዘገቡ መራጮችን በዕድሜ ከፋፍለው የሚያሳዩ ምንም ዓይነት በይፋ የወጡ አሀዞች የሉም። በወጣቶች ዘንድ የምርጫውን ሂደት በተመለከተ ግድ የለሽነት፣ ፍላጎት ማጣት እና ዕምነት ማጣት እንዳለ አብዛኛዎቹ አስተያየት ሰጪዎች በስፋት የገለጹ ቢሆንም በተቃራኒው ወደ 12.6 ሚሊዮን አካባቢ ወጣቶች በምርጫው ለመሳተፍ የተመዘገቡ መሆኑን ብልጽግና ፓርቲ የኢትዮጵያን ምርጫ ለመታዘዘብ ውስን ተልዕኮው ገልጿል። የፖለቲካ ፓርቲዎች የወጣቱ ድምጽ አስፈላጊ እንደሆነ የሚገነዘቡ ቢሆንም ወጣቶችን በምርጫ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለማሳተፍ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል ለማለት አይቻልም እንዲሁም የወጣቶችን ፍላጎቶች በፓርቲያቸው መርሀ ግብሮች ውስጥ አላካተቱም።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የመራጮች ምዝገባ በኢንተርኔት ለማድረግ የሚያስችሉ ልዩ አሠራሮችን ተግባራዊ ያደረገ ቢሆንም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በሚኖሩባቸው የምርጫ ክልሎች ባሉ የምርጫ ጣቢያዎች ድምጽ መስጠት ነበረባቸው። ወደ 4,075 የሚጠጉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለመምረጥ እንደተመዘገቡ ተገልጿል። ነገር ግን ለተማሪዎች በኢንተርኔት የሚደረግ የምዝገባ ሂደት የተዘጋጀ ቢሆንም ዋጋው ተመጣጣኝ እና ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ መጓጓዣ ባለመኖሩ የተነሳ በርካታ ተማሪዎች በሚኖሩበት ቦታ ወዳለ የምርጫ ክልል በመሄድ ድምጽ ለመስጥት አልቻሉም። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ስልጠና እንዲያዳርሱ ለ169 የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ዕውቅና የሰጠ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥም አብዛኛዎቹ ወጣቶችን እና ለመጀመሪያ ጊዜ ድምጽ የሚሰጡ ሰዎችን ዒላማ ያደረጉ ነበሩ። የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ወጣቶችን ዒላማ ያደረጉ በጾታ ተለይተው የተዘጋጁ ቀራረቦች አልነበሯቸውም።

በሀገሪቱ ወጣቶች ዘንድ የብሔር እና የባህል ክፍፍሎች እየጨመሩ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ የተነሱ ስጋቶችም ነበሩ። በዚህ ረገድ ብሔርን መሠረት ያደረጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች አብዛኛውን ጊዜ ወጣት አባሎቻቸው ከብሔር ጋር ግንኙነት ባላቸው ግጭቶች ውስጥ እንዲሳተፉ ሲያነሳሱ እንደሚስተዋሉ አስተያየት ሰጪዎች ገልጸዋል።

---

50 በ1987 የወጣው ሕገ መንግስት አንቀጽ 54(3)። ነገር ግን በሁሉም ብሔረሰቦች መካከል ዕኩልነትን እና አንድነትን የማስፋፋት እና "የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብትን በተመለከተ የሚነሱ ጥያቄዎች" ላይ የመወሰን ስልጠን የተሰጠው ዋነኛ አካል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው። በ1987 የወጣው የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 62(3) እና (4)።

51 ዝርዝሩ በትግራይ ክልል የሚገኙ በዚህ ምርጫ የማይሳተፉ ሁለት ልዩ የምርጫ ክልሎችን አያካትትም።

52 ሌሎቹ አራት ቋንቋዎች ኦሮምኛ፣ አፋርኛ፣ ሱማሊኛ እና ትግሪኛ ናቸው።

## የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ማካተት

ዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (International Organization for Migration) ባወጣው መረጃ መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ አራት ሚሊዮን የሚጠጉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች አሉ።[53] በሀገሪቱ ውስጥ ካለው መፈናቀል ውስጥ ወደ 82 በመቶ የሚጠጋው በግጭት የተነሳ የተከሰተ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት የአፍሪካ ህብረት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍ የማድረግ ስምምነትን (የካምፓላ ስምምነትን) (African Union Convention for the Protection and Assistance of Internationally Displaced Persons in Africa (Kampala Convention)) እ.ኤ.አ. በፌብራሪ ወር 2020 በመፈረም የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ከሀገሪቱ ሲቪክ ህይወት ውስጥ መገለላቸውን ለመፍታት የመጀመሪያውን እርምጃ ወስዷል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና ከሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ጋር ያደረጋቸውን ምክክሮች ተከትሎ ኢትዮጵያ ከገባቻቸው አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ጋር ራሷን ማጣጣም እንድትችል መመሪያ ቁ. 13/2012ን አዘጋጅቶ አጽድቋል።[54] መመሪያው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እና የመከላከያ ሰራዊት አባላት መምረጥ እንዲችሉ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙላቸው ይጠይቃል። መመሪያው ትልቅ ዓላማ ያለው እንዲሁም ጥብቅ ነው፤ በዚህ ረገድም በልዩ የምርጫ ጣቢያዎች የተመዘገቡ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ከመፈናቀላቸው በፊት በነበሩበት የምርጫ ክልል በሚካሄደው ምርጫ ላይ ድምጽ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ድንጋጌው ተጠቃሽ ነው። በሌላ በኩል መመሪያው መኖሪያቸው የማይታወቅ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የማይሸፍን በመሆኑ በመደበኛ የምርጫ ጣቢያዎች አመልክተው ለመመዝገብ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 18 እና 21 ውስጥ የተዘረዘሩትን የነዋሪነት መስፈርቶች እና የመታወቂያ ሰነዶች ማሟላት ይኖርባቸዋል። ይህ በሕግ ማዕቀፉ ውስጥ ያለ ክፍተት ተፈናቅለው በሚገኙበት ስፍራ ነዋሪነታቸውን ለማረጋገጥ አቅሙ ወይም የሕግ አቋሙ የሌላቸው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መምረጥ እንዳይችሉ ሊያደርግ የሚችል መሆኑን በመጥቀስ ኢሰመኮ ትችቱን ገልጿል።[55]

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አብዛኛዎቹን የመመሪያውን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ አልቻለም። በመሆኑም የተመዘገቡት የሀገር ውስጥ ተፈናቀዮች በቁጥር ትንሽ ነበሩ እንዲሁም አብዛኞቻቸው ሰኔ 14 ድምጽ ለመስጠት ብቁ አልነበሩም። የክልል ባለሥልጣን አካላት ተሳትፎ ያለማድረጋቸው ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች እንዳይቋቋሙ ወይም ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ተደራሽ እንዳይሆኑ እንቅፋት ሆኗል።[56] ቦርዱ ከዚህ ቀደም በነበሩ ግጭቶች የተፈናቀሉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰፈሩባቸው በአፋር፣ በድሬ ዳዋ፣ በሀረሪ፣ በጋምቤላ፣ በኦሮሚያ እና በሱማሌ ክልል የሚገኙ 427 ልዩ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን ዝርዝር ይፋ አድርጓል። ሆኖም ግን የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ለማረጋገጥ የቻለው ሰኔ 14 መራጮችን ያስተናገዱ አራት ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች ብቻ በጋምቤላ የነበሩ መሆናቸውን ነው። በሌሎች አካባቢዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የክልል ጽ/ቤቶች የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በመደበኛ የምርጫ ጣቢያዎች እንዲመዘገቡ የፈቀዱ ሲሆን ከሰፊው ህዝብ ጋር አንድ ላይ የአካባቢ ዕጩዎችን ለመምረጥ ድምጽ ሰጥተዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአማራ፣ በምዕራብ ኦሮሚያ እና በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ በማህበረሰቦች መካከል በነበሩ ግጭቶች የተነሳ በአንጻሩ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተፈናቀሉ ተጨማሪ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ፍላጎቶች እንዳያሟላ እንቅፋት የሆኑ ከሎጂስቲክስ ጋር የተያያዙ እና የተጸጥታ ተግዳሮቶች በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች ገጥመውታል።

በተጨማሪም የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በቂ የሲቪክ እና የመራጮች ስልጠና ባለማግኘታቸው የመሳተፍ መብታቸውን ለመጠቀም በበቂ ሁኔታ ዝግጁ አልነበሩም። በተመሳሳይ መልኩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መኖሪያዎች የሚገኙት መድረስ የማይቻልባቸው ቦታዎች ላይ መሆኑን እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በአጠቃላይ በይበልጥ መጠለያ እና ሌሎች ሰብአዊ ድጋፎችን በማግኘት የተጠመዱ መሆናቸውን በመግለጽ መራጮችን በማዳረስ (outreach) ስትራቴጂዎቻቸው ውስጥ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን አላካተቱም።

ልዩ የምርጫ ጣቢያዎችን በማቋቋም ዙሪያ ባሉ ያልተረጋገጡ ሁኔታዎች የተነሳ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መኖሪያ አካባቢዎች ውስጥ ያለውን ድምጽ አሰጣጥ የታዘበ የሲቪል ማህበራት ድርጅት አልነበረም። የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሳይቶች ላይ እንዲታዘብ ዕውቅና የተጠው ብቸኛው ድርጅት የሆነው ኢሰመድህ መጨረሻ ላይ ምርጫ ለመታዘብ ተልዕኮው የገንዘብ ድጋፍ ባለማግኘቱ በምርጫው ዕለት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሳይቶች ላይ ታዛቢዎችን ሳያሰማራ ቀርቷል። በሌላ በኩል በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል በኮንሶ ዞን የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መደበኛ የምርጫ ጣቢያዎች ውጭ ላይ መሰለፋቸውን የኢሰመኮ ተቆጣጣሪዎች በቀጥታ ለመታዘብ ችለዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በመደበኛ የምርጫ ጣቢያዎች የተመዘገቡ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በተመለከተ ያጠናቀረው መረጃ የለም እንዲሁም የሀገር ውስጥ ተፈናቃይ የሆኑ መራጮችን የመዘገቡ መደበኛ የምርጫ ጣቢያዎችን ዝርዝር አላጋራም። በተጨማሪም ከምርጫው በኋላ ቦርዱ በልዩ የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የተመዘገቡ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ቁጥር ወይም በእነዚህ የምርጫ ጣቢያዎች የተሰጠው ድምጽ ብዛት ምን ያህል እንደነበረ ሪፖርት አላደረገም።

## የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችን ማካተት

ኢትዮጵያ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችን ከማካተት ጋር የተያያዙ ዋና የሚባሉ ሰነዶችን እና ስምምነቶችን በሙሉ የፈረመች ሲሆን ይህም መብቶቻቸውን ለማረጋገጥ በንቃት እንድትሰራ ሀገሪቱን የሚያስገድድ ነው። በተጨማሪም ሕገ መንግስቱ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ከሌሎች ዕኩል የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የባህል መብቶች እንዳሏቸው ዕውቅና ሰጥቷል። የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ከኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ አንድ ስድስተኛውን አካባቢ ይይዛሉ፤ ነገር ግን ምንም እንኳን ቁጥራቸው ከፍተኛ ቢሆንም በምርጫ ሂደት እንዲሁም በህዝባዊ ጉዳዮች ውስጥ በጠቃላይ የሚጫወቱት ሚና አነስተኛ ነው። የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች መካተታቸውን የማረጋገጥ ዓላማ ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የአካል ጉዳተኞች ቡድኖች በደንቡ እና በአሠራሩ መካከል ክፍተት መኖሩን ይገልጻሉ።

ምንም እንኳን የአካል ጉዳት ያለባቸው ዕጩዎችን ላስመዘገቡ ድርጅቶች ተጨማሪ የምርጫ ቅስቀሳ ድጎማዎች ቢመደቡም የፖለቲካ ፓርቲዎች በፓርቲ ዝርዝሮቻቸው ውስጥ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችን በበቂ ሁኔታ አላካተቱም። ከተመዘገቡት 9,505 ዕጩዎች ውስጥ የአካል ጉዳት ያለባቸው ዕጩዎች 99 ብቻ ሲሆኑ ይህም የፖለቲካ ፓርቲዎች ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ ካስመዘገቧቸው ዕጩዎች ውስጥ 0.9 በመቶ እና ለክልል ምክር ቤት ካስመዘገቧቸው ውስጥ ደግሞ አንድ በመቶ ነው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተለያዩ የሂደቱ ምዕራፎች ላይ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ጋር ምክክሮችን በማድረግ የአካል

---

53 ‘‘የኢትዮጵያ ብሔራዊ የመፈናቀል ሪፖርት 8፣ የሳይት ግምገማ ዙር 25 እና የመንደር ግምገማ ዳሰሳ ጥናት ዙር 8፡- እ.ኤ.አ. ማርች 2021 እና አፕሪል 2021’’ (ሰኔ 23 ቀን 2013 ዓ.ም.)።

54 የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9(1) ፈራሚ ሀገራት “የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዜጋ በሆኑበት ሀገር ውስጥ በተለይም ደግሞ በህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍን እና ለመንግስት ኃላፊነት የመምረጥ እና የመመረጥ መብትን ጨምሮ ሲቪክ እና የፖለቲካ መብቶቻቸውን መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን እንዲወስዱ” ይጠይቃል።

55 የኢሰመኮን የሰኔ 7 መግለጫ ይመልከቱ።

56 ያሏቸውን የአካል ጉዳተኞች በተመለከተ ብዛታቸውን እና የሚገኙበትን ስፍራ ጨምሮ በቂ መረጃ ያቀረቡት አራት ክልሎች ብቻ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የግንኙነት አማካሪ ሶሊያና ሺመልስ ሰኔ 8 ቀን ለአሜሪካ ድምጽ ገልጸዋል።

ጉዳተኞችን በምርጫው ሂደት ውስጥ ለማካተት ያደረጋቸው ጥረቶች መኖራቸውን አስተያየት ሰጪዎች አረጋግጠዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይህን ጥረት ማድረጉ ወሳኝ ተደርጎ የሚታይ ነው። ምንም እንኳን አንዳንድ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ማህበራት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን የስልጠና ማቴሪያሎች በማዘጋጀት እና በመራጮች ስልጠና እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተሳተፉ ቢሆንም የአካል ጉዳተኞች ከነበራቸው መረጃ የማግኘት ዕድል ጋር በተያያዘ ውስንነቶች እንደነበሩ አስተያየት ሰጪዎች ገልጸዋል። የምርጫ ሕጉ ወደ ብሬል የተተረጎመ ቢሆንም የብሬል ድምጽ መስጫ ፍሬሞች (braille ballot frames) ያለመኖራቸው ማየት የተሳናቸው መራጮች ራሳቸውን ችለው ድምጽ የሚሰጡበት ሁኔታ ውስን እንዲሆን አድርጓል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በቴሌቪዥን ያስተላፋቸው ቪዲዮዎች እና ማስታወቂያዎች ላይ የምልክት ቋንቋ ጥቅም ላይ ውሏል፤ ነገር ግን የመራጮች ስልጠና የማዳረስ (outreach) እንቅስቃሴዎች በተለይም ደግሞ በብዛት የተለመደው የምልክት ቋንቋ ጥቅም ላይ የሚውልባቸው የገጠር አካባቢዎች ላይ ለሚኖሩ መስማት የተሳናቸው መራጮች ተስማሚ በሆነ መልኩ አልተከናወኑም። እንደ የኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን እና የእንባ ጠባቂ ጽ/ቤት ያሉ ባለድርሻ አካላት የመራጮች ምዝገባ እና የምርጫ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆናቸውን በተመለከተ ግምገማ ያከናወኑ ሲሆን ለበርካታ አካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዳልሆኑ ያወጧቸው ሪፖርቶች ይጠቁማሉ።

በከተማ ማዕከላት አካባቢ ላሉ አካል ጉዳተኞች መሳተፍ ቀላል የነበረ ሊሆን ቢችልም በገጠር አካባቢ የሚኖሩ አካል ጉዳተኞች ግን በቂ የመራጮች መረጃዎችን ከማግኘት፣ ከመጓጓዣ እና የመራጮች ምዝገባ እና የምርጫ ጣቢያዎች ጋር በአካል ከመሄድ አንጻር ከፍተኛ ችግሮች ነበሩባቸው።

## የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች እና የዜጎች ተሳትፎ

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ምስረታ፣ እንቅስቃሴ እና የገንዘብ ድጋፍ የሚያስተዳድረው ሕግ ላይ አዳዲስ ማሻሻያዎች ከተደረጉበት ወዲህ የሲቪል ምህዳሩ በመስፋቱ ሁሉም ዓይነት አስተያየት ሰጪዎች ያደነቁት ጉዳይ ነው። የሲቪል ማህበራት አዋጁ ከ2005 ዓ.ም. ጀምሮ የነበሩ ገደቦችን በከፍተኛ ሁኔታ ያቀለለ ነው። የቀድሞው ሕግ (ብዙዎች "ጨቋኝ" ብለው የሚገልጹት ሲሆን) የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የውጭ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት እና ዲሞክራሲን፣ አስተዳደርን እና ሰብአዊ መብቶችን ከማስፋፋት እና ከማስጠበቅ ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን እንዳይችሉ የሚያደርጉ ገደቦች ያሉት ነበር።

ነገር ግን ለዓመታት የቆየው ጭቆና እና የፖለቲካ ምህዳር መጥበብ በሲቪክ ምህዳሩ ላይ ከፍተኛ ጠባሳ ትቶ ያለፈ ከመሆኑም በላይ ዜጎች በሲቪል ማህበራት ላይ ያላቸውን እምነት ሸርሽሯል እንዲሁም የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ከምርጫ ጋር በተያያዙ እንቅስቃሴዎች፣ በዴሞክራሲ፣ በሰብአዊ መብቶች እና ከሰብአዊ እርዳታ ውጭ በሆኑ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ለመሥራት ያላቸውን ውስጣዊ አቅም አዳክሞታል። በ2012 ዓ.ም. የሲዳማ ህዝበ ውሳኔን ከመታዘብ ጋር በተያያዘ ካደረጉት ውስን እንቅስቃሴ ውጭ በዚህ ምርጫ ላይ የተሳተፉ ሲቪክ ቡድኖች በምርጫ ሂደት ውስጥ ከመሳተፍ ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀደም በጣም አነስተኛ ልምድ ወይም ተቋማዊ ትውስታ የነበራቸው ወይም ከነጭራሹ ያልነበራቸው ናቸው።

በርካታ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ምንም እንኳን የልምድ እጥረት ቢኖርባቸውም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያስተላለፈውን ጥሪ በመቀበል በመላው ሀገሪቱ የመራጮች ስልጠና እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን ዕውቀና እንዲሰጣቸው አመልክተዋል። በመጨረሻ በድምሩ 167 ድርጅቶች የመራጮች ስልጠና እንዲሰጡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዕውቅና የተሰጣቸው ሲሆን ወደ 45 የሚጠጉ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ደግሞ ምርጫውን ለመታዘብ ዕውቅና አግኝተዋል። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች በዕውቅና አሰጣጥ ሂደቱ ውስጥ በተለይም ደግሞ ባጆችን ከመቀበል ጋር በተያያዘ መዘግየቶች እንዳጋጠሟቸው ገልጸዋል። አብዛኞቹ አስተያየት ሰጪዎች ባጆች በሙሉ የተሰጡት አዲስ አበባ በሚገኘው የቦርዱ ማዕከላዊ ጽ/ቤት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የአቅም ውስንነት፣ የቅልጥፍና ማነስ እና የተማከለ የውሳኔ አሰጣጥ የነበረበት መሆኑን ገልጸዋል። መዘግየቱ ከተጣበበው የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ጋር ተደምሮ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የመራጮች ስልጠና ለመስጠት እና/ወይም ታዛቢዎችን ለመመልመል፣ ለማሰልጠን እና ለማሰማራት ያላቸው አቅም ይበልጥ ውስን እንዲሆን አድርጓል። በመሆኑም መራጮችን ይበልጥ ለማዳረስ ዕድሉን ይሰጡናል ብለው ተስፋ በማድረግ አስተያየት ሰጪዎች ማራዘሚያዎቹን የተቀበሏቸው በደስታ ነበር።

ከምርጫ ጋር በተያያዙ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ዕውቅና የተሰጣቸው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ያሉ ቢሆንም እንደዚያ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ሀብት እና ገንዘብ ለማሰባሰብ የቻሉት ግማሾቹ ብቻ ናቸው። ከሞላ ጎደል ሁሉም አስተያየት ሰጪዎች ያለባቸው ዋነኛ ተግዳሮት የገንዘብ ድጋፍ እጥረት እንደሆነ የገለጹ ሲሆን የኮቪድ-19 ወረርሽኙ እና ያልተረጋጋ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ መኖሩ ችግሩን ይበልጥ ያባባሱት ከመሆኑም በላይ የገንዘብ ድጋፍ ላገኙት የሲቭል ማህበረሰብ ድርጅቶችም እንኳን ገንዘቡ ሳይለቀቅላቸው እንዲቆይ ምክንያት ሆነዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከውጭ ለጋሾች ያገኘውን የገንዘብ ድጋፍ ከግምት ውስጥ በማስገባት በርካታ ቡድኖች ከቦርዱ የሚመጣ ለመራጮች ስልጠና የሚውል የገንዘብ ድጋፍ ይኖራል ብለው ጠብቀው ነበር።

አብዛኛዎቹ ከሲቪል ማህበራት ድርጅት የመጡ አስተያየት ሰጪዎች በነጻነት እና ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና ከሌሎች ኃላፊዎች ጋር በጥሩ ሁኔታ ተቀናጅተው ለመስራት መቻላቸውን ገልጸዋል። ነገር ግን ተልዕኮው ራስን በራስ ሳንሱር የማድረግ ሁኔታዎች እንደነበሩ ከአንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች መረጃዎች የደረሱት ሲሆን እንደተባለው ከሆነ ይህ አንዳንድ የሲቪል ማህበረሰሰብ ድርጅቶች አሁን ያለው መንግስት ገደቦችን በማቅለሉ ምስጋናቸውን ለመግለጽ እንዲሁም ሌሎች ደግሞ የፖለቲካ በቀል ይኖራል በሚል ፍራቻ ያደረጉት ነበር።

# በዜጎች የሚደረግ ምርጫ መታዘብ

የሲቪል ማህበራት የፖለቲካ ምህዳር ይበልጥ መስፋቱን በሚያንጸባርቅ ሁኔታ በሀገሪቱ ዙሪያ በርካታ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የረጅም ጊዜ እና የአጭር ጊዜ የምርጫ ታዛቢዎችን በማሰማራት ጠቅላላ እንዲሁም በዘርፍ የተለየ የመታዘብ ሥራ ሠርተዋል። ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በድምሩ ለ45 የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በዜጋ ምርጫ ታዛቢነት ዕውቅና ሰጥቷል እንዲሁም በድምሩ ከ32 የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የመጡ 47,932 የዜጋ ታዛቢዎች በምርጫው ዕለት ተሰማርተዋል።[57]

ከመላው ኢትዮጵያ የተወጣጡ 175 የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን እና ህብረቶችን በስሩ ያቀፈ እናት ድርጅት የሆነው የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ በዚህ ረገድ ከተሠሩት ሥራዎች ውስጥ ተጠቃሽ ነው። የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ የመራጮች ምዝገባን ጨምሮ በአጠቃላይ የምርጫ ሂደቱ ውስጥ ከ100 በላይ የረጅም ጊዜ ታዛቢዎችን መልምሎ፣ አሰልጥኖ አሰማርቷል። ለሰኔ 14ቱ ምርጫ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ ከ2,000 በላይ የሰለጠኑ እና ዕውቅና የተሰጣቸው ታዛቢዎችን አሰማርቷል እንዲሁም የተራቀቀ ብሔራዊ የመረጃ ማዕከል አቋቁሟል። የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በኮድ በተጻፈ አጭር የጽሁፍ መልዕክት አማካኝነት መደበኛ በሆነ መልኩ በየጊዜው ሪፖርቶችን ወደ ኮምፒውተር የመረጃ ቋቱ ልከዋል። የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ ከምርጫው ቀን አስቀድሞ የመራጮች ምዝገባን የተመለከተ ዝርዝር ሪፖርት አውጥቷል። ጥምረቱ በምርጫው ዕለት ዕኩለ ቀን ላይ የምርጫ ጣቢያዎች የተሰናዱበትን መንገድ በዝርዝር የሚያስረዳ ሪፖርት አውጥቷል እንዲሁም ከምርጫው ቀን በኋላ ብዙም ሳይቆይ የድምጽ አሰጣጥን እና ቆጠራን በተመለከተ የመጀመሪያ ሪፖርቱን አውጥቷል።[58]

በርካታ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በዘርፍ የተለዩ የመታዘብ ሥራዎችን ሠርተዋል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን በአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ እና ተደራሽነት ላይ አተኩሯል። በአራት ክልሎች እና በአዲስ አበባ 50 አካል ጉዳተኞችን በረጅም ጊዜ ታዛቢነት እና 100 አካል ጉዳተኞችን በምርጫ ቀን ታዛቢነት አሰማርቷል እንዲሁም አካል ጉዳተኞች በምርጫው ሂደት ውስጥ ስለተጫወቱት ሚና መጠነ ሰፊ ሪፖርት አውጥቷል። የኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያ ሴቶች ማህበር በምርጫ ሂደት ውስጥ በሴቶች ላይ በሚፈጸሙ ጥቃቶች ላይ ክትትል አድርጓል። 150 ሴቶችን በረጅም ጊዜ የምርጫ ታዛቢነት እና 130 ሴቶችን በምርጫ ቀን ታዛቢነት አሰማርቷል እንዲሁም የሠሩትን የመታዘብ ሥራ የተመለከተ ሪፖርት አውጥቷል።[59] የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን የተደራጀውን የሰራተኛ ኃይል በመወከል ምርጫውን እንዲታዘቡ 1,130 ታዛቢዎችን አዲስ አበባን ጨምሮ በ25 ከተሞች አሰማርቷል።[60] በተጨማሪም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ (ኢ.ሰ.መ.ጉ.) የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የምርጫ ጣቢያዎችን ለመታዘብ ዕቅዶችን አዘጋጅቷል።

በምርጫው ዕለት ከነበሩት ታዛቢዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ የተለያዩ የሴቶች እና የወጣቶች ማህበራት እና ፌዴሬሽኖች የተሰማሩ ነበሩ። እነዚህ አካላት በምርጫው ዕለት በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት ላይ ያተኮሩ ነበሩ እንዲሁም ጥብቅ ስልቶችን ተግባራዊ ያደረጉ አልነበሩም። እነዚህ ሥራዎች የገንዘብ ድጋፋቸውን ከየት እንዳገኙ ሁል ጊዜም ግልጽ ነበር ለማለት አይቻልም እንዲሁም የአባልነት ክፍያዎችን እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎችን እንደሆነ የሚጠቀሙት የገለጹ አካላት ነበሩ። ከዚህ ቀደም የወጣቶች እና የሴቶች ማህበራት በጥቅሉ ከመንግስት ጋር ግንኙነት ያላቸው እንደነበሩ እና ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻም ሆነ ገለልተኛ እንዳልነበሩ አንዳንድ ባለሞያዎች ጠቁመዋል።

ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዕውቅና አሰጣጥ ሂደት ጋር በተያያዘ ተግዳሮቶች እንደገጠሟቸው የታዛቢዎች ቡድኖች የገለጹ ቢሆንም አንድ ጊዜ ዕውቅና ከተሰጣቸው በኋላ ግን የምርጫ ጣቢያዎች በጥቅሉ ያለገደብ ለምርጫ ታዛቢዎች ተደራሽ ነበሩ። ሆኖም ግን መጀመሪያ ላይ በምርጫ ጣቢያዎች ከመታዘብ ጋር በተያያዘ ታዛቢዎች ተግዳሮቶች አጋጥመዋቸው የነበሩበት አንደንድ ሁኔታዎች አልፎ አልፎ ነበሩ። የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ እንደገለጸው ከሆነ ከድርጅቱ ታዛቢዎች ውስጥ ሦስት በመቶው ምንም እንኳን ባጃቸውን ያቀረቡ ቢሆንም እንዲታዘቡ ልተፈቀደላቸውም። የኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያ ሴቶች ማህበርም እንዲሁ አንዳንድ ታዛቢዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች ከመከፈታቸው በፊት በሚገቡበት ወቅት ተግዳሮቶች አጋጥመዋቸው እንደነበር ገልጿል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዕውቅና ከልክሏል። ኢሰመኮ ከሰብአዊ መብቶች ጋር በተያያዘ በምርጫ ውስጥ የሚጫወተው ሚና እንዳለ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቢገነዘብም ኢሰመኮ ከፊል-መንግስታዊ ተቋም እንደመሆኑ መጠን እንደ ታዛቢ ዕውቅና ለማግኘት መስፈርቱን አያሟላም በማለት ወስኗል። እንደዚያም ሆኖ ኢሰመኮ 100 ታዛቢዎችን በማሰማራት የምርጫውን ክንውን በተመለከተ በሰብአዊ መብቶች ላይ የተኮረ ሪፖርት አውጥቷል።[61]

57 ዕውቅና ከተሰጣቸው 45 የሀገር ውስጥ ታዛቢ ድርጅቶች ውስጥ አምስቱ ግለሰብ ታዛቢዎችን አላስመዘገቡም እንዲሁም ሌሎች ስምንት ድርጅቶች ደግሞ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባጆችን የሰጣቸው ቢሆንም ታዛቢዎቻቸውን አላሰማሩም።

58 የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫን *የመጀመሪያ መግለጫ* ይመልከቱ።

59 የኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያ ሴቶች ማህበርን *የመጀመሪያ መግለጫ* ይመልከቱ።

60 የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽንን *የመጀመሪያ መግለጫ* ይመልከቱ።

61 https://english.alaraby.co.uk/news/ethiopia-rights-commission-says-no-massive-poll-abuses

## የምርጫው ቀን

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና በስፋት የሚስተዋሉ የጸጥታ ችግሮች በመኖራቸው የተነሳ የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው በምርጫው ዕለት የአጭር ጊዜ ታዛቢዎችን አላሰማራም። ነገር ግን የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው የምርጫ እና አህጉራዊ ባለሞያዎች በምርጫው ዕለት እንዲሁም ከምርጫው በፊት እና በኋላ ለአጭር ጊዜ አዲስ አበባ ነበሩ።

ከምርጫ ታዛቢ ዜጎች፣ ከዓለም አቀፍ ታዛቢዎች፣[62] ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪል ማህበራት ድርጅቶች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ምክክሮችን መሠረት በማድረግ የምርጫው ዕለት በአብዛኛው ሰላማዊ እና የህዝብን ደህንነት ለማስጠበቅ የተቀመጡ የኮቪድ-19 ፕሮቶኮሎችን በተወሰነ መልኩ ብቻ ከመከተላቸው ውጭ የምርጫ ኃላፊዎች በጥቅሉ ሥነ--ሥርዓቶችን ያከበሩበት ነበር። በምርጫ ጣቢያዎች ዙሪያ አንዳንድ ግጭቶች እንደነበሩ የገለጹ አንዳንድ ይፋዊ ሪፖርቶች የነበሩ ቢሆንም አልፎ አልፎ የተከሰቱ ነበሩ። በተጨማሪም በመላው ሀገሪቱ የአንዳንድ የምርጫ ማቴሪያሎች እጥረት እንደነበር የገለጹ ሪፖርቶች የነበሩ ሲሆን በዚህም የተነሳ የምርጫ ጣቢያዎች ያልተከፈቱባቸው አንዳንድ አጋጣሚዎች ነበሩ። በምርጫው ዕለት ከሠዓት በኋላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ድምጽ የመስጠት ሂደቱ በሦስት ሠዓታት ተራዝሞ እስከ ምሽቱ 3 ሠዓት ድረስ እንደሚቀጥል አስታውቆ ነበር። መራጮች ሁለት የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለማስገባት ይወስድባቸው በነበረው ጊዜ እና ለአንድ ምርጫ ጣቢያ ተቀምጦ የነበረው ከፍተኛ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር (1,500) በአንጻሩ ከፍ ያለ በመሆኑ የተነሳ የድምጽ መስጫ ሠዓቱ መራዘሙ ጥሩ ተቀባይነት ያገኘ እንደነበረ ለማስተዋል ተችሏል።

የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው በክልሎች ካስቀመጣቸው ብሔራዊ ሠራተኞች እንደተገኙት መረጃዎች ከሆነ ከኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ፣ ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያ ሴቶች ማህበር፣ ከሴቶች ፌዴሬሽን እና ከኢሰመጉ የመጡ የሲቪል ማህበራት ታዛቢዎች ከኦሮሚያ እና ከጋምቤላ በስተቀር በአብዛኛዎቹ ክልሎች ውስጥ ተገኝተው ነበር። በርካታ የዜጋ ታዛቢዎች ግዴታቸውን እንዳይወጡ በጸጥታ ኃይሎች ተከልክለዋል እንዲሁም በአማራ ክልል አንዳንዶቹ ታስረዋልም ጭምር።

ከምርጫው ቀን በፊት ሕጉ በሚጠይቀው መሠረት ለዕጩ/ለፓርቲ ወኪሎች ይፋዊ የምርጫ ጣቢያ የውጤት ቅጾች ቅጂ ይሰጣቸዋል ወይስ አይሰጣቸውም የሚለውን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተገኙት መረጃዎች እርስ በእርስ የሚጋጩ ነበሩ። የምርጫው ቀን ማታ ላይ የውጤት ቅጾችን በአብዛኛው ማግኘት ባለመቻላቸው የፓርቲ ወኪሎች ፎቶዎችን በመጠቀም የራሳቸውን ማስረጃ መያዝ እንደነበረባቸው ፓርቲዎች ገልጸዋል።[63]

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ ጣቢያዎች እና በቆጠራ ማዕከላት የነበሩ ግድፈቶችን በተመለከተ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ቅሬታዎች ቀርበውለታል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መደበኛ በሆነ መልኩ በየጊዜው በሰጣቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎች አማካኝነት በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች ያጋጠሙ በርካታ ተግዳሮቶችን የገለጸ ሲሆን ለዚህም ምስጋና ይገባዋል። የምርጫ ማቴሪያሎች ዘግይተው መድረስ እና የምርጫ ጣቢያዎች ዘግይተው መከፈት፣ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች እጥረት፣ የሰልፎች መርዘም እና ከጸጥታ ጋር ግንኙነት ያላቸው ችግሮች ከብዙ በጥቂቱ ከቀረቡት ቅሬታዎች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው።

## የድምጽ ቆጠራ እና ውጤት ማሳወቅ

የምርጫ ውጤቶች በመጀመሪያ የፓርቲ እና የዕጩ ተወካዮች በተገኙበት በምርጫ ክልል ደረጃ ተቆጥረዋል፤ ከዚያም ይፋ ከመደረጋቸው በፊት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተጣርተው ተረጋግጠዋል። ሕጉ የተረጋገጡ (official) ውጤቶች ከምርጫው ቀን በኋላ ከ20 ቀናት በላይ ሳይቆዩ ይፋ መደረግ እንዳለባቸው ያዛል (ያልተረጋገጡ /unofficial/ ውጤቶች ግን በመታየት ላይ ያሉ ቅሬታዎች እስከሌሉ ድረስ ከዚያ አስቀድመው ሊወጡ ይችላሉ) ። ምንም እንኳን እስከ ሰኔ 30 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 51 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና 26 የክልል ምክር ቤት የምርጫ ክልሎችን ጨምሮ የ77 የምርጫ ክልሎችን ውጤት ያሳወቀ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ውጤቶች በይፋ የተገለጹት ሐምሌ 3 ነበር። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የተመረጡ መገናኛ ብዙሀን በተገኙበት ውጤት የማሳወቅ ሥነ-ሥርዓት አድርጓል። ከዚያም ብዙ ሳይቆይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተለያዩ ዕጩዎች ያገኟቸውን ድምጾች ብዛት ወይም በምርጫ ክልል ደረጃ ውድቅ የተደረጉ ድምጾች ብዛትን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃዎችን ይፋ ማድረግ ጀምሯል።[64]

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በክልል ደረጃ እንጂ በብሔራዊ ደረጃ ከተመዘገቡ ሰዎች ውስጥ ምን ያህሉ እንደመረጡ የሚያሳይ አሀዝ አላወጣም። በክልል ደረጃ ከተመዘገቡ ሰዎች ውስጥ የመረጡት በአዲስ አበባ 99 በመቶ፣ በአፋር 97 በመቶ፣ በኦሮሚያ 96 በመቶ እና በድሬ ዳዋ 95 በመቶ ነበር። ከተመዘገቡ ሰዎች ውስጥ የመረጡት 55 በመቶው ከነበረበት ከቤኒሻንጉል-ጉሙዝ በስተቀር በሁሉም ሌሎች ክልሎች ከተመዘገቡት ሰዎች ውስጥ የመረጡት ሰዎች 90 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ነበር። እነዚህ ከተመዘገቡ መራጮች ውስጥ ምን ያህሉ እንደመረጡ የሚያሳዩ ቁጥሮች ከምርጫው ቀን አስቀድመው የመራጮች ምዝገባ ለሚያደርጉ ሀገራትም እንኳን ቢሆን በጣም ከፍተኛ በመሆናቸው ስለ ድምጽ አሰጣጡ ትክክለኛነት ጥያቄ የሚያስነሱ ናቸው።[65] በ2002 እንዲሁም በ2007 የተደረጉት እና በስፋት የተተቹት ምርጫዎች ላይ በተመሳሳይ መልኩ ኢትዮጵያ ያመዘገበችው ከ90 በመቶ በላይ የሆነ ተመዝግበው የመረጡ ሰዎች ቁጥር ነበር።[66]

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ በስልጣን ላይ ያለው ብልጽግና ፓርቲ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውጤት ካወጣባቸው 425 ወንበሮች ውስጥ 410 ወንበሮችን ያሸነፈ ሲሆን አብን አምስት ወንበሮችን እና ኢዜማ አራት ወንበሮችን አሸንፈዋል፣ የጌዴኦ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሁለት ወንበሮችን አሸንፏል እንዲሁም በኦሮሚያ ሦስት እና በአዲስ አበባ አንድ የግል ዕጩዎችን ጨምሮ አራት የግል ዕጩዎች በየምርጫ ክልላቸው አሸንፈዋል። በመሆኑም ብልጽግና ፓርቲ መንግስት ለመመስረት ከሚያስፈልገው 274 ወንበሮች በላይ አሸንፏል። በተመሳሳይ መልኩ በክልል/በከተማ ምክር ቤት ምርጫዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የ1,664 ወንበሮችን ውጤት ያወጣ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 1,625 ወንበሮን ወይም ወደ 98 በመቶ አካባቢውን ያሸነፈው ብልጽግና ፓርቲ ነው። ሌሎች ፓርቲዎች በድምሩ 39

---

62 ለምሳሌ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ እና የኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያ ሴቶች ማህበር የዜጋ ታዛቢዎችን እንዲሁም የአፍሪካ ህብረት ዓለም አአቀፍ ታዛቢዎችን የመጀመሪያ መግለጫዎች ይመልከቱ።

63 አዋጅ ቁጥር 1162/2011ን ይመልከቱ፤ አንቀጽ ቁ. 60(3)።

64 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ድረገጽ ይመልከቱ።

65 ለምሳሌ ጋና እ.ኤ.አ. 2020 ላይ ያደረገችው ምርጫ ላይ የነበረው ተመዝግበው የመረጡ መራጮች መጠን ወደ 80 በመቶ አካባቢ ነበር።

66 የዓለም አቀፉን የዴሞክራሲ እና ምርጫ ድጋፍ ተቋም (International IDEA) ተመዝግበው የመረጡ መራጮች ዳታቤዝ ይመልከቱ።

የክልል/የከተማ ምክር ቤት ወንበሮችን ያሸነፉ ሲሆን ከእነሱም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡- በአማራ ክልል አብን ያሸነፋቸው 13 ወንበሮች፤ ኢዜማ በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል ያሸነፋቸው 10 ወንበሮች፤ የጋምቤላ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ በጋምቤላ ያሸነፋቸው ሰባት ወንበሮች፤ የጌዴኦ ህዝብ ድርጅት በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል ያሸነፋቸው ስድስት ወንበሮች እና የአአርጎባ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት በአፋር ክልል ያሸነፋቸው ሦስት ወንበሮች።

## በምርጫ ሂደት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች

በምርጫ አዋጁ የተዘረጋው የኢትዮጵያ የምርጫ አለመግባባቶች አፈታት መዋቅር ውስብስብ እና የሚከተሉትን ያካተተ ነው፡- ራሱን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን፣ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን፣ አጣሪ ኮሚቴዎችን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ጉባዔን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ መድረኮችን እና ፍርድ ቤቶችን። አለመግባባቶች የሚፈቱባቸው እነዚህ ዘዴዎች ስልጣናቸው እርስ በእርስ የሚደራረብበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ አንድ አለመግባባት ከአንድ በላይ በሆኑ መድረኮች ሊፈታ ይችላል። ፈቃደኝነትን መሠረት ካደረጉ አማራጭ ያለመግበባት አፈታት ዘዴዎች አንስቶ በክልል እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች እስከሚታዩ ክርክሮች የሚደርሱ የተለያዩ አማራጮች አሉ።[67] በተግባር ሲታይ ግን የምርጫ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓቱ በምርጫ አዋጁ ውስጥ የታሰበለትን ዓላማ ከማሟላት አንጻር ብዙ ክፍተቶች ታይተውበታል።

የምርጫ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ ንዑስ ሕጎች አስፈላጊ ነበሩ። የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን የሚመለከት መመሪያ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የጸደቀ ሲሆን ይህም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በምርጫ ጣቢያዎች እና በምርጫ ክልል እና በክልል ደረጃ እንዲቋቋሙ የሚጠይቅ ነው። የታሰበ የነበረው የዕጩዎች ምዝገባ ከመጀመሩ አስቀድሞ ተቋቁመው በዕጩዎች ምዝገባ፣ በመራጮች ምዝገባ እና በድምጽ አሰጣጥ እና በድምጽ ቆጠራ ዙሪያ ቅሬታዎችን እንዲቀበሉ ነበር። ነገር ግን በመላው ሀገሪቱ በጣት የሚቆጠሩ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ብቻ በመቋቋማቸው የተነሳ ቅሬታ ያላቸው ግለሰቦች እና ፓርቲዎች መፍትሄ ለማግኘት ጉዳያቸውን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፍተኛ አከላት ለማቅረብ ተገደዋል። የአርጎባ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ከመራጮች ምዝገባ ጋር በተያያዘ የሕግ ጥሰቶች ተፈጽመዋል በማለት ሰኔ 2013 በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ላይ ክስ መስርቷል። ፍርድ ቤቱ ግን በመጀመሪያ ወደ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ መሄድ ነበረበት በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል። የድህረ-ምርጫ ቅሬታ አቅራቢዎችም እንዲሁ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ፋንታ ጉዳያቸውን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና መሥሪያ ቤት በማቅረባቸው የተነሳ ቅሬታዎችን ከማቅረብ ጋር በተያያዘ ተመሳሳይ ችግሮች የገጠሟቸው መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን የምርጫ አለመግባባት አፈታት ሥነ-ሥርዓት በተመለከተ ቅሬታ ሰሚ ክፍል ማቋቋምን ያካተተ ረቂቅ መመሪያ ሳይጸድቅ ቀርቷል። አለመግባባቶች የሚስተናገዱበት ግልጽ ሥነ--ሥርዓቶች ባለመኖራቸው የተነሳ ኢ-መደበኛ መፍትሄዎች ተዘጋጅተው ነበር። በሱማሌ ክልል ውጫዊ ባለሞያዎችን እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሠራተኞችን ያካተተ ከመራጮች ምዝገባ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን የሚመረምር አጣሪ ጉባዔ ተቋቁሟል። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውስጥም እንዲሁ የድህረ-ምርጫ ቅሬታዎችን ተቀብሎ የሚመረምር "የባለሞያዎች ኮሚቴ" ተቋቁሟል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በወሰናቸው ውሳኔዎች ላይ ለፍርድ ቤት የቀረቡት በርካታ ክሶች የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባን የተመለከቱ ነበሩ። አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሚዛናዊ እንዲሆን ሁለቱም ወገኖች ጉዳያቸው ሊሰማ እና ውሳኔ ሲጪዎቹ ከአድሎ ነጻ ሊሆኑ ይገባል። ከኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ህብረት፣ ከኦሮሞ አቦ ነጻነት ግንባር እና ከኦሮሞ ነጻነት እና አንድነት ግንባር ጋር በተደረጉት ክርክሮች ፍርድ ቤቶቹ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንደገና ለመመዝገብ የቀረቡትን ማመልከቻዎች ውድቅ ያደረገው ሚዛናዊ የሆኑ ሥነ-ሥርዓቶችን ተከትሎ አይደለም ብለው ወስነዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የአባላት ፊርማዎቹ ተቀባይነት የሌላቸው እንደሆኑ የወሰነው ለባለጉዳይ ወገኖቹ ሳያሳውቅ እና መልስ እንዲሰጡ ዕድሉን ሳይሰጣቸው ነው። በምዝገባ ዙሪያ የተፈጠሩት አለመግባባቶች በጊዜ ብዛት የተጓተቱ ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያለማድረጉ ችግሩን ያባባሰው ሲሆን ይህም ባለጉዳይ ወገኖቹ በምርጫው ላይ ለመሳተፍ ዕድሉን ማግኘትን ጨምሮ በጊዜው ውጤታማ የሆነ ውሳኔ እንዳያገኙ ምክንያት ሆኗል።

የፓርቲዎች ጠቅላላ ጉባዔዎችን ተቀባይነት (ኦነግ፤ አንድ ኢትዮጵያ ፓርቲ)፤ በእስር ላይ የሚገኙ ዕጩዎን ምዝገባ (ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ)፤ የምርጫ ክልሎችን ድንበር አወሳሰን (ሞቻ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ)፤ በመራጮች ምዝገባ ላይ የነበሩ ግድፈቶችን (አርጎባ ፓርቲ)፤ የክልል እና ሀገር አቀፍ ፓርቲዎችን ዕኩል ያለማየትን (ጋሞ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ)፤ እና ለሀረሪ ክልል ምርጫ በመላ ሀገሪቱ ድምጽ መሰጠቱን (የሀረሪ ብሔራዊ ጉባዔ) ጨምሮ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔዎች ላይ የተነሱ ሌሎች የሕግ ክርክሮችም ነበሩ። ከእነዚህ ክሶች ውስጥ አራቱ አሸንፈዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔዎቹን ከማክበር ጋር በተያያዘ አላስፈላጊ መዘግየቶች የታዩበት ሲሆን በተለይም ደግሞ ከባልደራስ ጋር በነበረው ክርክር ቅሬታ አቅራቢዎቹ እርምጃ እንዲወሰድ ለማስገደድ ከፍርድ ቤቱ ተጨማሪ የአፈጻጸም ውሳኔ ማስሰጠት ነበረባቸው።

ከ201 የምርጫ ክልሎች ጋር የተያያዙ መደበኛ ቅሬታዎች ከ30 የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል ዕጩዎች እንደቀረቡለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ገልጿል።[68] በእነዚህ ቅሬታዎች የተነሳም የዘጠኝ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫዎች ውጤት ተሰርዞ ምርጫዎቹ እንደ አዲስ እንዲደረጉ ለጳጉሜ 1 ቀን ተቆርጦላቸዋል።

---

67 የክልል እና ፌዴራል ፍርድ ቤቶች የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ አንድ ወር አስቀድሞ ጀምረው ለምርጫ እንደተመደቡ ችሎቶች ተሰይመዋል። ከምርጫ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች በፍጥነት ውሳኔ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የዳኝነት ሥርዓቱ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በፍርድ ቤት የሚታዩበት የሥነ-ሥርዓት እና ማስረጃ ደንብ ያዘጋጀ ሲሆን ይህም መደበኛዎቹ የፍትሐ ብሔር ደንቦች ከምርጫ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆኑ አድርጓል። የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ደንቡን አላጸደቀውም።

68 የቅሬታዎቹ ፍሬ ነገር የተለያየ የነበረ ሲሆን አብዛኛዎቹ ውጤት እንዲሰረዝ የሚጠይቁ ነበሩ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቅሬታዎቹን በመገምገም እንዲያግዙት ከሦስት ውጫዊ የሕግ ቢሮዎች ጋር ውል ፈርሟል። ይህ ሰነድ በተጻፈበት ወቅት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ውሳኔዎች በመቃወም የቀረቡ ክሶች ልነበሩም።

# ምክረ-ሀሳቦች

ምንም እንኳን ምርጫ 2013 በከፍተኛ ሁኔታ የተገደበ የፖለቲካ ምህዳር፣ ተሳትፎ እና ፉክክር የነበረበት ቢሆንም ኢትዮጵያ ይበልጥ ግልጽነት የሰፈነበት፣ አካታች እና አሳታፊ ምረጫ የማድረግ አዲስ ጉዞ እንድትጀምር ዕድል የሚሰጥ ነው። የፖለቲካ እና የሲቪክ ምህዳሩን በማስፋት ረገድ አዎንታዊ እርምጃዎች የተወሰዱ ቢሆንም ለመምረጥ ብቁ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በሙሉ መምረጥ እንዲችሉ እንዲሁም ከዚያ ሰፋ ባለ መልኩ ደግሞ ህዝቡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና በምርጫ ሂደት ላይ ያለውን ዕምነት ለመገንባት ይበልጥ ተጋግዞ መሥራት ያስፈልጋል።

በዓለም አቀፍ ትብብር መንፈስ የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው በኢትዮጵያ ውስጥ ለወደፊቱ የሚደረጉ ምርጫዎችን ለማሻሻል የሚከተሉትን 39 ምክረ-ሀሳቦች ያቀርባል፡-

## የሕግ ማዕቀፍ

### ከአጭር ጊዜ አንጻር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ጊዜውን በጠበቀ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ፣ ከምርጫ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችን መፍቻ ዘዴዎችን ማቀላጠፍ እና በውሳኔ አሰጣጥ ረገድ ፍትሀዊነትን እና ከአድሎ ነጻ መሆንን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥነ-ሥርዓቶችን ሥራ ላይ ማዋል አለበት። በተጨማሪም ቅሬታዎችን የማስተናገድ እና ከምርጫ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችን የመፍታት ሂደቱ ይበልጥ ተጠያቂነት እና ግልጽነት ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው የተለየ ቅሬታ ሰሚ ክፍል በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውስጥ ሊቋቋም ይገባል።

### ከረጅም ጊዜ አንጻር

የምርጫ ሕጉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያዎች በሁሉም ይፋዊ የሥራ ቋንቋዎች ይበልጥ በስፋት ሊሰራጩ ይገባል እንደዲሁም ከምርጫ አዋጁ ስር ያሉ መመሪያዎች የተሟሉ እና የተጠናቀሩ ሊሆኑ ይገባል።

ከምርጫ ቅስቀሳ ጋር በተያያዘ ዕኩልነትን እና ፍትሀዊነትን ይበልጥ ማስፋፋት እንዲሁም ግንኙነት ያላቸው መረጃዎችን ህዝቡ ማግኘት እንዲችል በማድረግ ተጠያቂነትን ማስፋፋት የሚሉትን ዓላማዎች ለማሳካት በምርጫ ቅስቀሳ ዙሪያ ያሉ ድንጋጌዎችን በማሻሻል የምርጫ አዋጁ ሊሻሻል ይገባል።

ሠራተኞችን፣ ቁሳቁሶችን፣ መሳሪያዎችን፣ ግዢዎችን፣ ፈቃዶችን እና ሌሎች እርምጃዎችን ጨምሮ የመንግስት ሀብቶችን በስልጣን ላይ ላሉ አካላት ከምርጫ አንጻር ጥቅም በሚያስገኝ መልኩ መጠቀምን በግልጽ በሚከለክል እና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ለዐቃቤ ሕጎች እና ለፍርድ ቤቶች ተገቢውን ስልጣን መስጠትን ጨምሮ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስፈጸም የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን በሚያስቀምጥ መልኩ የሕግ ማዕቀፉ ሊሻሻል ይገባል።

የዕጩዎችን ያለመከሰስ መብት የሚመለከቱ የሕግ ድንጋጌዎች ጥብቅ በሆነ መልኩ ሊከበሩ ይገባል እንዲሁም ዕጩዎችን በፖለቲካ የተነሳ ከሚፈጸም እና በሌላ መልኩ ሕገ ወጥ ከሆነ እስር ለመጠበቅ የሚያስችሉ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል። ዕጩዎች የምርጫ ሂደቱን ለማወክ፣ በመራጮች መብቶች ጣልቃ ለመግባት ወይም ለወንጀል ድርጊቶች ተጠያቂነት ከመሆን ለማምለጥ ድንጋጌዎችን እንዳይጠቀሙ ለመከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎች ሊቀመጡ ይገባል።

የሀገር አቀፍ እና የክልል የፖለቲካ ፓርቲዎች መብቶች እና ግዴታዎች ዳኞች ትርጓሜ እንዲሰጡባቸው ከመተው ይልቅ በምርጫ አዋጁ እና ደንቦች ውስጥ በግልጽ ሊቀመጡ ይገባል።

## የምርጫ አስተዳደር

### ከአጭር ጊዜ አንጻር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከድምጽ ቆጠራ በኋላ የምርጫ ጣቢያ የውጤት ማሳወቂያ ቅጾች የተረጋገጡ ቅጂዎች ለፓርቲዎች/ለዕጩዎች ወኪሎች እንዲሰጡ የሚያስገድዱ የሕግ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለበት። ግልጽነትን ይበልጥ ለማሻሻል እና መራጮች በምርጫ ላይ ያላቸውን የመተማመን ስሜት ለማሳደግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ውጤቶችን በምርጫ ስፍራ ደረጃ ከፋፍሎ ጊዜውን በጠበቀ መልኩ ማቅረብ አለበት እንዲሁም በምርጫው ዕለት ማታ ላይ በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የተለጠፉትን የውጤት ማሳወቂያ ቅጾች ስካን የተደረጉ ቅጂዎች (scans) በኢንተርኔት ይፋ ሊያደርግ ይችላል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዓለም አቀፍ እንዲሁም የዜጋ ታዛቢዎች ጊዜውን በጠበቀ መልኩ ዕውቅና ማግኘታቸውን ሊያረጋግጥ እና ለዜጋ ታዛቢዎች ዕውቅና የመስጠት ሂደቱን ቀላል ሊያደርግ ይገባል። የታዛቢ ባጅ የማከፋፈል ሂደቱን በንዑስ-ብሔራዊ ደረጃ በመከፋፈል ያልተማከለ ማድረግ ሂደቱን ሊያቀላጥፈው እና ለወደፊት የሚደረጉ ምርጫዎች ላይ የዕውቅና አሰጣጥ በጊዜው እንዲከናወን የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ሊፈጠር ይችላል።

### ከረጅም ጊዜ አንጻር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በዜጎች መረጃ የመጠየቅ እና የማወቅ መብት መሠረት በምርጫ ሂደት ውስጥ ያለውን ግልጽነት ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ አዎንታዊ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት። በህዝብ ዘንድ መተማመን ስሜትን ለመገንባት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከግልጽ የምርጫ መረጃ ኢኒሼቲቭ (Open Election Data Initiative) ጋር በሚጣጣም መልኩ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳውን እና ሌሎች ወቅታዊ መረጃዎችን ይፋ ማድረግ፣ የዕጩዎች ዝርዝሮችን ጊዜውን በጠበቀ እና በቀላሉ ማግኘት በሚቻል መልኩ ማውጣት እና እንደ የመራጮች ምዝገባ አሀዞች ያሉ መረጃዎችን ህዝቡ ማግኘት እንዲችል ማድረግ አለበት።[69] በተጨማሪም የኢትዮጵያ

69 የግልጽ የምርጫ መረጃ ኢኒሼቲቭን (Open Election Data Initiative) ድረገጽ እና መርሆዎች ይመልከቱ።

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የዕጩዎች ምዝገባ እንደተጠናቀቀ የዕጩዎች ዝርዝሮችን ይፋ ማድረግ ያለበት ከመሆኑም በላይ ዕጩ የመለወጥ እና ከምርጫው ራስን የማግለል ተግባራት ለህዝቡ ሊገለጹ ይገባል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ካለማቋረጥ እንዲሻሻል የሚያስችል ዘዴን ጨምሮ አካታች እና ቋሚ የሆነ የመራጮች መዝገብ ሊያዘጋጅ ይገባል።

በምርጫ ክልሎች መካከል የድምጽ ዕኩልነት መኖሩን ለማረጋገጥ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል። በዚህ ረገድ በምርጫ ክልሎች መካከል ያሉት ልዩነቶች በዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮ መሠረት በሕጉ ከተቀመጠው 15 በመቶ መብለጥ የለባቸውም። ሁሉን አቀፍ ብሔራዊ የህዝብ ቆጠራ ከተከናወነ በኋላ እንደ አዲስ የማካለል ሥራ ሊጀመር ይገባል፤ እንዲህ ያለው የህዝብ ቆጠራ ካልተከናወነ ግን ምን ዓይነት እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው ስምምነት ላይ ለመድረስ ሁሉን አቀፍ የሆነ ውይይት ሊደረግ ይገባል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን በማሻሻል ረገድ የተሰሩ የመጀመሪያ ሥራዎችን ለማጠናከር እና ለማስፋፋት በዋና መሥሪያ ቤት፣ በክልል እና በምርጫ ክልል ደረጃ ያሉ ሠራተኞቹን ዓቅም በማሳደግ ተቋማዊ ጽናትን ለመገንባት የሚያስችሉ የስልጠና ፕሮግራሞች ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል።

# ጸጥታ እና በምርጫ ሂደት የሚፈጠሩ ግጭቶች

## ከአጭር ጊዜ አንጻር

አፈጻጸሙን ለማቀላጠፍ፣ ግልጽነትን ለማሻሻል እና ሚሊሻዎች እንዳይሳተፉ ለመከላከል ሲባል የምርጫ ጸጥታ አካላት መመሪያ ቁ. 12/2013 ከምርጫ ጋር በተያያዘ ጸጥታ የማስጠበቅ ስልጠን የተሰጣቸው የጸጥታ ኤጀንሲዎችን ለይቶ ሊያስቀምጥ እና ኃላፊነቶቻቸውን ዘርዝሮ ሊገልጽ ይገባል።

ጳጉሜ 1 በሚደረገው ምርጫ እንዲሁም ለወደፊቱ በሚደረጉ ምርጫዎች ውስጥ የሴቶች እይታዎች እና በምርጫ ሂደት በሴቶች ላይ ከሚፈጸሙ ጥቃቶች ጋር በተያያዘ ያሏቸው ተሞክሮዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ በታዛቢ ቡድኖች፣ በጸጥታ መስሪያ ቤቶች እና በምርጫ ሂደት የሚፈጠሩ ግጭቶችን የመቆጣጠር እና የመቀነስ ኃላፊነት ባላቸው ሌሎች አካላት አመራር እና ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ሊካተቱ ይገባል።

## ከረጅም ጊዜ አንጻር

በምርጫ ሂደት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን እና ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ በሆነ መልኩ ሥራቸውን ማከናወንን ጨምሮ በሕግ ለተቋቋሙ የጸጥታ አካላት የሚሰጡ ስልጠናዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲሁም ለዘላቂው ሰብአዊ መብቶችን፣ የፖለቲካ እና ሲቪል መብቶችን፣ በምርጫ ሂደት የሚፈጠሩ ግጭቶችን እና የምርጫ ጸጥታን ባካተተ መልኩ ሊሻሻሉ ይገባል፤ ይህም የጸጥታ አገልግሎት ሰጪዎችን ይበልጥ ሞያ የተላበሱ እና ከወገንተኝነት ነጻ ያደርጋል እንዲሁም በሴቶች፣ በተለያዩ ብሔረሰቦች፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና በወጣቶች ላይ ባተኮረ መልኩ በኢትዮጵያ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ቡድኖች ይበልጥ ደህንነቱ የተጠበቀ የምርጫ ምህደር እንዲፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል።

በምርጫ ወቅት እንዲሁም በምርጫዎች መካካል በክልሎች ውይይት እና ዕርቅ እንዲደረግ ለማመቻቸት በምርጫ ሂደት የሚፈጠሩ ግጭቶችን የመከላከያ የጋራ መድረኩ (Joint Election Violence Prevention Platform) ቋሚ መድረክ ተደርጎ ሊቋቋም ይገባል እንዲሁም ሴቶች እና ሌሎች የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በሚያጋጥሟቸው የተለዩ የጥቃት ስጋቶች ዙሪያ ስልጠና ሊያገኙ ይገባል።

የጸጥታ መሥሪያ ቤቶች ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና ከዜጋ ታዛቢ ቡድኖች ጋር ይበልጥ በቅርበት ሊሰሩ ይገባል እንዲሁም በምርጫው ቀን የሚኖቸውን ስምሪት በተመለከተ ይበልጥ ግልጽ ሊሆኑ ይገባል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የክልል ቅርንጫፎቹን በጸጥታ ስጋት ምዘና ውስጥ ሊያሳትፍ እና የምርጫ ጸጥታን በተመከተ ለታዛቢ ቡድኖች ይበልጥ ግልጽ ሊሆን ይገባል።

# የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የምርጫው ምህዳር

## ከአጭር ጊዜ አንጻር

የፖለቲካ ፓርቲዎች በማህበራዊ ሚዲያ እና በዲጂታል መገናኛ ዘዴዎች ጨምሮ አመጽን፣ ማስፈራራትን፣ ጠብ አጫሪነትን እና የጥላቻ ንግግርን ላለመጠቀም በይፋ ቃል ሊገቡ እና ሊያወግዙ እንዲሁም አክቲቪስቶቻቸውን እና ደጋፊዎቻቸውን ለማስተማር እና ከዚያ የተለየ ድርጊት የሚፈጽሙ አባሎቻቸው ላይ የስነ-ምግባር እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ እርምጃዎን መውሰድ አለባቸው።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ጉባዔው በሁሉም ደረጃዎች ሊጠናከር እና ጳጉሜ 1 ለሚደረገው እና ለወደፊት ለሚደረጉ ምርጫዎች የውይይት እና የግጭት መፍቻ መድረኮችን ለማመቻቸት ጥቅም ላይ ሊውል ይገባል።

## ከረጅም ጊዜ አንጻር

ከመቶ ቢያንስ የተወሰኑ ሴት ዕጩዎችን ለሚያስመዘግቡ ወይም የተወሰኑ ሴት የፓርቲ አመራሮች ላሏቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች መንግስት የሚሰጠውን ድጎማ ለማግኘት የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላትን ጨምሮ ነገር ግን በዚያ ሳይወሰን የፖለቲካ ፓርቲዎች ሴቶች፣ ወጣቶች እና ሌሎች የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በፓርቲዎች ውስጥ የኃላፊነት እና የአመራር ቦታዎች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሻሻል ጠንካራ ሥራዎችን መሥራት አለባቸው።

ያላቸውን ድጋፍ ለመገንባት እና መራጮች መረጃን መሠረት ያደረጉ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ለማስቻል ፓርቲዎች እና ዕጩዎች ዕድሉ ሲኖር በክርክሮች ላይ መሳተፍ አለባቸው። የፖለቲካ ፓርቲዎች ዓለማዎቻቸውን እና መርሀ ግብሮቻቸውን ይፋ እንዲያደርጉ እና ሴቶች፣ ወጣቶች እና ሌሎች የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ ጉዳዮችን እና የመንግስት ፖሊሲዎችን በተመለከተ ሊኖር ስለሚገባው አቀራረብ ያሏቸውን አመለካከቶች ባካተተ መልኩ እንዲከልሱ ሊበረታቱ ይገባል። የማዳረስ (outreach) አቅማቸውን ማሳደግ እና እንደ ነጻ የአየር ሰዓት እና የጋዜጣ አምዶች ያሉ ከመንግስት በተዘዋዋሪ የሚሰጡ ድጎማዎችን ጥቅም ላይ ማዋል አለባቸው።.

# ማካተት

## ሴቶችን ማካተት

የፌዴራል እና የክልል ባለስልጣን አካላት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ የጾታ ዕኩልነት እና የሴቶች መብት ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በሙሉ የተለያዩ የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች አባላት የሆኑ ሴቶን ጨምሮ የተለያዩ ሴቶች በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደቶች፣ አመራር እና ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ይበልጥ እንዲሳተፉ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው። ይህም ከሌሎች እርምጃዎች በተጨማሪ በፌዴራል፣ በአካባቢ እና በፓርቲ ደረጃ የጾታ ኮታዎችን በሕግ በማስቀመጥ ዙሪያ ውይይት ማድረግን ሊያካትት ይችላል።

የፌዴራል እና የክልል ሕጎች ሁሉንም ዓይነት የጾታ መድሎ በሚያስወግድ እንዲሁም በተለይም ደግሞ ጾታዊ ጥቃትን እና በምርጫ ሂደት ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃትን ወንጀል በሚያደርግ መልኩ ሊሻሻሉ ይገባል።

ራቅ ባሉ አካባቢዎች ሴቶች በምርጫ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖችን እና ባህላዊ ማህበራዊ መዋቅሮችን ባሳተፈ መልኩ ለመራጮች ስልጠና እና ለሴቶች አውትሪች (outreach) ልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

## የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ማካተት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በመደበኛ የምርጫ ጣቢያዎች የሚመዘገቡበትን ሁኔታ የሚያመቻቹ እርምጃዎችን ተግባራዊ በማድረግ እና በተለይም ደግሞ በአካባቢው ባለ ማህበረሰብ ውስጥ ለሚኖሩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የነዋሪነት መስፈርቶችን በማሻሻል በምርጫው ሂደት ውስጥ ይበልጥ እንዲካተቱ ማድረግ አለበት።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በልዩ እና በመደበኛ የምርጫ ጣቢያዎች ድምጽ የሰጡ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የተመለከተ መረጃ በመሰብሰብ፣ ከፋፍሎ በማቅረብ እና ይፋ በማድረግ ለወደፊት በሚደረጉ ምርጫዎች ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ለመለካት የሚያስችል አስተማማኝ ማነጻጸሪያ (baseline) ማዘጋጀት ይችላል።

## በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሔረሰቦችን እና ቋንቋዎችን ማካተት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና ሲቪል ማህበራት በገጠር ማህበረሰቦች ውስጥ እና በተለይም ደግሞ በጣም ለየት ባሉ አካባቢዎች ለመራጮች የሚሰጡ መረጃዎች እና ስልጠና በስፋት መዳረሱን ለማረጋገጥ በቁጥር አናሳ ለሆኑ የብሔር እና የቋንቋ ማህበረሰቦች ተስማሚ የሆኑ የማዳረስ (outreach) እና የግንኙነት ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀት አለበት።

የፖለቲካ ፓርቲዎች በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሔረሰቦች አባላትን በአስተዳደር መዋቅራቸው ውስጥ ለመመልመል፣ ለማሰልጠን እና የደረጃ ዕድገት ለመስጠት የሚያስችሉ የውስጥ ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት አለባቸው።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግስቱ በተሰጠው ስልጣን እና በሕጉ መሰረት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ልዩ ውክልና ለማግኘት መስፈርቱን የሚያሟሉ በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሔረሰቦች የሚለዩባቸውን መስፈርቶች ሊያዘጋጅ ይገባል።[70]

## የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችን ማካተት

የምርጫ አስተዳደር፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች አካላት በሁሉም የምርጫ ሂደቱ ክፍሎች ውስጥ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች እንዲካተቱ ለማድረግ ሥራዎችን መሥራታቸውን መቀጠል አለባቸው። የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ መስጫ ስፍራዎች ጋር ምንም ሳይስተጓጎሉ ራሳቸውን ችለው መድረስ መቻል እና ለመራጮች የሚሰጡ መረጃዎችን በብሬል ማግኘት አለባቸው እንዲሁም ማየት እና መስማት የተሳናቸው መራጮች በምልክት ቋንቋ የሚሰጥ የትርጉም አገልግሎት በስፋት ማግኘት መቻል ለባቸው።

## ወጣቶችን ማካተት

በምርጫ ሂደት ውስጥ የወጣቶችን ተሳትፎ ለማሳለጥ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ልዩ የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋምን ሊያስብበት ይገባል።

የፌዴራል እና የክልል ባለስልጣን አካላት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ወጣቶች በምርጫ እና በፖለቲካ ሂደቶች ውስጥ እንዲሳተፉ ለማበረታታት እና ለወጣቶች አሳሳቢ የሆኑ ጉዳዮችን እና አመለካከቶቻቸውን ለማካተት እና ለማስተናገድ በወጣቶች ላይ ጠንካራ የአውትሪች (outreach) ስራዎችን መስራት አለባቸው።

70 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. ያወጣውን "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ስልጣን እና ተግባራት የሚወስነውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ" አንቀጽ 62 ይመልከቱ።

## የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች፣ የዜጋ ምርጫ ታዛቢዎች እና የመራጮች ምዝገባ

በሲቪል ማህበራት የሚሠሩ የመራጮች ስልጠና ሥራዎች ራቅ ባሉ ወይም በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች የሚኖሩትን ጨምሮ ለተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ ሊከናወኑ ይገባል። ይበልጥ ስፋት ያለው ተሳትፎ መኖሩን ለማረጋገጥ የመራጮች ስልጠና እንቅስቃሴዎች ከመራጮች ምዝገባ ሂደቱ በጣም አስቀድመው መጀመር እና ይበልጥ ብዛት ያላቸው የግንኙነት ዘዴዎችን እና ቋንቋዎችን ጥቅም ላይ ማዋል አለባቸው።

በኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ለበርካታ ዓመታት እንቅስቃሴ ሳያደርጉ የቆዩ በመሆኑ የመራጮች ስልጠና፣ ሁሉን አቀፍ ምርጫ የመታዘብ እና ተያያዥ የምርጫ ተጠያቂነት እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስችል አቅም ላይኖራቸው ስለሚችል ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የሲቪል ማህበራትን አቅም ለመገንባት የሚሠሩ ሥራዎችን ቅኝት እንደገና ማስተካከል ይኖርበታል። በዚህ ረገድ የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በደንብ አስቀድሞ ድጋፍ መሰጠት አለበት።

## የመረጃው ምህዳር

የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁ. 1238/2013 ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ መደረጉ ሊረጋገጥ እና በሂደት ላይ ያሉ የመረጃ ተደራሽነትን፣ በኮምፒዩተር የሚፈጸሙ ወንጀሎችን እና የመረጃ ጥበቃን የሚመለከቱ አዋጆች በፍጥነት ሊጸድቁ ይገባል።

መግለጫዎቹ ሕገ ወጥ መሆናቸው በፍርድ ቤት ካልተረጋገጠ ወይም አመጽን የሚያነሳሱ ካልሆነ በስተቀር የሚዲያ ተቋማት ሦስተኛ ወገኖች ለሚያስተላልፏቸው ይዘቶች ተጠያቂ ሊደረጉ አይገባም።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን መገናኛ ብዙሀንን የመቆጣጠር አቅሙን ማሳደግ እና በምርጫው ወቅት የላቀ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ለማድረግ እንዲሁም መደበኛ፣ የኢንተርኔት እና ማህበራዊ ሚዲያ ክትትል ሪፖርቶችን ለማሰራጨት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር ተቀናጅቶ መሥራት አለበት።

የፖለቲካ እና የሲቪል ማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት ታማኝነት ያላቸው መረጃዎችን በቀላሉ መለየት እንዲችሉ መራጮችን ለማገዝ ለማህበራዊ ሚዲያ ገጾቻቸው “የተረጋገጠ” የሚል መለያ ማግኘትን ሊያስቡበት ይገባል።

የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና የመንግስት ባለሥልጣን አካላት የግላዊነት መብቶችን እና ሀሳብን የመግለጽ ነጻነትን ባረጋገጠ መልኩ ማህበራዊ ሚዲያ እና ሌሎች ዲጂታል የመረጃ መለዋወጫ መድረኮች ላይ ክትትል በማድረግ ሀሰተኛ መረጃዎችን የመለየት እና ለዚያ ምላሽ የመስጠት አቅማቸውን ማጠናከር አለባቸው። በተጨማሪም የሚዲያ አጠቃቀም ችሎታን እና የመረጃ ታማኝነትን የመጠበቅ ኃላፊነቶችን በተመለከተ የረጅም ጊዜ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል።

ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. የተደረገውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ የተመለከተ ሪፖርት

ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት

1225 Eye Street NW, Suite 800
Washington, DC 20005

info@iri.org

ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት

455 Massachusetts Ave NW, 8th
Floor Washington, DC 20001

http://www.ndi.org/contact